# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 83ኛ ዓመት ቁጥር 091 ታኅሣሥ 1 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!









# ለኢትዮጵያ

## የባሕር በር ማግኘት የተረጋጋ የፖለቲካ ምሕዳር ለመፍጠር ወሳኝ ነው

**ራስወርቅ ሙሉጌታ**

አዲስ አበባ፡- ለኢትዮጵያ የባሕር በር ማግኘት ከኢኮኖሚያዊ ፋይዳው ባለፈ የተረጋጋ የፖለቲካ ምሕዳር እንዲኖር ወሳኝ መሆኑን በወሎ ዩኒቨርስቲ የታሪክ መምህርና ተመራማሪ ዓለማየሁ እርቅይሁን(ዶ/ር) ተናገሩ።

ተመራማሪው እንደሚያብራሩት የባሕር በር መኖር ለአንድ ሀገር ዘርፈ ብዙ ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ አለው። እንደ ኢትዮጵያ ላሉ ሀገራት ደግሞ የባሕር በር መኖር ከዚህም ባለፈ የተረጋጋ የፖለቲካ ሁኔታ እንዲፈጠር ትልቅ አስተዋፅዖ ይኖረዋል።

በአሁኑ ወቅት የኑሮ ውድነት መጨመር እንዲሁም የሕዝብ ብዛትና የሥራ አጥ ቁጥር መጨመር በሀገሪቱ ይታያል ያሉት ዶክተር ዓለማየሁ፤ ይህ በቀጥታ የፖለቲካ አለመረጋጋት እንዲፈጠር በር የሚከፍት ነው ብለዋል።

በአንጻሩ የባሕር በር መኖር ምርቶችን ለውጪ ገበያ ለማቅረብና ወደ ሀገር ለማስገባት የሚረዳ ሲሆን ይህንን ተከትሎ የሥራ እድል ፈጠራም የሚስፋፋ ይሆናል። ጥያቄውም እነዚህ ችግሮች በተስፋፉበት በዚህ ወቅት በዚህ ትውልድ መቅረቡም ተገቢና ወቅቱን ያገናዘበ ነው ብለዋል።

በአሁኑ ወቅት እንደ አሜሪካ፤ ቻይና፤ ኢራንና ቱርክ የመሳሰሉት ሀገራት ጅቡቲን ጨምሮ ምሥራቅ አፍሪካን ለመቀራመትና ብሔራዊ ጥቅማቸውን ለማስጠበቅ

ለኢትዮጵያ የባሕር በር ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል












## ከ6 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ሦስተኛ ዙር ርዳታ ሊሰራጭ ነው

**ሞገስ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ፡- በተፈጥሮና በሰው ሠራሽ አደጋዎች ለተጎዱ ከ6 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ሦስተኛ ዙር ርዳታ ሊሰራጭ መሆኑን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን አስታወቀ፡፡

የኮሚሽኑ የሕዝብ ግንኙነት ከፍተኛ ባለሙያ አቶ አታለለ አቡሀይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት ባለፉት ጊዜያት ሁለት ጊዜ በተለያዩ አደጋዎች ለተጎዱ ዜጎች ርዳታ ማሰራጨቱን አስታውሰዋል፡፡

ከያዝነው ሳምንት ጀምሮም ለሦስተኛ ዙር ርዳታ ለማሰራጨት አጋር አካላትን በማስተባበር የቅድሚያ ቅድሚያ ርዳታ ለሚሹ፣ ትኩረትና ድጋፍ ለሚፈልጉ የኅብረተሰብ ክፍሎች ርዳታ ለማሰራጨት ዝግጅቱን ማጠናቀቁንም ገልጸዋል፡

እንደ አቶ አታለለ ገለጻ፤ በሦስተኛው ዙር በጎርፍ፣

ከ6 ነጥብ 5 ሚሊዮን... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ስምን?

**በሳሙኤል ወንደሰን**

በ2018 ዓመተ ምሕረት ማብቂያ ከ90 ሚሊዮን በላይ ዜጎች ብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ እንዲኖራቸው እንደሚደረግ የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮጀክት አስታውቋል። ለመሆኑ በኢትዮጵያ ብሔራዊ መታወቂያ ተግባራዊ መደረጉ ምን ፋይዳ አለው?

በብሔራዊ መታወቂያ ፕሮጀክት ከፍተኛ የፖሊሲና የሕግ አማካሪ የሆኑት አቶ በላይሁን ይርጋ ጉዳዩን አስመልክቶ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት በሰጡት ማብራሪያ ብሔራዊ መታወቂያ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሲደረግ ዓመታዊ የኢትዮጵያ ጂዲፒ በሰባት በመቶ እንደሚያድግ ይጠበቃል ይላሉ። ይህም ማለት አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብ በፋይናንስ ሥርዓቱ ውስጥ እንዲካተት የሚያደርግ መሆኑን ያነሳሉ።

አሁን ላይ ግን 70 በመቶ የሚሆነው ሕዝብ ከፋይናንስ ሥርዓቱ ውጭ ነው የሚሉት አቶ በላይሁን፤ ይህም የሀገሪቱ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው ሲሉ ይገልፃሉ።

እንደ አቶ በላይሁን ገለፃ፤ በኢትዮጵያ የዲጂታል መታወቂያ ሥርዓት መዘርጋት ነዋሪዎች የመታወቂያ መብታቸው እንዲረጋገጥ ይረዳል፡፡ ዜጎች ሌሎች መብቶችን የመጠቀም እድላቸው ይሰፋል፤ አገልግሎት ሰጪና ተቀባይ መካከል በሚኖር ግንኙነት ላይ እምነት እንዲዳብር ያደርጋል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃም የግልጽነት፣ የተጠያቂነትና የተሳለጠ አሠራር ሥርዓትን ለመዘርጋት ያስችላል ይላሉ።

ብሔራዊ መታወቂያ ሁሉም ዲጂታል አገልግሎቶች እና ግብይቶች በታመነ ማዕቀፍ ውስጥ ሊከናወኑ የሚችሉበት መሠረት ነው የሚሉት አቶ በላይሁን፤ የብሔራዊ መታወቂያ በአሁኑ ጊዜ የሚመራው በጠቅላይ ሚኒስትር ጽሕፈት ቤት ስር መሆኑን አንስተዋል።

የብሔራዊመታወቂያፕሮጀክትየተሻሻሉየፋይናንስ፣ የማኅበራዊ፣ የሕዝብ እና ሌሎች አገልግሎቶችን ተግባራዊ ሳይሆን መሠረታዊ ግለሰባዊ ዘዴዎችን በመጠቀም ሰውን የሚለዩ አገልግሎቶችን ለመስጠት በማቀድ ለሁሉም ነዋሪዎች ዲጂታል መታወቂያ እንዲመዘገብ እና እንዲሰጥ እየሠራ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

በብሔራዊ መታወቂያ ፕሮጀክት በ2018 ዓ.ም መጨረሻ ላይ በኢትዮጵያ ውስጥ ከ90 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ነዋሪዎች ዲጂታል መታወቂያ ለመስጠት ታቅዷል ያሉት አቶ በላይሁን፤ የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም በአሁኑ ወቅት የፋይዳ መታወቂያ ምዝገባን በተለያዩ ቦታዎች በመተግበር ላይ ይገኛል ብለዋል።

ብሐራዊ ዲጂታል ... ወደ ገጽ 6 ዞሯል

## በክልሉ ከ136 ሺህ በላይ አዳዲስ የቴክኒክና ሙያ ሠልጣኞችን ለመቀበል ዝግጅት ተደርጓል

ገጽ 6




# “በዓሉ ኅብረ ብሔራዊ ኢትዮጵያን ከማጽናት ባለፈ አለመረጋጋቶችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት ያስችላል”

- የዩኒቨርሲቲ ምሑራን

ታደሠ ብናልፈው



አዲስ አበባ፡- የብሔር ብሔረሰቦች ቀን በየዓመቱ መከበሩ ኅብረ ብሔራዊ ኢትዮጵያን ከማጽናት ባለፈ በሀገር ውስጥ የሚከሰቱ አለመረጋጋቶችን በሰላማዊ መንገድ በመፍታት ከፍተኛ ሚና ይጫወታል ሲሉ የዩኒቨርሲቲ ምሑራን ገለጹ፡፡

በዲላ ዩኒቨርሲቲ የሀገረሰባዊ ጥናት ተቋም መምህርና ተመራማሪ አበራ እያሱ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በየዓመቱ ኅዳር 29 የሚከበረው የብሔር ብሔርሰቦች ቀን ኅብረ ብሔራዊ ኢትዮጵያን ከማጽናት ባለፈ አለመረጋጋቶችን በሰላማዊ መንገድ በመፍታት ሰላምን ለማስፈን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም በዜጎች መካከል ያለው የመተሳሰብ የባሕል መስተጋብር እንዲጎለበት ያደርጋል ብለዋል፡፡

በዓሉ ብሔር ብሔረሰቦች የራሳቸውን ባሕል፣ ቋንቋ፣ ወግና ሥርዓት በእኩልነት የሚያንጸባርቁበትና በመካከላቸው የባሕል መስተጋብር በመፍጠር አንድነታቸውን የሚያጠናክሩበት ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ብሔር ብሔረሰቦች ቀን መከበሩ ኅብረ ብሔራዊ ኢትዮጵያን ከማጽናት ባለፈ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ፋይዳው የጎላ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በዓሉ የብሔር ብሔረሰቦችን ባሕልና የባሕል ምርቶችን የሚያለማ፣ የባሕል ኢንዱስትሪዎችን የሚያስፋፋ፣ ባሕል ተኮር የሆነ ኢኮኖሚ ለመገንባት የሚያስችል ነው ያሉት መምህር አበራ፤ በዓሉ የባሕል ኢንዱስትሪው እንዲለማ ትልቅ መነቃቃትንም እንደሚፈጥር አስገንዝበዋል፡፡

ይህም መሆኑም የቱሪስት ፍሰቱን በማሳደግ የሥራ እድል ለመፍጠርና የኢኮኖሚ እድገትን ለማምጣት ትልቅ ሚና ይጫወታል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

አንዱ ጋር ያለውን እውቀት ለሌላው ለማስተላለፍ፣ ያሉትን ባሕሎች የጋራ ለማድረግና ሀገር በቀል እውቀቶችን ለማልማት በዓሉ ትልቅ አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

የብሔር ብሔረሰቦች ቀን የባሕል፤ የቋንቋና የእምነት እኩልነትን በማረጋገጥ የአንዱ ባሕል ከአንዱ ይበልጣል የሚለውን አሉታዊ አስተሳሰብ በመቅረፍ የባሕል እኩልነትን የሚያረጋግጥ ነው ብለዋል፡፡

የሰመራ ዩኒቨርስቲ የሶሻል የአንትሮፖሎጂ መምህር አሊ አሕመድ በበኩላቸው፤ በዓሉ ኅብረ ብሔራዊ ኢትዮጵያን ከማጽናት ባለፈ አለመረጋጋቶችን በሰላማዊ መንገድ በመፍታት ሰላምን ለማፅናት ትልቅ ሚና ይጫወታል ብለዋል፡፡

በዓሉ መከበሩ የማኅበረሰቡን የመተሳሰብና የመረዳዳት መስተጋብሩ ይበልጥ እንዲዳብር በማድረግ ከፍተኛ ጥቅም ይሰጣል፤ በተለያዩ የባሕል ተፅዕኖዎች እየተሸረሸረ ያለውንም ባሕል ለመመለስና ከትውልድ ወደ ትውልድ ለማስተላለፍ ያስችላል ብለዋል፡፡

በዓሉ ሀገሪቱ የራሷ ባሕል፣ ማንነት ያላት መሆኗን ለዓለም ሕዝብ የምታሳይበት ነው ያሉት አቶ አሊ፤ የብዝኃ ባሕል ባለቤት መሆኗንም የሚረጋገጥበት ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

የእኔ ባሕል ነው ከሚል አስተሳሰብ ወጥተን የእኛ ባሕል ነው የሚል አስተሳሰብ እንዲኖረን በማድረግ የጋራ ባሕልና እሴት እንድንገነባ በዓሉ ቁልፍ ሚና ይጫወታል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

በዓሉ ያሉንን ልዩነቶችን አቻችለን በሰላምና በአንድነት እንድንኖር ከማድረግ ባለፈ ለሀገር ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ እድገት ይረዳል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

በዓሉ ሁሉም ብሔር እኩል መሆኑን በማሳየት ያለን ባሕል፤ ቋንቋና እምነት እንዲለሙ የሚያስችል ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

በዓሉ አንድነታችንን የምናፀናበትና ባሕላችንን የምናለማበት በመሆኑ አከባበሩ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት ሲሉም አመላክተዋል፡፡

# የኢትዮጵያ የዲፕሎማሲ አካሄድ ዘመኑን የዋጀ ነው

ራስወርቅ ሙሉጌታ

በቅርቡ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት 3ኛ ዓመት የሥራ ዘመን 4ኛ መደበኛ ስብሰባ ከምክር ቤት አባላት የሀገሪቱን ዲፕሎማሲን በተመለከተ ለቀረቡላቸው ጥያቄዎች በሰጡት ምላሽ የሀገር ውስጥ ፍላጎት ከሌሎች ጋር በሚኖር ትብብርና ስምምነት የሚፈጸም መሆኑን አመላክተው ነበር። የፖሊሲያችን መነሾዎችም አንደኛ ብሔራዊ ጥቅም፤ ሁለተኛ ሉዓላዊነት፤ ሦስተኛ መልክዓ ምድራዊ ታሪካዊ ትሩፋቶች መሆናቸውን የጠቆሙ ሲሆን፣ ይህም ጎረቤትን ያቀፈ ወደ ፊት የሚፈነጠር መሆኑን አመላክተው ነበር፡፡

በዋቻሞ ዩኒቨርሲቲ የፖለቲካል ሳይንስና ዓለም አቀፍ ግንኙነት ትምህርት ክፍል ኃላፊ፤ መምህርና ተመራማሪ የሆኑት አቶ ሙሉዓለም ኃይለማርያም እንደሚሉት፣ የአንድ ሀገር ዲፕሎማሲ እድገት የሚገመገምበት የራሱ መስፈርቶች አሉት። በዋናነትም ሀገሪቷ ያስቀመጠችውን የውጪ ፖሊሲ መሠረት የሚያደርግ ሲሆን፣ ከፖለቲካው አንጻር የሁለትዮሽና በባለ ብዙ ወገን የሚደረጉ የዲፕሎማሲ ግንኙነቶች ምን ይመስላሉ የሚለውን የሚያቅፍ ነው ይላሉ።

በዚህ ረገድ ወጣ ገባ የሚሉ አካሄዶች ቢታዩም ያለፉት ተከታታይ ዓመታት እንደአጠቃላይ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ አበረታች ለውጥ የተመዘገበበት እንደነበር የሚያነሱት አቶ ሙሉዓለም፣ ለውጡ ተከስቶ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ወደሥልጣን ከመጡበት ጀምሮ ያሉት ሁለት ዓመታት ጥሩ የሚባል የዲፕሎማሲ ሥራ ሲከናወን ቆይቷል ብለዋል።

ለዚህም የኢትዮ ኤርትራ የሰላም ስምምነት መፈረም፤ ኩርፊያ ውስጥ የነበሩና ከሰብዓዊ መብት አያያዝ ጋር ጥያቄ ሲያነሱ ከነበሩ ኃያላን ከሚባሉ ሀገራት ጋር የነበረው ግንኙነት መታደሱንም እንደ አብነት ጠቅሰዋል።

በአንጻሩ በሰሜን ተከስቶ የነበረው ጦርነት በዲፕሎማሲው ረገድ ጥሩ ያልሆኑ ተፅዕኖዎችም እንደነበሩት የጠቆሙት አቶ ሙሉዓለም፣ በዚህም በዋናነት የልማት ድጋፍ ከሚያደርጉ ሀገራት ጋር ያለው ግንኙነት መሻከር እንደታየበትም አንስተዋል፡፡

በዚህም ከአግዋ ከመውጣት ጀምሮ የተለያዩ ድጋፎችም ቀንሰው እንደነበር ጠቁመው፤ በአንጻሩ ደግሞ የፕሪቶሪያውን ስምምነት ተከትሎ ዲፕሎማሲው መነቃቃት በማሳየቱ ከአሜሪካና አውሮፓ ጋር ያለው ግንኙነት ወደነበረበት እየተመለሰ መሆኑን አንስተዋል። ለዚህም የዓለም ባንክ ፕሬዚዳንት የአሜሪካ የውጪ ጉዳይ ሚኒስትር እንዲሁም ከአውሮፓ ሀገራት ከፍተኛ ኃላፊዎች ወደኢትዮጵያ መጥተው ጉብኝትና ውይይቶችን ማካሄዳቸው እንደማሳያ አንስተዋል።

ይሄ ግንኙነቱ ቀስ በቀስ እየተሻሻለ መሄዱን የሚያሳይ ቢሆንም ሀገሪቷ ከሚጠበቅባት አንጻር ሲመዘን ግን ገና የሚጠበቁ በርካታ የዲፕሎማሲ ተግባራት እንዳሉም አቶ ሙሉዓለም ጠቁመዋል፡፡



አቶ ሙሉዓለም ኃይለማርያም

አቶ ሙሉዓለም እንደሚሉት፤ የዓለም አቀፍ ግንኙነት የተስተካከለ የሚሆነው የሀገር ውስጡ ነገር ሲስተካከል መሆኑ ይታወቃል። በመሆኑም ሁኔታዎችን ከሰሜኑ ጦርነት በፊት ወደነበሩበት ሁለት ዓመታት መመለስና ከዛም በተሻለ መዳዝ የሚጠበቅ ይሆናል።

እንደ አቶ ሙሉዓም ገለጻ፤ ከኢኮኖሚ አንጻር ዲፕሎማሲው ሲቃኝ የልማት ድጋፍ ከሀገራትም ከልማት ተቋማትም ምን ያህል እያገኘን ነው በሚለው ይሆናል። ይህም አንደኛ ምን ያህል ኢንቨስትመንት እየተሳባ ነው። ሁለተኛው በሀገሪቱ የተመረቱ ምርቶች ምን ያህል ለውጪ ገበያ እየዋሉ ነው። ሦስተኛ ቱሪዝም በመሳብ ረገድ ምን ያህል ውጤታማ ሆኗል የሚለው መታየት አለበት ብለዋል።

በዚህም ረገድ ሲታይ በፊት ይሰጥ የነበረው የልማት ድጋፍ እየቀጠለ ይገኛል። ከዓለም አቀፍ ተቋማት ጋር የሚኖረውም ግንኙነት እየተሻሻለ መጥቷል። የዓለም ባንክ የአውሮፓ ኅብረት አይ ኤም ኤፍ ለኢትዮጵያ ይሰጡ የነበረውን ድጋፍ ወደማቋረጥ ሄደው የነበሩበት ሁኔታ ተመልሶ ዛሬ እየቀጠለ ነው ሲሉም አንስተዋል።

ከዚህ ባለፈም በአሁኑ ወቅት ከኢኮኖሚ ረገድ እያደጉ ካሉ ሀገራት ጋር ያለን ግንኙነትም እየተጠናከረ ለመሆኑ ከብሪክስ ጋር ያለን ግንኙነት ያመላክታል ያሉት አቶ ሙሉዓለም፤ በብሪክስ አባል መሆን በሚቀጥሉት ጊዜያት ኢትዮጵያ የሚኖራትን ተደማጭነት የሚጨምር እንደሚሆንም ጠቁመዋል። በአፍሪካም ተሰሚነት ካላቸው ጠንካራ ሀገራት ጋር ያለን ግንኙነት እየጨመረ መጥቷል ብለዋል።

በሌላ በኩል የሀገሪቱ የውጪ ፖሊሲ ትኩረት ከሚያደርግባቸው ከምሥራቅ አፍሪካ ሀገራት ጋር ያለውን ግንኙነት ጠንካራ ለማድረግም ከሌላው ግዜ የተሻለ ሥራ ተሠርቷል ያሉት አቶ ሙሉዓለም፤ በዚህም የመንግሥት አቅጣጫ አዋጭ ነው ለማለት ይቻላል ይላሉ።

እንደ አቶ ሙሉዓለም ገለጻ፤ እነዚህ ሀገራት ከሽብር ጋር በተያያዘ የደህንነት ስጋት ያለባቸው ናቸው፣ በዚህ ረገድ ኢትዮጵያ በትብበር እየሠራች ትገኛለች። በኢኮኖሚውም መስከ ምሥራቅ አፍሪካ ደሀ ሀገራት ያሉበት ነው። በመሠረተ ልማት በኢኮኖሚ ለመተሳሰር ተነሳሽነቱን ወስዳ እየሠራች ትገኛለች። የኤሌክትሪክ አቅርቦት ነፃ የኢኮኖሚ ዞን ለመፍጠር የተጀመሩ ሥራዎችም አመላካች ናቸው።

በኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ታሪክ የዓረቡ ዓለምና ኢትዮጵያ የነበራቸው ግንኙነት በጥርጣሬ ላይ የተመሠረተ ነበር የሚሉት ምሑሩ፤ ነገር ግን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) ወደሥልጣን ከመጡ በኋላ መሻሻሎች መታየታቸውን ጠቅሰዋል፡፡

ከሳዑዲ ዓረቢያና ከዩናይትድ ዓረብ ኢምሬትስ ጋር በመሪዎች ደረጃ የተካሄዱ ግንኙነቶችን ስንመለከት አበረታች ውጤቶች የተገኙበት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል። ይህንን ተከትሎ የጫካ ፕሮጀክት፤ የቤተ መንግሥት እድሳት እና ለሌሎችም የተደረጉ ድጋፎች እንደሀገር ትልቅ ፋይዳ ያስገኙ ናቸው። በተጨማሪ ለተማሪዎች የተሰጠው የትምህርት እድል መመቻቸት የዲፕሎማሲ ግንኙነቱ ስር እንዲሰድ የሚያግዝና የለውጡ ማሳያ ነው ብለዋል።

በተመሳሳይ የኢትዮጵያ ዲፕሎማሲያዊ አካሄድ ከዘመኑ አንጻር ሲገመገም በቅድሚያ ሊታይ የሚገባው ዓለም አቀፉ ሁኔታ ያለበትን ነባራዊ ሁኔታ በመቃኘት ነው ያሉት አቶ ሙሉዓለም፤ በጥቅሉ ግን ወዳጅን በመጨመር ጠላትን የሚቀንስ አካሄድ ይጠበቃል ብለዋል። በዚህም የዓለም አሰላለፍ ምን ይመስላል? በየትኛው ጎራ ብንሰለፍ ወይንም ገለልተኛ ብንሆን በዘላቂነት ብሔራዊ ጥቅማችን ይጠበቃል? የሚለው ይመዘናል። አብዛኛውን ጊዜ በዓለም አቀፍ ግንኙነት ውስጥ አወዛጋቢ በሆኑ ጉዳዮች ላይ በተቻለ መጠን ከየትኛውም ጣልቃ ገብነት መታቀብ የተሻለ አማራጭ ነው። ምክንያቱም ዛሬ ወዳጅ የሆነ ነገ ጠላት ሊሆን ይችላል፤ በመሆኑም በየጉዳዩ መወገን ጠላት ሊያበዛ ይችላል ብለዋል።

በዚህ ረገድ የዓለም አሰላለፍ ሲታይ ላለፉት ሀያ ዓመታት ተፅዕኖ ፈጣሪ የነበረችው ሀገር አሜሪካ ብቻ ነበረች። በአሁኑ ወቅት ግን በርካታ ተፅዕኖ ፈጣሪ ሀገራት አሉ። ኢትዮጵያም ከአሜሪካም ሆነ ዛሬ ተፅዕኖ ፈጣሪ ከሚባሉት እንደነ ሩስያና ቻይና ካሉ ሀገራት ጋር ያላት ግንኙነት እንደተጠናከረ መቆየቱ ዲፕሎማሲው ዘመኑን እየዋጀ እየተጓዘ መሆኑን ያመላክታል ብለዋል።

# ኮሚሽኑ

## በአራት ወራት ከ40 ቢሊዮን ብር በላይ ሰብስቧል

- ከ512 ድርጅቶች ላይ የኦዲት ግኝት ተሰብስቧል

ሔርሞን ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ ጉምሩክ ኮሚሽን ከንግድ ማጭበርበርና ከኮንትሮባንድ ጋር ተያይዞ በድንገተኛ ፍተሻ እና ክትትል፣ እንዲሁም በመደበኛ ፍተሻ እና ሰነድ ምርመራ በአራት ወራት ውስጥ ከ40 ቢሊዮን ብር በላይ ማግኘቱን ገለፀ፡፡

የገቢዎች ሚኒስትር ወይዘሮ ዓይናለም ንጉሤ የአራት ወር ሪፖርት ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲያቀርቡ እንዳሉት፤ የኮንትሮባንድ ንግድ እያደገ ቢመጣም የባለሥልጣኑ ኮንትሮባንድ የመያዝ አቅምም እያደገ መምጣቱ ማየት ይቻላል፤ የዚህም ማሳያ በ2016 ዓ/ም በአራት ወር ውስጥ ከ40 ቢሊዮን ብር በላይ ማግኘት ተችሏል፡፡

ባለሥልጣኑ በ512 ድርጅቶች ላይ 3 ነጥብ አንድ ቢሊዮን ብር በኦዲት ግኝት ወለድና ቅጣት ሳይጨምር እንደሰበሰበም አስታውቀዋል፡፡ ከወጪ ኮንትሮባንድ ብቻ በአራት ወር ውስጥ 4 ነጥብ ሰባት ቢሊዮን ብር በቅጣት ማስገባቱንም በሪፖርቱ አመላክተዋል፡፡

በተመሳሳይ ከ312 ተጠርጣሪ ኮንትሮባዲስቶች ውስጥ 258 በቅንጅት ከተለያዩ አካላት በጋራ በመሆን በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ በተያዙት ላይም አስተማሪ እርምጃ መወሰዱን ገልጸዋል፡፡

በመሆኑም ከንግድ ማጭበርበርና ከኮንትሮባንድ ጋር ተያይዞ ባለሥልጣኑ በድንገተኛ ፍተሻ እና ክትትል፣ የቀረጥ ነፃ መብት አጠቃቀም እንዲሁም በመደበኛ ፍተሻ እና ሰነድ ምርመራ በአራት ወራት ውስጥ ከ40 ቢሊዮን ብር በላይ መገኘት ችሏል ብለዋል፡፡

የጉምሩክ ባለሥልጣን ከክልሎች ጋር እና ከተለያዩ የፀጥታ ተቋማት ጋር ያለውን ቅንጅት አጠናክሮ በእነዚህ አካላት ላይ የተጠናከረ እርምጃ እንደሚወስድ እየተሠራ እንደሆነም በመጠቆም፤ ባለሥልጣኑ አምና ከነበረው የሥራ አፈፃፀም ዘንድሮ ላይ አብላጫ ማሳየቱን ገልጸዋል፡፡

የገቢዎች ሚኒስቴር ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ(ዶ/ር) በተገኙበት 500 ለሚሆኑ ታማኝ የግብር ከፋዮች የሽልማት እና የዕውቅና ፕሮግራም ያደረገ ሲሆን፤ በየጊዜው ኅብረተሰቡ ግንዛቤ እንዲያገኝ እና የኮንትሮባንድ ንግድ አስከፊነት እንዲረዳ ሥልጠናዎች እንደሚሰጥም ተመላክቷል፡፡

ከሙስና፣ ሕገ ወጥ ሥራዎች እና ሌሎች መሰል ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ከሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት ለባለሥልጣኑ የተለያዩ ጥያቄዎች የቀረበለት ሲሆን፤ ወደፊት በቴክኖሎጂ በመቆጣጠር እና ሕዝቡ ግንዛቤ እንዲያገኝ በማድረግ የተለያዩ ሥራዎች በመሥራት ሕገ ወጥነትን እንደሚከላከልም ምላሽ ተሰጥቷል፡፡

# በኢትዮጵያ ጤነኛ የአመጋገብ ሥርዓትን የሚከተለው ማኅበረሰብ ከአንድ በመቶ ያነሰ ነው

**ዳግማዊት አበበ**

<u>አዲስ አበባ፡</u>- በኢትዮጵያ ጤነኛ የአመጋገብ ሥርዓትን የሚከተለው ማኅበረሰብ አንድ በመቶ የማይሞላ መሆኑን የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ፖሊሲ ጥናት ኢንስቲትዩት ያጠናው ጥናት አመላከተ፡፡

በኢንስቲትዩቱ ከፍተኛ ተመራማሪ እና የማኅበራዊና አካታችነት ልማት ጥናት ማዕከል አስተባባሪ ደሳለኝ አንሽሶ (ዶ/ር) እንደገለጹት፤ የአመጋገብ ሥርዓት ጤናማነትን አስመልክቶ ከጋምቤላና ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች ውጭ ሁሉንም ክልሎችና ሁለቱን ከተማ አስተዳደሮች ባካተተ መልኩ ጥናት ተካሂዷል።

በተጠናው ጥናት መሠረትም በኢትዮጵያ ጤነኛ የአመጋገብ ሥርዓትን የሚከተለው ማኅበረሰብ አንድ በመቶ የማይሞላ ነው ብለዋል፡፡

ጥናቱ የተሰበሰበው በሁለት ዙር ሲሆን ከምርት በፊት 2014 ዓ.ም ነሐሴና መስከረም ላይ እንዲሁም በ2015 ዓ.ም ከምርት በኋላ የካቲትና መጋቢት ላይ መሆኑን ተመራማሪው፤ ጥናቱ የአንድ ሺህ 974 አባወራዎች ናሙና ተወስዶ የተካሄደ ብለዋል፡፡

የጥናቱ ግኝት እንደሚያሳየውም በኢትዮጵያ በሁሉም ክልል ላይ አንድ በመቶ የማይሞላ ሰው ብቻ ጤነኛ የምግብ አመጋገብ ሥርዓትን እንደሚከተል ማወቅ ተችሏል ያሉት ተመራማሪው፣ ይህም በተለያዩ ምክንያቶች እንደሆነ ጠቁመዋል፡፡

እንደ ተመራማሪው ገለጻ፣ ጥናቱ በየአካባቢው ምን ምርት ይመረታል፤ የሚዳዳዘው የምርት አይነትስ ምን አይነት ነው፤ በገበያ፣ በትራንስፖርትና በአመራረት ሥርዓት ውስጥ ያሉት ችግሮች ምን ምን ናቸው የሚለውንም የያዘ ነው፡፡

አንድ ሰው ጤነኛ አመጋገብ ተመግቧል የሚያስብለው በሚመገበው ምግብ ውስጥ ማግኘት ያለበት ካሎሪና ኃይል ሰጪ ንጥረ ነገር ሲኖር ነው ያሉት ተመራማሪው በኢትዮጵያ ግን ይህ ተግባራዊ እየሆነ አይደለም ብለዋል፡፡ ይንንም የአመጋገብ ሥርዓት እንዲዛባ ያደረገው በአብዛኛው በኢትዮጵያ ያለው የአመጋገብ ሥርዓት ባሕልና ግንዛቤ ማነስ ነው ሲሉም ገልጸዋል ፡፡



በሀገራችን አብዛኛው ማኅበረሰብ ከስድስት የምግብ ዘርፎች ስታርች ፉድ የሚባሉትን ወይም አትክልትን መመገብ ያዘወትራል፡፡ በቫይታሚንና በፕሮቲን የበለጸጉትን እንደ የቅባት እህሎች፣ ፍራፍሬ፣ የእንስሳት ተዋፅዖ፣ የዓሣ ስጋ፣ እንቁላል የመሳሰሉትን የሚመገበው ሰው ከአንድ በመቶ በታች ነው ፡፡

ጥናቱን ለማድረግ ያነሳሱት ምክንያቶች ከአመጋገብ ሥርዓት ጋር ተያይዞ የተወሰኑ መመሪያዎችና ስትራቴጂዎች፣ የኢትዮጵያ ኅብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት ጋር እንደዚሁም ከሌሎች የዘርፉ ባለድርሻ አካላት ጋር የተሠሩ ሥራዎች ቢኖሩም ወደታች ተወርዶ ሲታይ እነዚህ የወጡ ስትራቴጂዎችና መመሪያዎች መሬት ላይ ተግባራዊ መሆናቸውን የሚያሣይ ጥናት ባለመኖሩ ነው ሲሉ ገልጸዋል ፡፡

ለዚህም ጥናቱ እንደ መፍትሔ ሃሳብ ያቀረበው የምግብ ተደራሽትን ማሳደግ አንዱ ሲሆን ሀገሪቱ ላይ አንድ ሰው ሲመገብ ምን የምግብ ዓይነቶችን በቀን መውሰድ እንዳለበትና ከየትኛው የምግብ ዓይነት ምን ያህል መመገብ እንዳለበት በቂ ግዛቤ መፍጠር ላይ ሊሠራ እንደሚገባ አሳስበዋል፡፡

የአመጋገብ ሥርዓቱ ጤናማ የሚያስብለው ከሁሉም አይነት በመጠን መመገብ ሲቻል መሆኑን ጠቅሰው፤ ከዚህ አኳያ ሰፊ ግንዛቤ መፍጠር ይጠበቃል ሲሉም አክለዋል።



ወይዘሮ በቀለች ኩማ

# ለሕዝብ ትራንስፖርት ከ25 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በላይ የነዳጅ ክፍያ ድጎማ ተደርጓል

**መክሊት ወንድወሰን**

<u>አዲስ አበባ፡</u>- ለሕዝብ መገልገያ ትራንስፖርቶች የድጎማ አሠራር ተግባራዊ ከተደረገ ጀምሮ ከ198 ሺ. በላይ ለሚሆኑ ተሽከርካሪዎች ከ25 ነጥብ 2 ቢሊዮን ብር በላይ ድጎማ መደረጉን እና ከ124 ነጥብ 3 ቢሊዮን ብር በላይ ነዳጅ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ግብይት መፈጸሙን የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን ገለጸ፡፡

የነዳጅና ኢነርጂ ባለሥልጣን የሕዝብ ግንኙነት ዳይሬክተር ወይዘሮ በቀለች ኩማ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት የታለመ ድጎማ አሠራር ተግባራዊ ከተደረገ ከሐምሌ 2014 ዓ.ም ጀምሮ ለ198ሺህ 237 ተሽከርካሪዎች በጥቅሉ ብር 25 ቢሊዮን 21 ሚሊዮን 777 ሺህ 203 ብር ድጎማ ተደርጓል፡፡

ከዚህ ቀደም የነበረው የድጎማ አሠራር በየዓመቱ ሀገሪቱን በቢሊዮን የሚቆጠር ብር ያሳጣ እንደነበር የተናገሩት ዳይሬክተሯ፤ የድጎማ ሥርዓቱ የነዳጅ ኮንትሮባንድ እንዲካሄድ ምክንያት ነበር ብለዋል።

"የታለመለት የነዳጅ ድጎማ" በሚል ተግባራዊ እየሆነ በሚገኘው አዲሱ የድጎማ አሠራር ለሕዝብ የትራንስፖርት አገልግሎት የሚሰጡ ተሽከርካሪዎች በተለየ መልኩ ተጠቃሚ እያደረገ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

ባለፉት ወራት በተደረጉት ተከታታይ የዋጋ ማስተካከያዎች ምክንያት ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያለውን የዋጋ ልዩነት በከፍተኛ መጠን ማጥበብ መቻሉንም ጠቅሰዋል፡፡ በዚህም ነዳጅን በኮንትሮባንድ መልክ ወደ ጎረቤት ሀገሮች የማሻገር ፍላጎት በከፍተኛ መጠን ቀንሷል ብለዋል፡፡

ለኮንትሮባንድ ተጋላጭ ወደሆኑ አካባቢዎች ሲሰራጭ የነበረውን ነዳጅ በኮታ ሥርዓት እንዲተዳደር በመደረጉ ከፍተኛ የሆነ የነዳጅ ብክነትን ማስቀረት እንደተቻለ ገልጸው፤ ወደ እነዚህ አካባቢዎች ሲሄድ የነበረውን የነዳጅ መጠን በሱማሌ ክልል 69 በመቶ በምዕራብ ኦሮሚያ እስከ 60 በመቶ መቀነስ እንደተቻለ ዳይሬክተሯ ተናግረዋል፡፡

ከተቀመጠው አሠራር ውጭ አገልግሎት በማይሰጡና ነዳጅ ሳይቀዱ የድጎማ ክፍያ ለሚጠቀሙ ተሽከርካሪዎች ትብብር በሚፈጽሙ አምስት ነዳጅ ማደያዎች ላይ አስተዳደራዊ ርምጃ ተወስዷል።

በተጨማሪም አጠቃላይ ካሉት 1ሺ. 553 የነዳጅ ማደያዎች ውስጥ/የትግራይን ክልል ጨምሮ/ 1ሺ. 476 የሚሆኑት በቴሌ ብር ተመዝግበዋል፡፡ ከነዚህ ውስጥ 1ሺ. 387 ማደያዎች ተግባራዊ የንግድ ልውውጥ ጀምረዋል፡፡ በዚህም እስከ ጥቅምት 30 ቀን 2016 ዓ.ም ድረስ ከ124 ነጥብ 3ቢሊዮን ብር በላይ ነዳጅ በኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ግብይት መፈጸሙን ተናግረዋል፡፡

ለሕዝብ ትራንስፖርት አገልግሎት ሰጭዎች የነዳጅ ድጎማ መደረግ የተጀመረው ሐምሌ 2014 ዓ.ም መሆኑ እና የኤሌክትሮኒክስ የነዳጅ ሽያጭ ክፍያ በአዲስ አበባ ሚያዝያ 24 ቀን 2015 እንዲሁም በመላው ሀገሪቱ ግንቦት 1 ቀን 2015 ዓ.ም ተግባራዊ መደረጉ ይታወሳል፡፡

# የፖሊሲ ግብዓት ለማሰባሰብ የሚጠቅም የአሠሪና ሠራተኛች ጉባኤ ሊካሄድ ነው

## • ኢትዮጵያ የዓለም ሥራ ድርጅት አባል የሆነችበት 100ኛ ዓመት ይከበራል

**ዳግማዊት ግርማ**

<u>አዲስ አበባ፡</u>- ባለድርሻ አካላትን ያቀናጀ ለፖሊሲ ግብዓት የሚጠቅም ውይይት የሚካሄድበት “ማኅበራዊ ምክክርንና የጎለበተ ምርታማነትን በመጠቀም ማኅበራዊ ፍትሕን ማላቅ” በሚል መሪ ሃሳብ የአሠሪና ሠራተኞች ጉባኤ ሊያካሂድ መሆኑን የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ገለጸ፡፡

ተቋሙ ለዝግጅት ክፍሉ በላከው መግለጫ እንዳስታወቀው፤ ኢትዮጵያ የዓለም ሥራ ድርጅት አባል የሆነችበትን 100ኛ ዓመት ክብረ በዓል እና የ2016 ዓ.ም ሀገር አቀፍ የአሠሪና ሠራተኛ ጉባኤ የከፍተኛ ደረጃ መድረክ ከታኅሣሥ 4 እስከ 6 ቀን 2016 በአዲስ አበባ ይካሄዳል፡፡

ጉባኤው የሚዘጋጀው የሥራና ክህሎት ሚኒስቴር ከዓለም የሥራ ድርጅት፣ ከኢትዮጵያ ሠራተኛ ማኅበራት ኮንፌዴሬሽን፣ ከኢትዮጵያ አሠሪዎች ማኅበር እና ከኢትዮጵያ አሠሪዎች ፌዴሬሽን ኮንፌዴሬሽን ጋር በመተባበር ነው፡፡

ጉባዔው በሥራው ዓለም ያሉ ባለድርሻ አካላትን በማቀናጀት ትርጉም ያለው የፖሊሲ ውይይት፣ የሦስትዮሽ ምክክር እና የጋራ መማማርን በማስተዋወቅ እንደ መሳሪያ መድረክ ሆኖ ያገለግላል።

በመጪው መድረክ በዋናነት በሦስትዮሽ አጀንዳዎች ላይ በማተኮር፣ እንደ ማዕከላዊ ሀገር አቀፍ ትኩረት አስፈላጊነት በማጉላት በኢትዮጵያ የሥራ ገበያ ውስጥ ያሉ ልዩ ልዩ ተዋናዮች ላበረከቱት አስተዋፅዖ ክብርና እውቅናን ይሰጣል።

ይህ የትብብር ከባቢ የሃሳብ፣ የልምምዶች እና የበጎ ልምዶች ግልጽ ልውውጥን ያበረታታል፣ ተሳታፊዎች ተግዳሮቶችን በጋራ እንዲለዩ እና በፍትሐዊ ሽግግር ላይ የተመሠረተ ሰውን ያማከለ ልማት እና ሥነ-ምሕዳራዊ ጥበቃን ለማሳካት በማለም ምቹ የሥራ ጉድለቶችን፣ ድህነትን እና የተጋነነ የኑሮ ልዩነትን ለመፍታት ተግባራዊ እና ውጤታማ መፍትሔዎችን ለማግኘት በጋራ እንዲሠሩ ያበረታታል ተብሏል።

"በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሁሉም ሠራተኞች ምቹ ሥራ እንዲኖራቸው እና መሠረታዊ የሥራ መብቶቻቸው እንዲጠበቅ ለማድረግ ቁርጠኞች ነን ያለው መግለጫው፤ የሠራተኛ አስተዳደር ሥርዓትን ለማጠናከር፣ የሠራተኛ ጥበቃ ሽፋንን በሁሉም የሠራተኞች ምድብ ለማስቀጠል፣ በአሠሪዎች እና በሠራተኞች መካከል ማኅበራዊ ምክክርን ለማሳደግ ከዓለም የሥራ ድርጅት እና ሌሎች አጋሮች ጋር እየሠራ መሆኑን አመልክቷል፡፡

መንግሥት፣ ሠራተኞች እና አሠሪዎች ከአዳዲስ ስር ነቀል ለውጥ ጋር ለመስማማት እና የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳዮች አሠራሮች ለሚሳተፉበት ሁሉ አስፈላጊ እና ጠቃሚ ሆነው እንዲዘልቁ ለማድረግ ቀጣይነት ያለው ውይይት ማድረግ እንዳለባቸውም አመልክቷል።

ባለፉት 100 ዓመታት ውስጥ የኢትዮጵያ የአሠሪና ሠራተኛ አስተዳደር በከፍተኛ ደረጃ እድገት አሳይቷል፡፡ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር የኢትዮጵያ ሠራተኞች መብቶች እንዲጠበቁ ድጋፍ በማድረግ፣ የአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ሕጎች፣ የውጭ ሀገር የሥራ ስምሪት አዋጅና የማስፈጸሚያ ዘዴዎች በማጠናከር ውጤትን አስገኝቷል።

ጥረቶቹ በአሠሪዎች፣ በሠራተኞች እና በመንግሥት መካከል ማኅበራዊ ምክክርን በማበረታታት፣ በኢትዮጵያ የተሻለ የአሠሪና ሠራተኛ ግንኙነቶችን እንዲኖር ማድረጉንም መግለጫው ጠቅሷል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የአየር ኃይላችን አሁናዊ ቁመና የሚያስተላልፈው መልዕክት ከፍ ያለ ነው!

አንድ ሀገር ሉዓላዊነቷን አስከብራ ለመቀጠልም ሆነ የሕዝቦቿን ሰላምና ደህንነት አስተማማኝ ለማድረግ ከሁሉም በላይ በመከላከያ ዘርፍ የሚኖራት ሁለንተናዊ ዝግጁነት ወሳኝ ነው። በዚህ ዘርፍ የሚኖር የትኛውም ዓይነት ክፍተት ሀገርን በግልጽም ይሁን በስውር ለከፋ አደጋ መጋበዝ የሚያስችል አቅም እንዳለው ይታመናል።

የቴክኖሎጂ ልህቀት የመከላከያ ኢንዱስትሪውን በከፍተኛ ደረጃ እያዘመነ ባለበት በዚህ ዘመን፤ ሀገራት ባላቸው አቅም መከላከያቸውን ማዘመን ካልቻሉ፤ የሀገራቱ ህልውናም ሆነ የሕዝቦቻቸውን ደህንነት በየትኛው ሰዓት ከእጃቸው እንደሚወጣ እርግጠኛ መሆን ይቻላል። ይህ ደግሞ በዓለም አቀፍ ደረጃ ባለፉት ሶስት አስርት ዓመታት በተጨባጭ እየታየ ያለ እውነታ ነው።

በተለይም እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ውድቀታቸውን የሚሹ፤ እንደ ጥላ በየዘመኑ የሚከተሏቸው ጠላቶች ያሏቸው ሀገራት፤ ከጠላቶቻቸው የልብ መሻትና ሴራ ራሳቸውን መታደግ የሚችሉት ጠንካራና አስተማማኝ፤ ዘመኑን የሚዋጅ የመከላከያ ሠራዊት መገንባት ሲችሉና ይህንኑም በቀጣይነት አጠናክረው ሲቀጥሉ ብቻ ነው።

ይህን እውነታ በአግባቡ የተረዳው የለውጡ መንግሥትም ወደ ሥልጣን ከመጣ ማግስት አንስቶ የመከላከያ ሠራዊቱን ሁለንተናዊ አቅም ማሳደግ የሚያስችሉ የሪፎርም ሥራዎችን ተግባራዊ ሲያደርግ ቆይቷል። በዚህም የሠራዊቱ ሕዝባዊነት ሆነ አሁነኛ ግዳጅ የመፈጸም ብቃት በከፍተኛ ደረጃ አድጓል። የሀገርም የሕዝባችንም ብሄራዊ ክብር ምንጭ እየሆነም ይገኛል።

ሠራዊቱ እየታጠቃቸው ያሉ ዘመናዊ የጦር መሣሪያዎች፤ በተለያዩ ሥልጠናዎች እያካበታቸው ያሉ ሙያዊ ክህሎቶች፤ ኢትዮጵያዊ ከሆነው ጀግንነትና ልበ ሙሉነት ጋር ተዳምሮ ለጠላትም ሆነ ለወዳጅ ተገቢ መልዕክት ማስተላለፍ የሚያስችልበት ደረጃ ላይ ስለመድረሱ ባለፉት ሁለት ዓመታት እያስተዋልናቸው ያሉ እውነታዎች ማሳያ ናቸው።

ለዚህም በኢትዮጵያ አየር ኃይል ዙሪያ እየተደረጉ ያሉ የሪፎርም ሥራዎችን እና እየተመዘገቡ ያሉ አንጸባራቂ ስኬቶችን ማንሳት ይቻላል። የሀገሪቱ የመከላከያ ሠራዊት ዋነኛ አካል የሆነው ይህ ተቋም ፤ በአፍሪካ ደረጃ በቀዳሚነቱ የሚጠቀስ ፤ በአየር ላይ ውጊያ ገድሎች ባለ ብዙ ታሪክ ነው። ብቁ ባለሙያዎችንም በማፍራት አንቱታ ያተረፈም ነው።

ከሀገር ውስጥ ባለፈ በዓለም አቀፍ የሰላም ማስከበር ግዳጆች የተሰጠውን ተልእኮ በስኬት በመወጣት የሀገርና የሕዝብ ኩራት ነው፤ በዚህም ዓለም አቀፍ እውቅና ጭምር የተቸረው ነው። በበረራ እና ጥገና ማሠልጠኛ ተቋሙም ብዛት ላላቸው አፍሪካውያን ወንድሞቻችን አቅም ምንጭ በመሆን በማገልገል ላይ ያለ፤ በዚህም ለአፍሪካውያን ሳይቀር ኩራት የሆነ ተቋም ነው።

ይህን የትናንት ታሪኩን ወደ ላቀ ምዕራፍ ለማሻገር ባለፉት አምስት ዓመታት በተቋሙ ሁሉን አቀፍ ሪፎርም ሲደረግ ቆይቷል። በዚህም የተቋሙን ጊቢ ለሥራ አመቺ እንዲሆን ከማስዋብ ጀምሮ፤ ዘመኑ ያፈራቸውን ትጥቆችን እንዲታጠቅና ሙያዊ ብቃቶችን እንዲላበስ ተደርጓል።

በዚህም የሀገሪቱን የአየር ክልል በአስተማማኝ ደረጃ መጠበቅ የሚያስችለውን አቅም ተጎናጽፏል። በየትኛውም የግዳጅ ወረዳ የሚሰጠውን ወታደራዊ ተልዕኮ በስኬት የሚወጣበትን ቁመና መላበስም ችሏል።

የተቋሙ የሪፎርም ስኬት ከዚህም ባለፈ ለሀገሪቱ ወዳጆች ሆነ ጠላቶች አሁናዊ መልእክት ማስተላለፍ የሚችል አቅም ሆኗል። በተለይም ሀገሪቱ እንደ ሀገር የጀመረችውን ልማትና በልማቱ እያስመዘገበች ያለውን ተስፋ ሰጪ ውጤት ለማሰናከል ለሚሹ ኃይሎች መልዕክቱ ከፍ ያለ፤ በሀገሪቱ እና በሕዝቦቿ ላይ የሚያስቧቸውን የጥፋት ሃሳቦች ደጋግመው እንዲያጤኑ የሚያስገድዳቸውም ጭምር ነው!


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል :- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** :- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የኑሮን ውድነት በመፍትሄ ርምጃ…

መልካምሥራ አፈወርቅ

በየጊዜው እየናረ የሄደው የሸቀጦችና የመሠረታዊ ፍጆታዎች ዋጋ ከተጠቃሚው ህብረተሰብ አቅም ጋር የተመጣጠነ አለመሆኑን ብዙዎች ይመሰክራሉ፡ የግብዓት ምርቶች ማነስና የንግድ ሥርዓቱ ወጥ አለመሆን ከአንዳንድ የስግብግብ ነጋዴዎች ፍላጎት፣ ጋር ተዳምሮ በሀገሪቱ የኑሮ ውድነትን ካስከተለ ሰነባብቷል፡፡

ጠዋት ማታ በየሰዉ ልቦና ይመላለስ የያዘው የኑሮ ውድነት ዛሬም መፍትሄ ያገኘ አይመስልም። የየዕለቱ የሚዲያ ዘገባዎች፣ ይህንኑ መሠረታዊ ችግር እያነሱ ይወያዩበታል፡፡ ለኑሮ ውድነቱ ዋንኛ ሰለባ የሆነው ሰፊው የህብረተሰብ ክፍል ቤት ጓዳውን እያሰበ ስለኑሮው ያስባል፣ ይጨነቃል፡፡

ተደጋግሞ እንደሚነገረው የዋጋ ጭማሪ አጋጠመ ማለት የዋጋ ንረት ተፈጥሯል ማለት አይደለም። የኢኮኖሚ ባለሙያዎች እንደሚሉትም በአንድ ሀገር ላይ የሚስተዋል የዋጋ ጭማሪ የአንድ ጤናማ ኢኮኖሚ አይነተኛ መገለጫ ነው፡፡

እንዲህ አይነቱን እውነታ ባደጉ ሀገራት የሚገኙ ታላላቅ ባንኮች ዋንኛ የፖሊሲያቸው ግብ አድርገው ይወስዱታል፡፡ ይህ በልኬታ የተቀመጠ መስፈርት በአግባቡ የሚካሄድ እስከሆነ ድረስ ኢኮኖሚው ስብራት አይገጥመውም፡፡

ከዚህ በተቃራኒ ያለአግባብ የሚጓዝ የዋጋ ጭማሪ ግን የሀገርን ኢኮኖሚ ለመጉዳትና የህብረተሰቡን የመኖር አቅም ለመፈተን መንገዱ ፈጣን ነው፡፡ መረጃዎች እንደሚጠቁሙት፤ በሀገራችን ለኑሮ ውድነት እንደምክንያት ከሚጠቀሱት መሀል በአቅርቦትና ፍላጎት መሀል የሚያጋጥም ኢኮኖሚያዊ አለመጣጣም አንዱ ነው፡፡

ከምርት በኋላ የሚኖር ስርጭትና የገበያ ሥርዓት መዛባትም የኑሮ ውድነቱን ችግር ለማፋጠን ዋነኛ ሰበብ ይሆናል፡፡ ይህ አይነቱ አካሄድ አሁንም ድረስ ኢኮኖሚውን የፈተነ ምክንያት ሆኖ ይጠቀሳል፡፡

በአንድ ሀገር የተትረፈረፈ የምርት አቅርቦት አለ ቢባልም ስርጭቱ በወጉ ካልሆነ ኪሳራው የበዛ ነው፡፡ ይህ አይነቱ አሠራር በተለመደ ቁጥር የኑሮ ውድነቱን ሸክም የሚያከብዱ አጋጣሚዎች ይፈጠራሉ፡፡

ለኑሮ ውድነቱ ሌላው ተጠቃሽ ምክንያት ከውጭ ሀገራት የሚገቡ ምርቶች ጋር ተያይዞ የሚስተዋል የዋጋ መናር ነው፡፡ ሀገራችን በኢኮኖሚ ተወዳዳሪ ካለመሆኗ ጋር ተያይዞ የዓለም ገበያ ዋጋን ከመቀበል ውጭ ምርጫ የላትም፡፡ ይህ አይነቱ ገበያን የመወሰን አቅም ማጣትም የዓለምን ገበያ ዋጋ ከነጫናው ተቀብላ እንድትጓዝ ምክንያት ይሆናል፡፡

ይህ እውነታ አንደኛው ሰበብ ሆኖ ይጠቀስ እንጂ በሀገራችን የውጭ ሀገራትን ምርቶች የሚጠቀመው ሃይል ጥቂት የሚባለው ክፍል መሆኑ ይታወቃል። ይህ እንዳለ ሆኖ በአሁኑ ጊዜ ወቅትን ጠብቀው የሚገቡ የሀገር ውስጥ ምርቶች ዋጋ ማሻቀብ ጭምር ምክንያቱን አሳማኝ እንዳይሆን ያደርገዋል፡፡

ከገንዘብና የመንግሥት በጀት ፖሊሲ ጋር ተያይዞ የሚፈጠር የዋጋ ጭማሪም የኑሮ ውድነቱን ከሚያጎሉ ምክንያቶች መሀል አንዱ ሆኖ የሚጠቀስ ነው፡፡ የተጠቀሱ ችግሮች እንዳሉ ሆኖ በአንድ ሀገር ለኢኮኖሚው መሳሳት ምክንያት ናቸው የሚባሉ ጉዳዮች ተደራርበው በሚከሰቱ ጊዜ የኑሮ ውድነቱ ይበልጥ ያይላል፡፡

እንደ ኢኮኖሚ ባለሙያዎች ትንታኔ፤ የኢትዮጵያ የምግብ ንግድ ሁኔታ ምርት ሲኖር ዝቅ የሚል፣ ምርት ባነሰ ጊዜም ከፍ የሚል ሆኖ ቆይቷል። በአሁኑ ጊዜ ግን ይህ እውነታ ተቀይሮ ፍሰቱ በተቃራኒው እየተጓዘ ይገኛል ፡፡ ይህ እውነታም የኑሮ ውድነቱን የማያረግብ ከመሆኑ አኳያ ጉዳዩን አሳሳቢ አድርጎታል፡፡

ባላደጉ ሀገራት የኑሮ ውድነቱን ለማባባስ በርካታ ጉዳዮች ሊነሱ ይችላሉ ፡፡ ለወቅታዊው የሀገራችን ችግር ዋነኛው መንስዔ ግን ያለፍንበትና አሁንም የምንገኝበት የሰላም ማጣት ችግር ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛል፡፡ ሰላም ከሌለ ገበሬው ከእርሻው ፣ ምርት ከገበያው አይውልም፡፡ የተለመደው የንግድ ሥርዓት በአግባቡ አይጓዝም፡፡ ለከርሞ የታሰበው ለዘንድሮው ሳይበቃ፣ አውድማው ይራባል፣ ጎተራው ይራቆታል፡፡

በርካቶች እንደሚስማሙት ለኑሮ ውድነቱ ሌላው አይነተኛ ምክንያት የዋጋ ግሽበት አንዱ ሆኖ ይጠቀሳል፡፡ ግሽበቱን አስመልክቶ አንዳንዶች እንደሚሰጡት አስተያየትም ገንዘብን ያለእንቅስቃሴ ማስቀመጥ አንዱ ምክንያት ይሆናል፡፡ ያልተንቀሳቀሰ ገንዘብ ከጥቅሙ ይልቅ ጉዳቱ ያይላልና ኢኮኖሚውን አስሮ ለመያዝ ሰበብ ነው፡፡

ለኑሮ ውድነቱ መባባስ መንግሥት በየጊዜው የሚወስዳቸው የመፍትሄ ርምጃዎች መኖራቸው ይታወቃል፡፡ እንዲህ መሆኑ ብቻ ግን ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት አቅም ሊሆን አይችልም። በተለያዩ አጋጣሚዎች የሚከሰተውን ሰው ሰራሽ ክፍተት ለመሙላት አማራጮችን ማስፋት የግድ ይላል።

በየጊዜው ለሚያጋጥሙ የኢኮኖሚ ስብራቶች የግብርናውንና የኢንዱስትሪውን ዘርፍ ቅብብሎሽ ማቀላጠፍ አስፈላጊ ነው፡፡ የዘርፉ ባለሙያዎች እንደሚሉትም ከግብርናው ምርት የሚገኘውን ውጤት ለኢንዱስትሪው ግብዓት በመመገብ ኢኮኖሚው እንዲያንሰራራ ማድረግን በአማራጭነት መያዝ ያስፈልጋል፡፡

በመንግሥት አሠራር ላይ የሚታዩ ብልሹ አሠራሮች የዋጋ ንረቱን በማባባስ ከፍተኛውን ሚና ይጫወታሉ። ባላደጉ ሀገራት ውስጥ አብዝቶ የሚስተዋለው የሙሰኝነት ችግርም ኢኮኖሚውን እያቀጨጨ ተጠቃሚውን በግልጽ እየጎዳው ይገኛል፡ ፡

በተገቢው ጊዜ ተመርቶ በተመጣጣኝ ዋጋ ለገበያ መቅረብ የሚኖርበት ምርት በአንዳንድ ስግብግብ ነጋዴዎች፣ በተላላኪ ደላሎችና በጥቂት የመንግሥት ባለሥልጣናት ፈጻሚነት በታሰበው ልክ የማይጓዝበት አጋጣሚ ሰፊ ነው፡፡

እነዚህ አካላት የምርት እጥረት በማይኖርባቸው ጊዜያት ሁሉ አቅርቦቱን በማሰናከል የገበያ ሂደቱን የሚያደናቅፉ ናቸው፡፡ በኢትዮጵያ የግል ባለሀብቱን በሚያበረታታ የንግድ ሂደት ያለው መንገድ ከአምራች እስከ ገበያ የሚደርስ ሰንሰለታዊ ጉዞን የተከተለ ነው። ከችርቻሮ ፣ እስከ ጅምላና ሀገራዊ የንግድ ትስስር የሚኖረው ሂደትም ጤናማ መሆኑ እስካልተፈተሸ ለኑሮ ውድነቱ መነሻ የማይሆንበት ምክንያት አይኖርም፡፡

ይህ አይነቱ ስር የሰደደ ችግር ባለበት የህብረተሰቡን ፍላጎት ማሟላትና የታመመውን ኢኮኖሚ ማዳን አዳጋችና ፈታኝ ይሆናል፡፡ መንግሥት ገበያውን ለማረጋጋት እስከዛሬ የወሰዳቸው አማራጮች በጎ የሚባሉ ናቸው፡፡ ይህ እውነታ እንዳለ ሆኖም በተሻሉ አማራጮች ተጨማሪ መፍትሄዎችን መፍጠር ያስፈልጋል ፡፡

ሁሌም ቢሆን ምርቶችን በነፃነት በማንቀሳቀስ የገበያ ዝውውሩን ማስፋት ጠቀሜታው የጎላ ነው። በታላላቅ ከተሞች የሚስተዋለውን የኢኮኖሚ ድቀት ለማረጋጋትም አነስተኛ የንግድ ማዕከላትን በማስፋት ለተጠቃሚው መድረስ ተገቢ ይሆናል፡፡

ይህ አይነቱ ልማድ ዕውን መሆኑ ብቻውን ወደ መፍትሄው ላያደርስ ይችላል፡፡ ይሁን እንጂ ከዚሁ ጎን ለጎን ጥቃቅን የንግድ አማራጮችን በማስፋት ከታክስ ነጻ የሆነ አሠራርን መፍጠር ተገቢነቱ መልካም ነው፡፡ እንዲህ አይነቶቹን አዳዲስ አሠራሮች ማስተዋወቅ በተለይ መካከለኛ ኑሮ ላይ ለሚገኘው የህብረተሰብ ክፍል ጠቀሜታውን ያጎላዋል፡፡

በተማረው የሰው ሃይል ብርታት የግብርና ሂደቱን በማዘመን ኢኮኖሚውን ማከም ከተቻለ ችግሩን ለመቅረፍ አንድ ርምጃ መፍጠን ይሆናል፡፡ በከተማ ግብርናና ፣ በበጋ መስኖ ፕሮጀክት ምርቶችን በመደጋገም አርሶደሩን በዕውቀት የሚያግዝ ሃይል መፍጠርም አንዱ መፍትሄ ነው፡፡

ገበያ መር የሆነ ሥርዓትን በኢኮኖሚው መደገፍ ከተቻለ ፍላጎትና አቅርቦትን ማጣጣም የማይቻልበት አግባብ አይኖርም፡፡ ከአምራቹ፣ እስከ ሸማቹ ያለውን ትስስር ጤናማ በማድረግ ሀገራችን እየተፈተነችበት ያለውን ኢኮኖሚያዊ ህመም በወጉ ማከም ይቻላል፡፡ ይህን ዕውን ለማድረግ ግን ቅን ልቦና፣ ሀገር የመውደድ ስሜትና የእኔነት መንፈስን መላበስ ግድ ይላል፡፡ የኑሮ ውድነት የሁሉንም ወገን በርና ጓዳ አንኳኩቷልና፡፡

# በክልሉ ከ136 ሺህ በላይ አዳዲስ የቴክኒክና ሙያ ሠልጣኞችን ለመቀበል ዝግጅት ተደርጓል

ቃልኪዳን አሳዬ

አዲስ አበባ፡- በአማራ ክልል በተያዘው የትምህርት ዘመን ከ136ሺህ በላይ አዳዲስ የቴክኒክና ሙያ ሠልጣኞችን ለመቀበል ዝግጅት መደረጉን የክልሉ ሥራ እና ሥልጠና ቢሮ አስታወቀ፡፡

በቢሮው የተቋማት አቅም ግንባታ አግባብነትና የጥራት ማረጋገጥ ዳይሬክተር አቶ ሙላው ልመንህ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ በክልሉ በሚገኙ በ126 የመንግሥትና በ110 የግል የቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች በተያዘው የትምህርት ዘመን 136ሺህ 98 አዳዲስ ሠልጣኞችን ተቀብሎ ለማሠልጠን ዝግጅት ተደርጓል፡፡

እንዲሁም በመደበኛ ፕሮግራም 69ሺህ 200 ነባር ሠልጣኞች ተቀብሎ ለማሠልጠን የታቀደ ሲሆን እስካሁን ባለው ሂደት አንጻራዊ ሰላም ባለባቸው 17 ዞኖች 32 ሺህ 877 ነባር መደበኛ ሠልጣኞችን መመዝገብ የተቻለ ሲሆን ሰላም በሰፈነባቸው አከባቢዎች ቁጥሩ እየጨመረ መጥቷል ነው ያሉት፡፡

የኮሌጆቹ አጠቃላይ የዝግጅት ሁኔታ የተገመገመ ሲሆን የአሠልጣኝ፣ የቤተ ሙከራ፣ የመማሪያ ክፍሎችንና ሌሎች አስፈላጊ ግብዓቶችን ማሟላት በመቻሉ፤ የአዳዲስ ሠልጣኞች ምዝገባ አንጻራዊ ሰላም ባለባቸው አካባቢዎች መጀመሩን አቶ ሙላው ጠቁመዋል፡፡

ሠልጣኞች በወቅቱ ተመዝግበው ሥልጠናቸውን እንዲጀምሩ በየኮሌጆች ቅስቀሳዎች እየተካሄዱ ሲሆን በቀጣይ ቅስቀሳው ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ነው ያወሱት።

በክልሉ በተወሰኑ ስፍራዎች ላይ የፀጥታ ችግር በመኖሩ የሠልጣኞች ምዝገባ ያልተጀመረባቸው አከባቢዎች በመኖራቸው መንግሥት ከምንም በላይ ለሰላም ቅድሚያ በመስጠት ሰላምን እንዲያሰፍን አሳስበው፤ እንዲሁም የኢንተርኔት አገልግሎት ለሥልጠና አሰጣጥ ሂደቱ አስፈላጊ በመሆኑ መንግሥት ሊያስብበት ይገባል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ሙላው ገለጻ፤ የግልም ሆኑ የመንግሥት ኮሌጆች በሥራና ክህሎት ሚኒስቴር የተቀመጠውን የመቁረጫ ነጥብ ያላሟሉ ሠልጣኞችን መቀበል እንደሌለባቸውና የግል ተቋማት በክልሉ ያለውን ነባራዊ ሁኔታ በመጠቀም ሕገወጥ ተግባራትን ሊያከናውኑ ስለሚችሉ ሠልጣኞች ጥንቃቄ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል፡፡

ከዚህ ቀደም የተቀመጡ ቅድመ ሁኔታዎችን አሟልተው ያልተገኙ 15 የግል ቴክኒክና ሙያ ኮሌጆች መዘጋታቸውን አስታውሰው፤ አሁን ላይ ካላቸው ግብዓትና ዝግጁነት በላይ ማሠልጠን እንደሌለባቸውና ተላልፈው በሚገኙት ላይ በሚደረገው የቁጥጥርና የክትትል ሥርዓቶች እርምጃ እንደሚወሰድባቸው ተናግረዋል፡፡

የግል ኮሌጆችን የጥራትና አግባብነት የማረጋገጥ ሥራ በትኩረት እየተሠራበት ሲሆን ከግሉ ዘርፍ 13 አዲስ ኮሌጆችን የመክፈት ጥያቄ በመኖሩ መመሪያና ደንብን በመከተል ፍቃድ እንደሚሰጥ አመላክተዋል፡፡

በተለይም በግል ኮሌጆች የሚሰጡ ሥልጠናዎች ለትርፍ ማግኛ ብቻ ሳይሆን ተገቢውን እውቀት፣ ክህሎትና አመለካከት የጨበጠ ሠልጣኝ ማፍራትን መሠረት ባደረገ መልኩ መሆን እንዳለበት የገለጹት ዳይሬክተሩ፤ የግልም ሆኑ የመንግሥት ኮሌጆች ለሠልጣኞች ጥራት ያለው ሥልጠና ለመስጠት ትኩረት አድርጎ መሥራት እንደሚጠበቅባቸው አሳስበዋል፡፡

በተያዘው የትምህርት ዘመን በክልሉ የሚገኙ 24 ፖሊ ቴክኒክ ኮሌጆች በየአካባቢያቸው ያላቸውን ፀጋ በመለየት ያንን ሊደግፉ የሚችሉ የሥልጠና ዘርፎችን በመክፈት እንደሚያሠለጥኑና የተቀሩት ከዚህ ቀደም ሥልጠናዎችን በሚሰጡበት የሙያ አይነቶች እንደሚቀጥሉ ጠቁመዋል።

ከመደበኛ ሠልጣኞች በተጨማሪ በክህሎት ሥልጠና በሩብ ዓመቱ 39ሺህ 804 ሠልጣኞች በሥልጠና ሂደት ውስጥ አልፈው ወደሥራ እንዲገቡ ሙከራዎች ተደርገዋል ብለዋል፡፡

እንደ ዳይሬክተሩ ጥቆማ፤ ዜጎችን በኢንተርፕራይዞች ከማደራጀት አኳያ በከተማም በገጠርም 1ሺህ 561 ኢንተርፕራይዞችን በኢንዱስትሪ፣ በግብርና፣ በአገልግሎትና በሌሎች የሥራ መስኮች ማደራጀት ተችሏል እንዲሁም በሩብ ዓመቱ 29ሺህ 937 የሥራ እድሎች ተፈጥረዋል፡፡

# የጀጎል ቅርስን የማስዋብ ሥራ ተጀመረ

ማርቆስ በላይ

አዲስ አበባ፡-የሐረር ጀጎል ዓለም አቀፍ ቅርስን ለጎብኚዎችና ለነዋሪዎች ምቹ ለማድረግ ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ የመጀመሪያ ምዕራፍ ሥራ እየተሠራ መሆኑን የሐረሪ ክልል ባሕልና ቅርስ ቢሮ አስታወቀ፡፡

የሐረሪ ክልል ባሕልና ቅርስ ቢሮ የቅርስ ዳይሬክተር አቶ አሚን ረመዳን ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የጀጎል ዓለም አቀፍ ቅርስን ለጎብኚዎችና ለነዋሪዎች ምቹ ለማድረግ የተለያዩ ሥራዎች እየተሠሩ ነው፡፡

እንደ አቶ አሚን ገለጻ፤ ቅርሱን የማስዋብ የመጀመሪያ ምዕራፍ ሥራዎች ከ20 ሚሊዮን ብር በላይ ወጪ እየተሠራ ነው፡፡

የጀጎል ዓለም አቀፍ ቅርስ እንክብካቤና ልማት ሥራዎች በክልሉ በሚገኙ 19 የተለያዩ ተቋማት እየተከናወነ ነው ያሉት አቶ አሚን በቅርሱ ውስጥ የሚገኙ መንገዶችን ምቹ ማድረግ፣ የውበት፣ የጽዳትና የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች እየተሠሩ ነው ብለዋል፡፡

ቅርሱን ምቹና ሳቢ ማድረግ ከተቻለ የጎብኚዎችን ቁጥር ማሳደግ እንደሚቻል ጠቅሰው እንደሀገር ከዘርፉ የሚገኘውን ገቢ ለማሳደግ የሚረዳ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

በፕሮጀክቱ ባሕላዊ ቤቶች ጉዳት እንዳይደርስባቸው የሚያስችሉ ሥራዎች መከናወናቸውን በመግለጽ ይህም የነዋሪዎችን የኑሮ ደረጃ ከፍ ለማድረግ የሚያስችል መሆኑን ተናግረዋል፡፡

የጀጎል ዓለም አቀፍ ቅርስን ለጎብኚዎችና ለነዋሪው ምቹ ለማድረግ እየተከናወኑ የሚገኙ ሥራዎች ተጠናክሮ እንደሚቀጥሉ ጠቅሰው ቅርሱን ውብና ምቹ የማድረግ ሥራዎች በትኩረት እየተሠራ ይገኛል ብለዋል።




የጀጎል ዓለም አቀፍ ቅርስ የውስጥ ለውስጥ መንገዶች ልማት ፕሮግራም ሥራዎች እየተከናወኑ እንደሚገኝ በመግለጽ በቀጣይ የተለያዩ ምዕራፎች አካባቢውን ለጎብኚዎች ምቹ የማድረግ ሥራ እንደሚሠራ አመላክተዋል፡፡

በቅርሱ ዙሪያ እየተከናወኑ የሚገኙ የውበት፣ የጽዳትና የአረንጓዴ ልማት ሥራዎች ተጨባጭ ውጤት እያመጡ መሆናቸውንም ገልጸው የአካባቢው ማኅበረሰብ ቅርሶችን በመጠበቅ የበኩሉን ድርሻ መወጣት እንዳለበትም አሳስበዋል።

በመጨረሻም የሐረሪ የሸዋል ኢድ በዓለም ቅርስነት መመዝገቡን ጠቅሰው የክልሉን የጎብኚዎች ቁጥር ከፍ ለማድረግ ምቹ ሁኔታን የሚፈጥር መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

# ለኢትዮጵያ የባሕር በር ማግኘት የተረጋጋ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እየተንቀሳቀሱ መሆኑን የጠቀሱት ዶክተር ዓለማየሁ፤ ኢትዮጵያም ሌሎች ሀገራት ጥቅማቸውን ለማረጋገጥ በዚህ ደረጃ እየተንቀሳቀሱ በቅርብ ተቀምጣ በዝምታ ልታልፈው አትችልም ብለዋል።

ዶክተር ዓለማየሁ እንደገለጹት፤ በአሁኑ ወቅት የባሕር በር የሌላቸው ሀገራት የጀመሩት በጥምረት የመሥራት እንቅስቃሴ አለ። የባሕር በር የማግኘት ጉዳይ የመንግሥት ብቸኛ ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ አይደለም። በመሆኑም ሌሎች የባሕር በር የሌለቸው ሀገራት የኢትዮጵያን ጥያቄ በማሰማቱ ረገድ ትልቅ ሚና መጫወት ይችላሉ። በተጨማሪም ከጦርነት ውጪ ያሉ አማራጭ መንገዶችን ሊያመላክቱ ይችላሉ። እንዲሁም የሥራ አጥ ቁጥር መብዛት አጠቃላይ የሕዝብ ብዛት መጨመር በተመለከተ እየተፈጠረ ያለውን ችግር አሳሳቢነትም ለጎረቤት ሀገራትም ሆነ ለሌሎች ኢትዮጵያን ለሚደግፉ ለማሳወቅም ይጠቅማል።

የባሕር በር ጉዳይ ለኢትዮጵያ የኢኮኖሚ ወይንም የተረጋጋ የፖለቲካ ምሕዳር መኖር አለመኖር ብቻ ሳይሆን ታሪካዊ ማንነትን ከማጣት ጋርም የሚያያዝ ነው ያሉት ዶክተር ዓለማየሁ፤ አካባቢው የሀገሪቱ ሥልጣኔ የነበረበት ቦታ እንደመሆኑ ከኢኮኖሚና ፖለቲካዊ ፋይዳው ባለፈ የታሪካዊ ማንነት ጥያቄን የሚመልስ ነው።

የኢትዮጵያ ባሕር በር ጉዳይ ከመሠረቱ ሲታይ ኢትዮጵያ በአፍሪካ የራሳቸው ሥልጣኔ ከነበራቸው ሀገራት መካከል ነበረች። ከተለያዩ የዓለም ሀገራት ጋር ግንኙነት ስታደርግና በምሥራቅ አፍሪካ ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጣሪ የነበረችም ሀገር ናት። አውሮፓ፣ እስያ፣ ላቲን አሜሪካ ሀገራትም ከኢትዮጵያ ጋር ጠንካራ ግንኙነት ነበራቸው።

“እስከ ቅርብ ግዜ የባሕር በር ጥያቄ ማንሳት እንደ ወንጀል ይታይ ነበር፣ አሁን ይሄ ተቀይሯል። በአንጻሩ በርካታ ሰዎች ኢትዮጵያውያንን ጨምሮ የባሕር በር ጉዳይ በጦርነት ብቻ የሚፈታ አድርገው ይመለከቱታል። ይህ ግን ስህተት ነው። ሌሎች አማራጮችንም ማማተር ይቻላል። ይህም ሆኖ ሁሉም አካላት በዚህ ረገድ መንግሥትንም ሆነ በጋራ ለመሥራት የተሰባሰቡትንና በዲፕሎማሲ ረገድ እየተሠራ ያለውን ሥራ ሊደግፉ ይገባል” ሲሉ መልእክታቸውን አስተላልፈዋል።

# ብሔራዊ ዲጂታል...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እንደ አቶ በላይሁን ገለፃ፤ የፋይዳ ቁጥር የዲጂታል መታወቂያ ሲሆን ቴክኖሎጂን በመጠቀም የነዋሪዎችን የተመጠነ የባዮሜትሪክ እና ዲሞግራፊክ መረጃ በመሰብሰብ “አንድ ሰው አንድ ነው” በሚል መርሕ አንድን ሰው ልዩ በሆነ ሁኔታ መለየት የሚያስችል ሥርዓት ነው።

የፋይዳ ቁጥር በብሔራዊ መታወቂያ ፕሮግራም የተቀመጠውን ቅድመ ሁኔታ ለሚያሟሉ ነዋሪዎች የሚሰጥ ባለ 12 አኃዝ ልዩ መለያ ቁጥር ነው ያሉት አቶ በላይሁን፤ የፋይዳ ቁጥር (ዲጂታል መታወቂያ) የያዙ ነዋሪዎች በሀገሪቱ ውስጥ ማንነትን በማረጋገጥ የሚሰጡ አገልግሎቶችን ለማግኘት ያስችላል ብለዋል፡፡

ከዚህም ባለፈ የባንክ ሒሳብ ለመክፈት፣ ሥራ ለማመልከት እና የተለያዩ አገልግሎቶችን ለማግኘት እንዲሁም ለተለያዩ ዓላማዎች ለመጠቀም የማንነት መሠረታዊ ማስረጃ ሆኖ ያገለግላል። የሚቀርበውም መረጃ ትክክለኛ መሆኑን በማረጋገጥ ከመጭበርበር እና ተመሳሳይ ድርጊቶች ለመከላከል ይረዳል ብለዋል፡፡

የብሔራዊ መታወቂያ ፕሮጀክት ዋና ሥራ አስኪያጅ አቶ ዮዳሄ አርዓያሥላሴ በበኩላቸው፤ መርሐ ግብሩ በ2014 ዓመተ ምሕረት ምዝገባ መጀመሩን ጠቁመው፤ እስካሁንም በተለያዩ አካባቢዎች ከ125 ሺህ በላይ ለሚሆኑ ሰዎች የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ መስጠት ተችሏል ብለዋል።

በ2015 ዓ.ም ማብቂያ ከትምህርት ሚኒስቴርና ከሌሎች ድርጅቶች ጋር በጥምረት በተሠሩ ሥራዎች ወደ ሦስት ሚሊዮን የሚጠጉ ዜጎችን የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ ባለቤት ማድረግ እንደተቻለ ገልጸዋል።

እንደ አቶ ዮዳሄ ገለፃ፤ የዲጂታል መታወቂያን ኅብረተሰቡ በተለያዩ አካባቢዎች እንዲያገኝ የማመቻቸት ሥራ እየተሠራ ነው። በ2018 ዓ.ም ማብቂያ ከ90 ሚሊዮን በላይ ዜጎች የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያ እንዲኖራቸው ይደረጋል። በዘንድሮ ዓመትም ለ25 ሚሊዮን ዜጎች ዲጂታል መታወቂያ ለመስጠት ተማሪዎችንና የባንክ ደንበኞች ላይ ትኩረት ተደርጎ ይሠራል።

ለዚህም ከትምህርት ሚኒስቴር፣ ከፋይናንስ ዘርፉ፣ ከገቢዎች ሚኒስቴርና ከሌሎች ተቋማት ጋር በመተባበር እንሠራለን ያሉት አቶ ዮዳሄ፤ ትግበራው የአሠራር ሥርዓትን ለማዘመን ያለመ ነው ብለዋል። የብሔራዊ ዲጂታል መታወቂያው ኅብረተሰቡ በአገልግሎት ሰጪ ተቋማት ተገቢውን አገልግሎት እንዲያገኝ ጉልህ እገዛ እንደሚያደርግም ተናግረዋል፡፡

እንደ ባንክ፣ ጤና፣ ኢንሹራንስ እና የመሳሰሉ ሌሎች አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ለኅብረተሰቡ የተፋጠነ እና ዘመናዊ ሥራ እንዲሰጡ ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥርም አቶ ዮዳሄ ገልጸዋል።

አቶ በላይሁን በበኩላቸው፤ ብሔራዊ መታወቂያ ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ሲደረግ ዓመታዊ የኢትዮጵያ ጂዲፒ እስከ ሰባት በመቶ እንደሚያድግ ገልጸዋል።

# ከ6 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

በድርቅ፣ በሰው ሠራሽ አደጋዎችና በግጭት ምክንያት ለተፈናቀሉ ከ6 ነጥብ 5 ሚሊዮን በላይ ለሚሆኑ ዜጎች ከ867 ሺህ ኩንታል በላይ የምግብና በጥሬ ገንዘብ ለመለገስ ቅድመ ዝግጅት ተደርጓል፡፡

በታኅሣሥ ወር ርዳታ ለሚፈልጉ ዜጎች ርዳታ ለማንቀሳቀስ ተሽከርካሪዎች እንቅስቃሴ እንደሚጀምሩ ጠቁመው፣ ይህም በገንዘብ ሲሰላ ከ8 ነጥብ 6 ቢሊዮን ብር በላይ ይሆናል ብለዋል፡፡

እንደ ባለሙያው ገለጻ፤ ከ560 ሚሊዮን ብር በላይ በጥሬ ገንዘብ ይሰራጫል፡፡ ይህም ዜጎች በአካባቢያቸው ካለ ገበያ ገዝተው ምግብ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ሦስተኛው ዙር ርዳታ በድርቅ አደጋ የተጠቁትን የሰሜን ኢትዮጵያ አካባቢዎች የሰብዓዊ ርዳታው ልዩ ትኩረት የሚሰጣቸው ሲሆን የሚሰጠው በአንድ ጊዜ ለ6 ነጥብ 5 ሚሊዮን ዜጎች ሲሆን፤ የብሩ መጠንም ከዚህ በፊት በሁለት ዙር ከተሰጠው በላይ እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን ለሦስተኛ ዙር በቅርቡ ወደ ርዳታ የተመለሱትን አጋር አካላት ጭምር በማስተባበር በሀገር አቀፍ ደረጃ የቅድሚያ ቅድሚያ ድጋፍና ትኩረት ለሚፈልጉ ዜጎች ድጋፍ ያደርጋል፡፡ በአስቸኳይ ርዳታ ለሚያስፈልጋቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች ርዳታ ለመለገስ አስፈላጊውን ዝግጅት መጠናቀቁንም አቶ አታለለ ገልጸዋል፡፡

በአጋር አካላት ይደረግ የነበረው ርዳታ በጊዜያዊነት መቋረጡን ተከትሎ መንግሥት በርዳታ ፈላጊዎች ላይ የሚደርሰውን የማኅበራዊና ኢኮኖሚዊና ጫና ለመቅረፍ ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ በተሰጠው አፋጣን ምላሽም በሁለት ተከታታ ዙሮች 7 ነጥብ 9 ቢሊየን ብር የሚያወጣ የአይነትና የገንዘብ ድጋፍ ለ7 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዜጎች ማድረሱ ይታወሳል፡፡

ኢኮኖሚ

# ግብርና

# የአርሶ አደሮች ቀን - ጠንካሮችን ለማበረታታት

**ወርቅነሽ ደምሰው**

ከኢትዮጵያ ሕዝብ 85 በመቶ ያህሉ አርሶ አደር መሆኑ ይነገራል፡፡ ይህ አርሶ አደር የሀገሪቷ ኢኮኖሚ የጀርባ አጥንት በሆነው የግብርና ሥራ ይተዳደራል። መንግሥት የዚህን አርሶ አደር አመራረትና ሕይወት እየሠራ ይገኛል፡፡ አርሶ አደሩን ከእጅ ወደአፍ የማምረት ሂደት በማውጣት ትርፍ አምራች ለማድረግ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል፡፡

የግብርናው ዘርፍ እንዲዘምንና ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር በዘርፉ የተለያዩ ድጋፎችን ያደርጋል፡፡ ግብዓት በማቅረብ፣ ሜካናይዜሽን እንዲስፋፋ፣ የኩታ ገጠም እርሻ እንዲስፋፋ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማትን እውን በማድረግ አርሶ አደሩ በዓመት አንዴ ከሚያመርትበት ሂደት ሁለትና ሶስቴ ማምረት የሚችልበትን እድል እየፈጠረ ይገኛል፡፡

ይህን ሁሉ ተከትሎም የግብርና ሥራ እየተሻሻለና ምርትና ምርታማነት እየጨመረ መጥቷል፡፡ በዚህም የበጋ መስኖ ስንዴ ልማትን በማስፋፋት ስንዴ ከውጪ የሚመጣበትን ሁኔታ ማስቀረት ተችሏል፡፡ በሩዝ ልማትም እንዲሁ እየታየ ያለውን ለውጥ ተከትሎ ሩዝን በሀገር ውስጥ ምርት ለመተካት እየተሠራ ነው፡፡

ይሁንና የምርት እድገቱ ሀገሪቷ ካላት ዕምቅ አቅምና ጋር ሲነጻጸር የምርትና ምርትማነት እድገት አሁን ብዙ ይቀረዋል፡፡ ሀገሪቷ ከዘርፉ ከምትጠብቀው ምርትና ምርታማነት አንጻር ሲታይም ውጤቱ ብዙም የሚያኩራራ አይደለም፡፡ መንግሥት የግብርናው ዘርፍ እንዲያድግና እንዲዘምን ብሎም ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር በየዓመቱ የተለያዩ ድጋፎችን የሚያደርገውም ለዚሁ ነው፡፡

የአርሶ አደሩን ሕይወት ለመቀየር፣ ግብርናው እንዲዘምንና ምርትና ምርታማነትን ይበልጥ ለማሳደግ አርሶ አደሩ ይበልጥ ተበረታቶ የሚሠራበትን ሁኔታ መፍጠርም ይገባል፡፡ አርሶ አደሩ ምርትና ምርታማነትን እያሳደገ ለመጣበት ሁኔታ እውቅና የሚሰጡና የሚያበረታቱ ሥራዎች እምብዛም አይስተዋሉም፡፡

በኢኮኖሚ የበለጸጉ እንደ አሜሪካ፣ ህንድ እና ቻይና ያሉ ሀገራት ተሞክሮን ስንመለከት አርሶ አደሩን የሚያበረታቱና ቅድሚያ እንዲያገኝ የሚያስችሉ ሁኔታዎች ስለመኖራቸው መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ለዚህም በየዓመቱ የተለያዩ ስያሜዎችን በመስጠት አርሶ አደሩ ዕውቅና የሚያገኝበትና የሚበረታታበት የአርሶ አደሮች ቀን ይሰየማል፡፡

በኢትዮጵያም በተመሳሳይ ምርትና ምርታማነትን ያሳደጉ፣ ኑሯቸውን ያሻሻሉ እና ለሌሎች አርሶ አደሮች አርአያ መሆን የቻሉ አርሶ አደሮችን በማበረታታት በሌሎች ዘንድ ተነሳሽነት መፍጠር የሚያስችል የእውቅና መርሀ ግብር ሲካሄድ እንደነበር ይታወሳል፡፡ ይህ የእውቅና መርሀ ግብር በ 1988 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በባሕርዳር ከተማ ተካሂዷል፡፡ የእውቅና ሥነ ሥርዓቱ እስከ 2006 ዓ.ም ድረስ ሳይቆራረጥ ለዘጠኝ ተከታታይ ዓመታት ሲካሄድ ቆይቶ ተቋርጧል፡፡

ከሰሞኑም ለአርሶ አደሩ እውቅና መስጠት ላይ የመከረ መድረክ በግብርና ሚኒስቴር፣ በቀድሞ የሀሮማያ ኮሌጅ ተመራቂ ተማሪዎች ማህበር እና በአሊያንስ ፎር ሳይንስ የተሰኘ ግብረ ሰናይ ድርጅት አባላት አማካኝነት ተካሂዷል፡፡ የአርሶ አደሩ ተወካዮች፣ ተመራማሪዎች፣ ከፍተኛ የግብርና ባለሙያዎች እና የሚመለከታቸው አካላት በመድረኩ ተሳትፈዋል፡፡

የግብርና ሚኒስቴር የእርሻና የሆልቲካልቸር ኤክስቴንሽን ዘርፍ መሪ ሥራ አስፈጻሚ ወይዘሮ የኔነሽ ኤጉ እንዳሉት፤ መድረኩ የተቋረጠውን የአርሶ አደር ቀን በዓል ለማስቀጠል ያለመ ነው፡፡ ቀኑ ጠንካራ አርሶ አደሮች የሚሸለሙበት እና ወደኋላ የቀሩ አርሶ አደሮች ደግሞ የሚበረታቱበት፣ አርሶ አደሩን የተመለከቱ መልዕክቶች የሚተላለፉበት፣ መሪዎችና ፖሊሲ አውጪዎች ከአርሶ አደሮች ጋር የሚመከሩበት ነው። እንደዚህ አይነት መድረኮች ቀጣይነት እና ወጥነት ባለው መልኩ መካሄድ ባለመቻሉ በቀጣይ የአርሶ አደሮች ቀን እንዲኖር ለማድረግ ያስችላል፡፡

‹‹የአርሶ አደሮች ቀን አርሶ አደሩን የምናበረታታበትና የምንሸልመበት፣ ጠንካሮችን በደንብ አጠናክረን ወደ ኢንቨስትመንት የምናስገባበት እና ሌሎች ወደኋላ የቀሩ አርሶ አደሮችን የምናበረታታበት ነው›› ያሉት ወይዘሮ የኔነሽ፣ ከዚሁ ጎን ለጎን ኤግዚቢሽኖች እና የተለያዩ ፕሮግራሞች የሚካሄድበት መሆኑንም አብራርተዋል። መድረኩም በጋራ ለመወሰን የሚያስችል እንደሆነም አመላክተዋል፡፡

የኢኮኖሚው የጀርባ አጥንት የሆነውን የግብርና ዘርፍ ዋና ተዋናይ አርሶ አደር ማበረታታት ትልቅ ፋይዳ አለው ያሉት ወይዘሮ የኔነሽ፤ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ ትልቁ ባለድርሻ አርሶ አደሩ እንደሆነ ተናግረዋል፡፡ አርሶ አደሩን ማበረታታት እውቅና መስጠት በተለይ ውጤታማ የሆኑትን መሸለም ወደ ኋላ የቀሩትን ለማነቃቃት ጠቃሚ እንደሆነም አመላክተዋል፡፡

የግብርናው ዘርፍ ችግሮች ምላሽ የሚያገኙበት አንድ መድረክ እንደሚሆንም ወይዘሮ የኔነሽ፤ አመላክተዋል። ድርቅ፣ በሽታ እና በመሳሰሉት በርካታ ጉዳዮች ዙሪያ ለሚነሱት ችግሮች የፖሊሲ፣ የስትራቴጂ እና በተለያየ መልኩ ምላሽ የሚሰጥበት እንዲሁም አርሶ አደሩ የቴክኖሎጂ እና የገበያ ተጠቃሚ እንዲሆን ለማድረግ የበኩሉን ሚና ሊጫወት እንደሚችልም ጠቁመዋል፡፡

የግብርና ሚኒስትር ዴኤታ ዶክተር መለስ መኮንን እንዳሉት፤ አርሶ አደሩን የማመስገን ጉዳይ ዘላቂነት ባለው መልኩ መፈጸም ይኖርበታል፡፡ በዚህም ሂደት የመጀመሪያው ተግባር ቀኑ የሚከበርበትን ሁኔታ ለመወሰን የሚያስችል አንድ ግብረ ኃይል መቋቋም አለበት፡፡ ይህ ግብረ ኃይል አርሶ አደሩን ለማመስገን የሚያስችሉ ቀደም ሲል የተሠሩ ሥራዎችንና ሌሎች ተሞክሮዎችን በደንብ ተንተኖ ለውሳኔ ሊሆን የሚችሉ ሃሳቦች አዘጋጅቶ ማቅረብ ይጠበቅበታል፡፡

የቀድሞው የአርሶ አደሮች ቀን ብዙ መልካም ጎኖች እንደነበሩት ያስታወሱት ሚኒስቴር ዴኤታው፣ ይህን ቀን እንደገና መመልከትና ወቅቱ ከሚፈልገው አኳያ መቃኘት እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል፡፡ አንዳንድ መስተካከል እና መቅረት ያለባቸው ነገሮች እንዳሉም ጠቅሰው፣ በአርሶ አደሮች ቀን አርሶ አደሮች ተለውጠዋል፣ ባለሀብት ሆነዋል ተብለው የሚመረጡባቸው መንገዶች አንዳንድ ችግሮች እንደነበሩባቸው አስታውሰዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት ሕይወታቸው ያልተለወጠ አርሶ አደሮች ጭምር ባለሀብት /ሚሊየነር/ ሆነዋል ተብለው ይቀርቡ እንደነበር ነው፡፡ በእውነቱ የተለወጡ እንዳሉ ሆነው እንደዚህ አይነት ስህተቶች እንዳይደገሙ ማድረግ እንደሚገባም አመላክተዋል፡፡ አሁን መሆን አለበት? የሚለው በጥልቀት ታይቶ ውሳኔ ለሚሰጡ አካላት መቅረብ እንዳለበትም አስገንዝበዋል፡፡ ‹‹የአርሶ አደሮች ቀን ብለን ስናከብር ሌላ አዲስ ነገር የምንጀምርበት ሳይሆን፣ የቀደሙ ጥሩ ተሞክሮዎችን በመቀመር፣ የማይጠቅሙትን በመተው፣ ቀኑ እንዲከበር የሚደረግበት ነው›› ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ይህንን ሥራ በባለቤትነት የሚመራው የግብርና ሚኒስቴር ነው፡፡ ያሉት ሚኒስትሩ ለአርሶ አደሩ የሚሠራ ስለሆነ አርሶ አደሩን የሚጠቅም የትኛውንም ተግባር ያከናውናል፡፡ ይህ ሲባል ደግሞ የግብርና ሚኒስቴር ብቻውን ይሠራል ማለት አይደለም፤ የመስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴር፣ የንግድ ሚኒስቴር፣ ኢንዱስትሪ ሚኒስቴር እና ሌሎች የግብርና ቤተሰብ የሆኑ ተቋማትም ጉዳዩ ይመለከታቸዋል፡፡ ግብረ ኃይሉ የአርሶ አደሮች ቀን በምን መልኩ መከበርና እንዴት መከበር እንዳለበት ሁሉንም ሠርቶ የሚያቀርብ ይሆናል፡፡ የግብርና ሚኒስቴርም ይህን ጉዳይ ሰፋ አድርጎ በመመልከት ቀጣይነት ያለው ተግባር ያከናውናል፡፡

በመድረኩ ላይ ቀኑ እንዲከበር በማድረግ በኩል ግብርና ሚኒስቴር የሚያከናውነው ተግባር እንዳለ ሆኖ፣ የአርሶ አደሮች ማህበር የማቋቋም አስፈላጊነትም

**የአርሶ አደሮች ቀን ሲከበር አርሶ አደሩ ችግሮቹን አውጥቶ የሚናገርባቸው የውይይት መድረኮችም ጎን ለጎን መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፤ በዚህም ከአርሶ አደሩ ጋር መመካከር ያስፈልጋል። አርሶ አደሩን መደገፍና በሁሉም መስክ ተሰማርቶ ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል ያስፈልጋል**

ተጠቁሟል፡፡ ሚኒስትር ዴኤታው የተነሳው ሃሳብ ትክክል መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ለዚህም ጥናት ማድረግ እንደሚገባ አመልክተው፣ የአርሶ አደሮች ማህበር ወደፊት የአርሶ አደሮች ቀን በዓል አንዱ ባለቤት እንደሚሆን ገልጸዋል፡፡

ሚኒስትር ዴኤታው እንዳሉት፤ የአርሶ አደሮች ቀን ከአርሶ አደር የሥራ ባህሪ ጋር የሚሄድ መሆን አለበት፡፡ የአርሶ አደሩ የሥራ ባህሪ አንድ ቀን ላይ ብቻ እንዲተኮር አያደርግም፡፡ እንዲከበር የሚፈለገው የአርሶ አደሮች በዓል ስለሆነ ከመሬት ባለቤትነት ባሻገር ብዙ ነገሮች ሊነሱበት ይችላሉ፤ ቀኑ መቼ መከበር አለበት የሚለው በደንብ መታየት ይኖርበታል፡፡ በዓሉ ለአንድ ቀን ብቻ ሳይሆን ለአንድ ወር የሚከበርበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል፤ ሌሎች አማራጮችም በጥልቀት መታየት አለባቸው፡፡

አርሶ አደሩ ቀኑን ሲያከብር ምርቶቹን የሚያቀርብበትና ብዙ ጥያቄዎቹ ምላሽ እንዲያገኙ የሚሠራበት እንዲሆን ተደርጎ መታየት እንዳለበትም ጠቁመዋል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዝርዝር ሥራዎችን በማካተት ግብረ ኃይሉ ከግብርና ሚኒስቴር ጋር እንደሚሠራም ገልጸዋል፡፡

እንደ ሚኒስትር ዴኤታው ማብራሪያ፤ የአርሶ አደሩን ቀን ለማክበር የተመረጠው ግብረ ሃይሉ በጥናት ላይ ተመሥርቶ መሥራት ይኖርበታል፤ ሥራውን በደንብ ተንትኖ የሚያቀርብ ይሆናል፡፡ በሥራው ሂደት ሌሎች ግብዓቶች ካስፈለጉም ተጨማሪ መድረኮችን ማዘጋጀት ይቻላል፤ በዚህም የሚያቀርበውን ሃሳብ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመገናኘት የበለጠ እንዲበለጽግ ማድረግ ይችላል፡፡ ግብረ ሃይሉ በተሰጠው አጭር ጊዜ በዚህ መድረክ ላይ የተነሱትን ሃሳቦች በደንብ በመተንተን የቤት ሥራውን አጠናቅቆ ለውሳኔ ያቀርባል፡፡

የአርሶ አደሮችን ቀን ለማክበር የሚከናወነው የሥራ ሃላፊነት ከፍተኛ መሆኑን የጠቀሱት ሚኒስትር ዴኤታው፤ የቀድሞው የአርሶ አደሮች ቀን ያኖረውን ዐሻራ በመውሰድ፣ መካተት ያለባቸውን በማካተት ቀኑ እንደገና መከበር እንዲጀምር የማድረጉ ሥራ ብዙ ጥረት ማድረግን እንደሚጠይቅም አመልክተዋል፡፡ በደንብ የተደራጀና ዘላቂነት ባለው መልኩ የሚከበር የአርሶ አደር በዓል እንዲኖር ለማድረግ በሚኒስቴሩ በኩል በትኩረት እየተሠራ መሆኑንም ሚኒስትር ዴኤታው ተናግረዋል፤ ቀኑ እንዲከበር የመነሻ ሃሳብ ያነሱትን የቀድሞ የሀሮማያ ኮሌጅ ተመራቂ ተማሪዎች ማህበር አባላትን እና አሊያንስ ፎር ሳይንስ የተሰኘውን ግብረሰናይ ድርጅትም አመስግነዋል፡፡

በመድረኩ ላይ ከተገኙ አርሶ አደሮች ወጣት አርሶ አደር ትዕግስት ከበደ አንዷ ናት፡፡ ‹‹የገበሬ ልጅ ነኝ፤ እኔም ገበሬ ነኝ›› ያለችው አርሶ አደር ትዕግስት፣ ቀደም ሲል ገበሬ የሚለው ቃል ለስድብ የሚውል ነበር፡፡ አሁን ግን ገበሬ ሲባል ሀብታም እንደሆነ ይታሰባል። ገበሬው ገበሬ መሆኑን ሲናገር በራሱ ኩራትን ያጭራል›› ትላለች፡፡

አርሶ አደር ትዕግስት አሁን ድረስ አብዛኛው የግብርና ሥራ ከባህላዊ አስተራረስና አመራረት አለመላቀቁን ጠቅሳ፤ አብዛኛው ገበሬ በበሬ የሚያርስ በመሆኑ የአርሶ አደሩን ሕይወት የሚያሻሽል የተሻለ አሠራር ሊኖር የግድ መሆኑን ጠቁማለች፡፡ የአርሶ አደሩን ቀን ለማክበር ስንነሳ ይህ ከግንዛቤ ውስጥ መግባት አለበት ብላለች፡፡

አርሶ አደሩን መሸለም ብቻውን በቂ እንዳልሆነም ጠቅሳ፣ የአርሶ አደሩን ችግሮች ከመሰረቱ ሊፈቱ የሚችሉ ነገሮችን አብሮ ማሰብን ይጠይቃል ብላለች። አርሶ አደሩ ለፍቶ ያመረተውን ለሸማቹ በአግባቡ የሚያቀርብበት የገበያ ትስስር መፈጠር ያለበት መሆኑን አብነት በመጥቀስ አንስታለች፡፡ አሁን ላይ ባለው አሠራር አርሶ አደሩ ምርቶቹን በቀጥታ ለህብረተሰቡ የሚያቀርብበት ሁኔታ አለመኖሩን ጠቅሳ፤ ይህ በመሆኑም ተጠቃሚዎቹ በመሀል ያሉ ደላሎች መሆናቸውን አመላክታለች፡፡

እሷ እንዳለችው፤ የአርሶ አደሮች ቀን ሲከበር አርሶ አደሩ ችግሮቹን አውጥቶ የሚናገርባቸው የውይይት መድረኮችም ጎን ለጎን መዘጋጀት ይኖርባቸዋል፤ በዚህም ከአርሶ አደሩ ጋር መመካከር ያስፈልጋል፡ አርሶ አደሩን መደገፍና በሁሉም መስክ ተሰማርቶ ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል ያስፈልጋል፡፡

ሌላው በመድረኩ የተገኙት አርሶ አደር አቶ ተስፋዬ በዳዳ ናቸው፡፡ እሳቸው እንዳሉት፤ አርሶ አደሩ አሁን የሚያመርተው ጤፍና ስንዴ ብቻ አይደለም፤ የግብርና ሥራው እጅግ ሰፍቷል፡፡ አርሶ አደሩ በሁሉም የግብርና ሥራዎች ላይ እንዲሠማራ ለማስቻል እውቅና መስጠትና ማበረታት ይገባል። በዚህም ጠንክሮ የሠራው አርሶ አደር ሲበረታታ፣ ወደኋላ የቀረው ይነቃቃል ነው ያሉት፡፡

የአርሶ አደሩ ሕይወት የሆነው የግብርና ሥራ ሊደገፍና ሊበረታታ የሚገባው ጉዳይ እንደሆነ ያነሱት አቶ ተስፋዬ፤ ለእዚህም የአርሶ አደሮች ቀን መከበር አንዱ እንደሆነ ነው የተናገሩት፡፡ ቴክኖሎጂ እየተስፋፋ ባለበት በዚህ ጊዜ ግብርናውን በማዘመን አርሶ አደሩን የቴክኖሎጂ ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችሉ ሥራዎችን መሥራት ይጠይቃልም ብለዋል። ግብርናውን የሚያሻሽሉ ቴክኖሎጂዎችን ለአርሶ አደሩ ማቅረብ ላይ በተጠናከረ መልኩ መሠራት እንደሚገባ ገልጸው፤ የግብርና ሚኒስቴርም ሆነ በዘርፉ የሚሠሩ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ለአርሶ አደሩ በአጠቃላይ ለግብርናው ዘርፍ የሚያደርጉት ድጋፍ ይበልጥ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አመላክተዋል።

መድረኩ የአርሶ አደሮችን ቀን ለማክበር የቅድመ ሁኔታ ሥራዎችን የሚሠራ ከግብርና ሚኒስቴርና ከሚመለከታቸው አካላት የተውጣጡ ሰባት አባላት ያሉት ኮሚቴ አዋቅሮ ተልዕኮ በመስጠት ተጠናቅቋል።

ማህበራዊ

# አስኳላ

# የትምህርት ስብራቱን ለመጠገን የመምህራን ሚና

**ቤዛ እሸቱ**

መምህርት ጽጌ ገብሩ (ለዚህ ፅሁፍ ሥሟ የተቀየረ) ላለፉት አስር ዓመታት በመምህርነት አገልግላለች። መምህርነት የምትወደው ሙያዋ ነው፡፡ የመጀመሪያ ዲግሪዋን ከደብረማርቆስ ዩኒቨርሲቲ በእንግሊዝኛ ቋንቋና ሥነ-ጽሑፍ አግኝታለች፡፡ ቋሚ መኖሪያዋን አዲስ አበባ ከማድረጓ በፊት በኢትዮጵያ የተለያዩ ገጠር አካባቢዎች ተዘዋውራ የማስተማር እድል ገጥሟታል፡፡

ዩኒቨርሲቲ ካገኘችው እውቀት በተጨማሪ የማስተማር ሥራ ላይ እያለች ከምታስተምርበት ቋንቋ ጋር የተያያዙ ክበባትን መሠረት ያደረጉ ሥልጠናዎች ወስዳለች፡፡

የመጀመሪያ ዲግሪዋን ወደ ሁለተኛ ዲግሪ ማሳደግ የምትችልበት እድል የነበረ ቢሆንም፤ ራሷን አሻሽላ በመምህርነት ሙያ የምታገኘው የደሞዝ ጭማሪ በቂ ነው ብላ አላሰበችም፡፡ ለዛም ነው የመምህርነትን ሙያዋን በሌላ ትምህርት መስክ ለመቀየር በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የሁለተኛ ዲግሪ ትምህርቷን እየተከታተለች ያለችው፡፡ ማስተማር በሷም ሆነ በባልደረቦቿ ዘንድ የሚወደድ ሙያ ቢሆንም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን በዚህ ሙያ ኑሮን መግፋት እየከበደ እንደመጣ ትናገራለች። የመምህርነት ደመወዟ ከዘጠኝ ሺ ትንሽ ፈቀቅ ያለ ቢሆንም ለቤት ኪራይ ብቻ አስር ሺ ብር ወጪ እንደምታደርግ ትገልፃለች፡፡

እንደመምህርቷ ገለፃ፣ መምህራን በደመወዛቸው ብቻ ወር ከወር መድረስ ስለማይችሉ ተጨማሪ ሥራዎችን ይሠራሉ፡፡ አብዛኞዎቹ የሥራ ባልደረቦቿ የግል ትምህርት ቤት ያስተምራሉ፣ ተማሪዎችንም ያስጠናሉ፡፡ እርሷ ግን ባለቤቷ የተሻለ ገቢ የሚያገኝ በመሆኑ ተጨማሪ ሥራ አትሠራም፡፡ ባለቤቷ ባይደግፋት ኖሮ ብቻዋን በምታገኘው የመምህርነት ደመወዝ ኑሮን መግፋት ከባድ ሊሆን እንደሚችል ትገምታለች፡፡

ተጨማሪ ሥራ የሚሠሩ ባልደረቦቿ የትምህርት ክፍለ ጊዜ እየተጋጨባቸው ለማስተማር ክፍል ሳይገቡ ሲቀሩና በተደጋጋሚ ሲያረፍዱ ታዝባለች፡፡ ይሄም በሱፐርቫይዘሮችና በመምህራን መሃል የጸብ መነሻ ሲሆን ተመልክታለች፡፡ በዚህ የተነሳ ተማሪዎች ማግኘት ያላባቸውን እውቀት ሳያገኙ እንደሚቀሩም አስተውላለች። ሆኖም የትምህርት አመራሮቹም የኑሮ ሁኔታውን ስለሚያውቁ ጫን ብው መምህራኖቹን ሲናገሩ አላየችም፡፡

በትምህርት ሚኒስቴር የመምህራን እና ትምህርት አመራር ልማት አስተዳደር ዴስክ ኃላፊ ወይዘሮ አሰገድ ምሬሳ እንደሚናገሩት፣ ትምህርት ሚኒስቴር ብቁ ተማሪዎችን ለማፍራት የበቁ መምህራን ሚና የጎላ መሆኑን በመረዳት ደረጃውን የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት ያላቸውን መምህራን ለማፍራትና ያሉትንም መምህራን ብቃት ለማሻሻል የሚያስችሉ ሥልጠናዎች በስፋት ሲሰጡ ቆይተዋል፡፡

በሀገር አቀፍ ደረጃ በ39 የመምህራን ትምህርት ኮሌጆች ሥልጠናዎች በስፋት እየተሰጡ ይገኛሉ። ከ30 በላይ በሚሆኑ ዩኒቨርሲቲዎች ውስት ባሉ የትምህርት ኮሌጆች በመጀመሪያ ዲግሪና በሁለተኛ ዲግሪ በመደበኛና በክረምት መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮችን በስፋት የማፍራት ሥራ ሲሠራ ቆይቷል፡፡

የትምህርት ሥራ ውጤት ለማግኘት ከታች ጀምሮ ለተማሪዎችን በቂ እውቀት እየሰጡ ማብቃት የሚችሉ ብቁ መምህራን ማፍራት ይጠይቃል፡፡ ይህንኑ መሠረት ያደረገ ሥራም እየተሠራ ነው፡፡

እንደ ዴስክ ኃላፊዋ መረጃ ከቅድመ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን መካከል 85 በመቶዎቹ በሰርተፍኬትና ከዛ በላይ የተመረቁ ናቸው፡፡ በዚህ ስሌት 85 በመቶዎቹ ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት አላቸው፡፡ ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ከሚያስተምሩ መምህራን ውስጥ 94 በመቶዎቹ ዲፕሎማና ከዛ በላይ የትምህርት ዝግጅት አላቸው፡፡

አዲስ በተዘጋጀው የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲ መሠረት ከሰባተኛ እስከ ስምንተኛ ክፍል የሚያስተምሩ መምህራን የመጀመሪያ ዲግሪ ሊኖራቸው ይገባል። ሆኖም 30 በመቶዎቹ ብቻ የመጀመሪያ ዲግሪ ሲኖራቸው 70 በመቶዎቹ ከዲግሪ ያነሰ የትምህርት ዝግጅት አላቸው፡፡



ወይዘሮ አሰገድ ምሬሳ፣

የሁለተኛ ደረጃ መምህራን ለደረጃው የሚመጥን የትምህርት ዝግጅት እንዲኖራቸው በርካታ ሥራ ተሠርቷል፡፡ በተመሳሳይ የመጀመሪያ ዲግሪና ከዛ በላይ ያላቸው መምህራንን ለማፍራት በርካታ ሥራዎች ተሠርተዋል፡፡ በዚህም 94 በመቶ የሚሆኑት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን የመጀመሪያ ዲግሪና ከዛ በላይ የትምህርት ደረጃ እንዲኖራቸው ተደርጓል። መምህራን አስፈላጊውን የትምህርት ዝግጅት መያዛቸው ብቻ በቂ ባለመሆኑ የሥራ ላይ ሥልጠና መርሀ-ግብሮች ተዘጋጅተው ሥልጠና ተሰጥቷቸዋል፡፡

ባለፉት ዓመታት የመምህራንና የትምህርት ቤቶችን ደረጃ ለማሻሻል ሰፊ ሥራ ቢሠራም፤ የትምህርት ጥራቱ ላይ የሚፈለገው ውጤት አልመጣም፡፡ የትምህርት ጥራትን ችግር ለመፍታት ትምህርት ሚኒስቴር ከ2013 ዓ.ም ጀምሮ የአጠቃላይ ትምህርት ለውጥ እያደረገ ነው። በሥልጠና ሥርዓቱ ላይ ያሉ ተግዳሮቶች ምንድናቸው? ለምን የተማሪዎች ውጤትን ማሻሻልና አስፈላጊውን ብቃት ማምጣት አልተቻለም? የሚለውን ምላሽ ለመስጠት በርካታ ጥናት ተደርጓል፡፡

የተጠኑ ጥናቶችን መነሻ በማድረግ አዳዲስ ስትራቴጂዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ የተደረጉት ጥናቶች በክረምት የሚደረገው የመምህራን የትምህርት ማሻሻያ ውጤታማ አለመሆኑን በማመላከቱ መረሃ-ግብሩ ሙሉ በሙሉ ተቋርጧል፡፡

የክረምት መርሃግብሩ መምህራን ሲገቡ ከሀምሌ 15 በኋላ መሆኑንና ሲወጡም ከነሀሴ 10 እስከ ነሀሴ 15 መሆኑንና አለፍ ሲልም ስሙ የክረምት ቢባልም አንዳንድ ጊዜ ከአስር ቀን ያልበለጠ የመማር ማስተማር ሥራ የሚከናወንበት ጊዜ መኖሩን በመናገር ወረቀትን ከማደል በስተቀር ወቅቱ የተቀመጡ ይዘቶችን ለመሸፈን የሚያስችል አለመሆኑን ይናገራሉ፡፡ በዚህ የተነሳ ከአሁን በኋላ በክረምት መርሀ-ግብር መምህራንን ከዲፕሎማ ወደ ዲግሪ እንዲሁም ከዲግሪ ወደ ሁለተኛ ዲግሪ የትምህርት ደረጃ ማሻሻያ ሥልጠና አይቀጥልም ብለዋል፡፡

የመምህራን ሥልጠና ሥርዓት ያለውን የትምህርት ስብራት መጠገን አለበት፤ የሚል ሃሳብ ተይዟል፡፡ የመምህራን የሥልጠና ሥርዓተ ትምህርቱን የመቀየር ሥራ እየተሠራ ይገኛል፤ በቅርብ ተጠናቆ ለትግበራ ይወርዳል። አዲሱ የመምህራን የሥልጠና ሥርዓተ ትምህርት ከዚህ ቀደም ካለው ሥርዓት የተለየ ነው፡፡

አንዱ መለያውም ተዛማጅነቱ የተጠበቀ መሆኑ ነው፡፡ ከዚህ ቀደም ተማሪዎች የሚማሩት ሥርዓተ ትምህርትና መምህራን የሚሠለጥኑበት ሥርዓተ ትምህርት የተዛማጅነት ችግር ነበረበት፡፡ ይሄንን ችግር ለመቅረፍም መምህራን ተማሪዎችን እንዲያስተምሩ የሚማሩት ሥርዓተ ትምህርትና ተማሪዎቹን በትምህርት ቤት የሚያስተምሩበት ሥርዓተ ትምህርት ተዛማጅ ሆኖ ተዘጋጅቷል፡፡

ዴስክ ሃላፊዋ እንደሚያብራሩት፣ ከዚህ ቀደም በሥራ ላይ ካሉና ከተመዘኑ መምህራን መካከል 24 በመቶው ብቻ ምዘናውን አልፈዋል፡፡ አሁን ያለውን መሠረታዊ ችግር ለመቅረፍ መምህራንን በአጫጭር የሥራ ላይ ሥልጠና ለማብቃት ታቅዷል፡፡ በዚህም ከዚህ ቀደም በክረምት መርሃግብር የተማሩትንና በቂ የትምህርት ክፍለ ጊዜ ያልተማሩትንም መምህራን መድረስ ይቻላል፡፡

የትምህርት ደረጃ ማሻሻያ ሲወስዱ ያልተካተቱ ርዕሰ ጉዳዮችና የተቀየረውን ሥርዓተ ትምህርት መነሻ ያደረጉ ይዘቶች እየተመረጡ ይሠለጥናሉ። ከመምህራን ደመወዝ አነስተኛነት ጋር ተያይዞ ለሚነሳው ጥያቄ በ2012 ዓ.ም ከሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ጋር በመተባበር ‹‹ጂ ኤ ጂ›› ተዘጋጅቶ ተተግብሯል፡፡ በዚህም በወቅቱ የመምህራንም ሆነ የርዕሳነ መምህራን ደመወዝ የተሻለ ነበር፡፡ ሆኖም የዋጋ ግሽበቱ ደመወዙን ዋጋ አሳጥቶታል፡፡

ለዚህም መምህራን በዋናነት የመኖሪያ ቤትና መሥሪያ ቦታ እንዲያገኙ ማድረግ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራ ይገኛል፡፡ በዚህም ከ120 ሺ በላይ መምህራን የመኖሪያ ቤትና ቦታ አግኝተዋል፡፡ በቀጣይም ይህ ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት ከክልሎች ጋርም መግባባት ላይ ተደርሷል፡፡

በተጨማሪም መኖሪያ ቤት ለሌላቸው መምህራን ክልሎች አቅማቸውን ባገናዘበ መልኩ የቤት አበል እንዲያገኙ እየተደረገ ነው፡፡ በቀጣይ መምህራን የራሳቸውን ኢኮኖሚ የሚያዳብሩበት ሁኔታን ለመፍጠር የመምህራን ሕብረት ሥራ ባንክ ለመክፈት ጥናቶች እየተካሄዱ ነው፡፡ በባንኩና በሌሎች አማራጮች መምህራን የሚቆጥቡበት የሚበደሩበትና ኑሯቸውን የሚያሻሽሉበት ሥርዓት መዘርጋት ካልተቻለ በየጊዜው የመምህራንን ኑሮ ለማሻሻል ደመወዝ መጨመር ምንም ጥቅም የለውም፡፡ ስለዚህ ሌሎች አማራጮችን መፈለግ ላይ ትኩረት ማድረግ ይገባል፡፡

የትምህርት ስብራቱ የሚጠገነው በዋናነት መምህራንና የትምህርት አመራሮች በሚያደርጉት ርብርብ ነው፡፡ ሌሎች ባለድርሻዎች ተሳትፎ ቢኖራቸውም ዋናው ቁልፍ በክፍል ውስጥ ባለው መማር ማስተማርና በትምህርት ቤት አመራር የትመህርት ስብራቱ ሊጠገን የሚችለው። በየደረጃው ያሉ መምህራንና የትምህርት ቤት አመራሮች የተፈጠረውን የትምህርት ስብራት ለመቀልበስ የሚያስችል ሥራዎችን ባለው አቅም አጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል፡፡

የኢትዮጵያ መምህራን ማህበር ምክትል ፕሬዚዳንት መምህር ሽመልስ አበበ በበኩላቸው እንደሚናገሩት ከቅርብ ዓመታት ወዲህ የነበረው የተማሪዎች ውጤት ልክ እንዳሁኑ ‹‹ይሄን ያህሉ አለፈ ይሄን ያህሉ ወደቀ›› ተብሎ ቢለይ ኖሮ ከዚህ የተሻለ ውጤት ይመዘገብ ነበር የሚል እምነት የለኝም፡፡

ከዚህ ቀደም 101 ያመጣ ተማሪ ዩኒቨርሲቲ ይገባ የነበረበት ሁኔታ እንደነበር በማንሳት ‹‹ስንት በመቶው ነው ከ50 በመቶ በላይ ስንቱስ ከ50 በመቶ በታች ውጤት አመጣ የሚለው›› በደንብ አይለይም ነበር ብለዋል፡፡ አሁን ባለው ሁኔታ ተማሪዎች ተረጋግተው እየተማሩ ያለበት ሁኔታ አለመኖሩ የኮቪድ መከሰት፣ በሀገሪቱ የተለያዩ አካባቢዎች ጦርነት መኖሩን ተከትሎ ተማሪዎች በአንድ ሃሳብ ተረጋግተው የሚያጠኑበትና የሚፈተኑበት ሁኔታ አለመኖሩ ለውጤቱ ማነስ አሉታዊ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡

ፈተና በራሱ የተረጋጋ አካባቢ ይፈልጋል። ተማሪዎቹ ፈተናውን ለመፈተን ከመኖሪያ አካባቢያቸው ርቀው ሄደዋል፡፡ አብዛኛው ተማሪ ከ20 ዓመታች በታች መሆናቸውና አዲስ ቦታ ፍራቻ ነበረባቸው፡፡ በዚህ ላይ የብቃቱ ችግር ተደምሮ ያለፉት ተማሪዎች ሦስት ነጥብ ሁለት በመቶ ብቻ ናቸው፡፡ ተማሪዎች በደንብ የተዘጋጁበት ሁኔታ ቢኖር ከዚህ የተሻለ ውጤት ይመዘገብ ነበር፡፡

ያም ሆኖ ግን የትምህርት ጥራት ከጊዜ ወደጊዜ እየወረደ መጥቷል፡፡ ለዚህ እንደምክንያት የተቀመጡት ተማሪዎች ትኩረት ሰጥተው እየተማሩ አለመሆናቸውና በመምህራንም በኩል የተለያዩ ችግሮች መኖራቸው ነው። የመምህራን ጥቅማጥቅም ይከበር የሚለውም ሌላው ምክንያት ነው፡፡

እንደ ምክትል ፕሬዚዳንቱ ማብራሪያ፤ የኑሮ ውድነቱን ተከትሎ በክልሎች ባጃጅ እየነዱ የሚያስተምሩ መምህራን፣ አናጺ ቤት እየሠሩ የሚያስተምሩ መምህራንና፣ በገጠር አካባቢ እርሻ እያረሱ የሚያስተምሩ መምህራን አሉ፡፡ ሆኖም መምህር ሆኖ ተጨማሪ ሥራ መሥራት እንደማይቻልና መምህር የመምህርነትን ሥራ ብቻ መሥራት እንዳለበት መግባባት ላይ ተደርሷል። በዛው ልክ ተማሪም የሚጠበቅበትን ድርሻ መወጣት ካልቻለ ችግሩ አይፈታም፡፡ የትምህርት ጥራት ጉድለት አሳሳቢ ነው። ስለዚህ የወደቀውን ትምህርት ማንሳት የሁሉም ሕብረተሰብ ድርሻ መሆን አለበት፡፡

የመምህራንን የጥቅማጥቅም ጥያቄ መጠየቅ የሚቻለው የመማር ማስተማሩ ሥራ ላይ ውጤት ሲመዘገብ ነው፡፡ መምህር ሙሉ ጊዜውንና እውቀቱን አውጥቶ የመማር ማስተማር ሥራ ላይ አውሎ የተጣለበትን ኃላፊነት መወጣት መቻል አለበት። ሆኖም በዘርፉ ሰፊ የመልካም አስተዳደር ችግሮች አሉ፡፡ ስድስት ወር ድረስ ደሞዝ ያላገኙ መምህራን መኖራቸውንና ደሞዛቸው ከፍቃዳቸው ውጪ እስከ 18 በመቶ የሚቆረጥባቸው አካባቢዎችም አሉ፡፡ አልፎ አልፎም መምህራን በራሳቸው ደሞዝ የማያዙበት ሁኔታ በመኖሩ ይህ የመልካም አስተዳደር ችግር ሊቀረፍ ይገባል፡፡ በዛው ልክ መምህራንም ሙሉ አቅማቸውን ይዘው ማስተማር ይጠበቅባቸዋል፡፡

ምንም እንኳን በኢትዮጵያ ለመምህራን የሚከፈለው ክፍያ ዝቅተኛ ቢሆንም መምህራኖች ሥራ ሊሠሩ የሚገባው በቂ ክፍያ ሲከፈላቸው ብቻ መሆን የለበትም፡፡ አንዴ የተገባበት የውድድር ሜዳ እንደመሆኑ ውድድሩን አሸናፊ ሆኖ መውጣት ግድ ይላል፡፡ ማህበሩ የመምህራንን ጥያቄ ለማስመለስ የማይደርስበት ቦታ የለም፡፡ እንደዛም ሆኖ መምህራን ባላቸው አቅም ልክ ማስተማር መቻል አለባቸው የሚለው ጉዳይ ላይ መግባባት ተደርሷል፡፡

ከዚህ ውስጥ የመምህራንን የመኖሪያ ቤት ጥያቄ በ2007 ዓ.ም ለቀድሞው የኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ኃይለማርያም ደሳለኝ ቀርቧል፡፡ በአዲስ አበባ ቅድሚያ ተሰጥቷቸው የጋራ ኮንዶሚኒየም የተሰጣቸውና በስማቸው የዞረላቸው አምስት ሺ መምህራን እንዳሉ ይታወሳል፡፡ በተመሳሳይም በክልሎች ከሦስተኛ ወገን ክፍያ ነጻ የሆነ በማህበር ለተደራጁ 120ሺ መምህራን የመኖሪያ መሥሪያ ቦታ ተሰቷቸዋል፡፡

የኦሮሚያ ክልል በ2016 ዓ.ም ቦታ ላልደረሳቸው መምህራን ቦታ ለመስጠትና ትምህርት ቤት ላይ በመመላለስ ጊዜ እንዳይባክንና መምህራን ላልተገባ ወጪም እንዳይዳረጉ ገጠር ላይ ለሚገኙ ሁሉም ትምህርት ቤቶች የመምህራን ማረፊያ ቤት እሠራለሁ ብሎ ወደ ሥራ ገብቷል፡፡ በመኖሪያ ቤት ረገድ ጥሩ ደረጃ ላይ እንዳለና ማህበሩም ይበልጥ ጥያቄው ምላሽ እንዲያገኝ የማስታወስ ሚና ይጫወታል፡፡

‹‹ለመምህር መኖሪያ ቤት ቤቱም ቢሮውም ነው›› ያሉት መምህር ሽመልስ፤ የመማር ማስተማር ሥራ እንደሌላ ሥራ ከቢሮ ወጣሁ በማለት ጠረጴዛ ላይ ተትቶ የማይወጣና ዝግጅት የሚፈልግ ነው ይላሉ። ለመምህራን ሁለንተናዊ ዝግጅት የመኖሪያ ቤት ያስፈልጋል፡፡ የመኖሪያ ቤት ማግኘታቸው ቢሮም ቤትም በሆነው ቤታቸው መምህራን ተነቃቅተው እንዲሠሩ ያግዛል፡፡ በዚህ የተነሳ ለመምህራን የመኖሪያ ቤት ማግኘት ቅድሚያ የሚሰጠው ጉዳይ መሆን አለበት፡፡

አዲስ አበባ መኖሪያ ቤት ላላገኙ መምህራን የቤት አበል መጀመሩና የከተማ ባስ ትራንስፖርት ነጻ መደረጉ የሚበረታታ ነው፡፡ ይሄን ተሞክሮ ሌሎችም እየወሰዱት ነው፡፡ የመምህራን ጥቅማጥቅም ጥያቄ አለ ግን የማህበሩ አመራሮች ባለሥልጣናት ዘንድ ይሄን ጥያቄ ይዘው ሲቀርቡ ‹‹ትምህርቱ ያለበትን ታውቃላችሁ ወይ?›› እየተባልን አንገታችንን እየደፋን ነው የሚሉት መምህር ሽመልስ፤ ማስተማር የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጠው ተግባር መሆኑን በማንሳት የወደቀውን ትምህርት ለማንሳት መምህራን ምንም ቅድመ ሁኔታ ሳያስቀምጡ ባላቸው አቅም በሙሉ እንዲያስተምሩ አደራ ብለዋል፡፡

# “የዓድዋ ድልና የሕዳሴ ግድብ ኢትዮጵያውያንን በአንድነት ያቆሙ የዐቢይ ትርክቱ ተምሳሌት ናቸው”

ረዳት ፕሮፌሰር አየለ በክሪ (ዶ/ር)
የታሪክ ምሁር



አስቴር ኤልያስ

**ትርክት ለሀገረ መንግሥት ግንባታ ያለው ሚና አሉታዊም አዎንታዊም እንደሆነ ይነገራል። ለዚህም በምክንያትነት የሚቀመጠው እንደ ሕዝብ ለመተባበርም ሆነ ለመፎካከር፣ ግጭት ለመፍታትም ሆነ ለማባባስ እንዲሁም ሁለንተናዊ ብልጽግና ለማምጣትም ሆነ ድህነትን ለመሸከምም የሚያገለግል በመሆኑ ነው፡፡**

**ትርክትን ዐቢይ እና ንዑስ ትርክት በሚል በሁለት የሚከፍሉ የዘርፉ ምሁራን፣ ዐቢይ የሚባለው ትርክት የጋራ ማንነትና የሁሉም ጉዳይ የሆነ መሆኑን እንዲሁም የጋራ ችግር ለሆነው ጉዳይ የጋራ መፍትሔ ማስገኘት የሚችል መሆኑን ያመላክታሉ፡፡ ንዑስ ትርክት ደግሞ ተናጥላዊ ነው። የጋራ ጉዳዮች ላይ አያተኩርም።**

**አዲስ ዘመን ከዚሁ ጉዳይ ጋር ተያይዞ ስለትርክት ምንነትና ሀገራዊ አንድነትን በማጠናከር በኩል ያለውን ፋይዳ በተመለከተ ኢትዮጵያ ከታሪክ ምሁሩ ከረዳት ፕሮፌሰር አየለ በክሪ (ዶ/ር) ጋር ያደረገውን ቆይታ እንደሚከተለው አጠንቅሯል፡፡**

**አዲስ ዘመን፡- እንደ አንድ የታሪክ ምሁር ትርክት ምንድን ነው ይላሉ? ንዑስና ዐቢይ ትርት የሚባሉት ልዩነታቸው ምንድን ነው?**

**አየለ (ዶ/ር)፡-** ትርክት ከታሪክ አንጻር ከወሰድነው የተከናወኑ ድርጊቶችን የምንረዳበት መንገድ ነው። አሊያም የተከናወኑ ድርጊቶችን ወደቃላት በመቀየር ለዚያ ጉዳይ ሕዝብን እንዲገዛ ማድረግ እና በሥርዓቱ እንዲተዳደር ማስቻል ነው፡፡

የትርክት አይነቶች ሁለት ናቸው፡፡ አንደኛው ታላቁ ወይም ዐቢይ ትርክት የሚባለው ሲሆን፣ ብዙውን ጊዜ የሚሠራውና የሚሰራጨው የሀገር አንድነትንና አብሮነትን ለማስረጽ ነው። በሌላ በኩል የበላይነትን ለማስረጽም ጥቅም ላይ ይውላል፡፡ ለምሳሌ የአንድ ሀገር ንጉሥ ማስረጽ የሚፈልገውን ሀገራዊ ጉዳይ ደጋግሞ ወደሕዝቡ የሚያደርስ ከሆነ ትርክት ሊቀየር ይችላል፡፡ በተለይ ንጉሡ የራሱ ኃይል አይነኬ መሆኑን የሚያሳይበት መስመር ሊሆን ይችላል፡፡ ሌላ ምሳሌ ብንወስድ ምዕራባውያን አፍሪካን በሙሉ አሊያም ደግሞ አብዛኛውን ዓለም በቁጥጥር ሥር ስላደረጉ እኛ ነን ገናናዎች በሚል አስተሳሰቡን ከድርጊት ጋር ቀምረው ያስረጹት አይነት አካሄድ ነው፡፡

ከዚህ የተነሳ ምዕራባውያኑ የበላይ ነን የሚለው ጉዳይ መመሪያቸው አድርገው ይዘውት ቆይተዋል፡ እናም ከሌሎች ጋር ሊፈጠሩ የሚችሉ ግንኙነቶችን የበላይና የበታች እንዲሁም የደረጃ ጉዳይ አድርገውት እየኖሩ ይገኛሉ፡፡ ከዚህ የተነሳም በዚህ መንፈስ ቀሪዎቹን የዓለም ሀገራትን ሊጫኑ ችለዋል፡፡

እነዚህ ታላላቅ ትርክቶች ጊዜው ደርሶ ደረጃቸው ዝቅ ያሉ ሕዝቦች አሊያም ደግሞ በሌላ አነጋገር በቅኝ አገዛዝ ስር የወደቁ ሕዝቦች ይህንን አካሄድ በሚገባ ከተገነዘቡ በኋላ እነርሱን ለመጨቆን የተፈጠሩ መሆኑን በማወቃቸው የምዕራባወውያኑ ዐቢይ ትርክት ፈተና እየገጠመው መሆኑ ይታወቃል፡፡ ለምሳሌ በአሜሪካ እስከ እኤአ 1950 ድረስ ጥቁሮች የበታች፤ ነጮች ደግሞ የበላይ ተብለው ዘልቀው ነበር። ነገር ግን ጥቁሮቹ “እኛ እንዴት የበታች እንሆነናለን? አይደለንም!” የሚለውን ጉዳይ ለማስረጽ ሲሉ የሚጠቀሙባቸው የበላይ የሆኑ ስልቶች አሉ፡፡ ከዚህ ውስጥ አንዱ የሚደረጉ የፖለቲካ እንቅስቃሴዎች ናቸው፡፡

ወይም ደግሞ ቅዱስ መጽሐፍን ሲረዱና ሲተረጉሙ በእነርሱ አይነት መልክ ያለ ጉዳይ መኖሩን ማስተዋላቸው ነው፡፡ ከዚህም ውስጥ አንዱ በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ያገኙት ነገር ሲሆን፣ ይኸውም ከ60 ያህል ጊዜ በላይ ኢትዮጵያ መጠቀሷ ነውና ያንን ይረዳሉ፡፡ በዚህም “ኢትዮጵያ ማለት ጥቁር ሕዝብ ያላት ሀገር ናትና እኛም እግዚአብሔር የፈጠረን ጥቁር ሕዝቦች ስለሆንን በምንም አይነት ሁኔታ ደረጃችን ዝቅ ያለ ሕዝብ አይደለንም” በሚል ወደታላቅ ትርክት ውስጥ የገቡ ናቸው፡፡

ከዚህም የተነሳ ዐቢይ ትርክታቸው “የነጭ የበላይነት የለም፤ ሁሉም እኩል ነው” በሚል እንቅስቃሴ ውስጥ ይገባሉ፡፡ በዚህ ዐቢይ ትርክታቸው አብዝተው የሚገልጹት ዋና ጉዳያቸው “ጥቁር ሕዝቦች ማለት የእግዚአበብሔር ምርጥ ሕዝቦች ናቸው” የሚለውን ነው፡፡ ለዚህም ዋና ማሳያቸው በቅዱስ መጽሐፍ ውስጥ ኢትዮጵያ የሚለው ስም ደጋግሞ መገለጹን ጭምር ነው፡፡ በመሆኑም “ጥቁር በጣም ቆንጆ ነው” የሚለውን መፈክር አጥብቀው በመያዝ የራሳቸውን ታላቅ ትርክት መፍጠር የቻሉበት ሁኔታ ነው ያለው፡፡

እናም ሀገር የሚታየው እንዲሁ ነው፡፡ ለምሳሌ የእኛ ዐቢይ ትርክት መሠረቱ ሲታይ ትልቁ ጉዳይ ከንግሥተ ሳባ ጋር የተያያዘ ጉዳይ ወይም ታሪክ ነው። በእርግጥ አንዳንዶቹ “ንግሥተ ሳባ የመናዊት እንጂ ኢትዮጵያዊት አይደለችም” ይላሉ፡፡ እንዲህ የሚሉ አካላት ሊገነዘቡ ያልቻሉት ነገር በቀደመው በጥንቱ ዘመን ከክርስቶስ ልደት በፊት በነበረው ዘመን ነው። ኢትዮጵያዊት አይደለችም የሚሉ ስህተታቸው ኢትዮጵያ የሚባለው ግዛት በወቅቱ ቀይ ባህርንም የሚጨምር መሆኑን አለመገንዘባቸው ነው፡፡ በዛ አካባቢ ያሉ የመንና ሳዑዲ አረቢያ በሚል ስያሜ የሚታወቁት በወቅቱ እነርሱም በኢትዮጵያ ስር መሆናቸውን “ንግሥት ሳባ ኢትዮጵያዊት አይደለችም” የሚሉ አካላት ይዘነጉታል። እንዲያም ሆኖ የንግሥት ሳባ ትርክት የተፈጠረበት የራሱ አካሄድ አለው። ጥበብን ፍለጋ ወደ ኢየሩሳሌም ስትሔድ የራሷም መንግሥት ሀብታም መሆኑን የሚያሳይ ስጦታ ይዛ የሄደች ንግሥት የነበረችም ናት።

ዋና ቁም ነገሩ ሁሉም ሕብረተሰብ የየራሱ ታላቅ ትርክት እንዳለው መረዳቱና በዚያ ታላቅ ትርክት ተጠቃሚ ለመሆን መበርታቱ ነው፡፡ አለኝ የሚለው ትርክት ግን የተገነባበት መንገድ ምን ፍለጋ ነው የሚለው ላይ ማተኮሩ መልካም ነው፡፡ አንድ ሀገር አለኝ የሚለው ዐቢይ ትርክት ሕዝብን የሚያስተባብርና በማንነቱ እንዲኮራ የሚያደርግ ቢሆን ተመራጭ ነው። ችግሩ የአንዱ ትርክት የራሱን ማንነት ብቻ የሚያጎላ በመሆኑ ሌላው ላይ ለመጫን መፈለጉ ነው። በሌላ በኩል አንዱ ሀገር አለኝ የሚለውና አብዛኛውን ሕዝብ የሚያስማማ ዐቢይ ትርክት ሆኖ እያለ ሌላው አካል ግን “ይህን አልቀበልም” ማለቱ ላይ ነው፡፡ ይህ “አልቀበልም” ባዩ አካል ትርክቱ የተገነባበት መንገድን አለማስተዋሉ ነው። ከዚህም ሌላ ጉዳዩን ፖለቲካዊ ከማድረጉ በተጨማሪ አጥብቦ ማየቱም ሌላው ፈተና የሆነ ነገር ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አንዳንዶች ዐቢይ ትርክት የሚገነባው በትውልድ ነው ይላሉ፡፡ ከዚህም የተነሳ እርስዎ ከጠቀሱት ዐቢይ ትርክት በተጨማሪ ጉዳዩን ከጊዜ አኳያ ቀረብ ስናደርግ የዓድዋ ድል እንዲሁም የበለጠ ስናቀርበው ደግሞ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ እንደ ዐቢይ ትርክት ያነሳሉና ከዚህ አኳያ ይህንን እንዴት ይገልጹታል?**

**አየለ (ዶ/ር)፡-** የዓድዋ ድልንም ሆነ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን በምናስተውልበት ጊዜ የአንድነት ዐቢይ ትርክት ተምሳሌቶች ሊሆኑ የሚችሉ ናቸው፡፡ ስለሆነም የዓድዋ ድልና የሕዳሴ ግድብ ኢትዮጵያውያንን በአንድነት ያቆሙ የዐቢይ ትርክቱ ተምሳሌት ናቸው፡፡

በተለይ ዓድዋ አይነተኛ ዐቢይ ትርክት ነው ማለት ይቻላል፡፡ ዓድዋ በትውልድ የተሠራና አሁን ላለንበት ማንነታችን መሠረት ያስቀመጠ ታላቅ ድል ነው። ለዘመናዊነታችንም መነሻ ነው፡፡ ምክንያቱም በወቅቱ የመጣው ጠላት እኔ የበላይ ነኝ በሚል መንፈስ ኢትዮጵያን ቅኝ ለመግዛት የመጣ ሲሆን፣ ሲሸነፍ አሸናፊው ከእሱ የተሻለ ሥልጣኔ እና ማንነት አለው ማለት ነው፡፡

ትልቁ ችግራችን ነው ብዬ የማስበው በተለይ ባለፉት 30 ዓመታት ያንን ጸጋ እና ታላቅ ድል ለአንድነታችን ማጠናከሪያ እንደ ድልድይ ከመጠቀም እና የተሻሉ ሁኔታዎችን ለሁላችንም ከመፍጠር ይልቅ ታሪክን ለማዛበት የተኬደበት ሙከራ መኖሩን ነው። በዐቢይ ትርክት ውስጥ ሌላ ያንን አይነት የሆነውን ትርክት ለማቃለል የሚደረጉ አካሄዶችም ነበሩ፡፡

ዓድዋ ዐቢይ ትርክት ነው፡፡ ዐቢይ ትርክት የሚያደርገው ዋና ነገር ደግሞ በወቅቱ ኢትዮጵያዊ የተባለው ሕዝብ ሁሉ የተሳተፈበት ጦርነት መሆኑ ሲሆን፣ የተገኘውም በኢትዮጵያውያን ትጋት መሆኑ ነው፡፡ ይህ ድል ለእኛ ለኢትዮጵያውያን ዘመናዊነትና ወደፊት መገስገስ ታላቅ አርዓያ መሆን ያለበት ነው፡፡

ይህ የእኛ የኢትዮጵያውያን ዐቢይ ወይም ታላቅ ትርክት ነው የሚባለው የዓድዋ ድል በቅኝ ገዢዎች እጅ ሳንወድቅ ሙከራዎቻቸውን ሁሉ አክሽፈን በነጻነት መኖር መቻላችን ነው፡፡ ይህ ትግላችንና በአንድነታችን ያገኘነው ድላችን ዐቢይ ትርክታችን በመሆኑ ለሌሎች የአፍሪካ ሀገራት በአርዓያነት የሚጠቀስ ጭምር ነው፡፡ የዓድዋ ድል እነርሱም በሚፈጥሩት ዐቢይ ትርክት ላይ ይጠቃለላል። በዐቢይ ትርክታቸው ውስጥ ከመጨመር አልፎ ወደ ሌሎችም ይሄዳል። ምክንያቱም ዐቢይ ትርክት ሲገነባ እዛው የሚቀር ሳይሆን ከራስ አልፎ ለሌሎች የሚተርፍ ነው፡፡

የሌላው ዐቢይ ትርክት ጠቃሚ እስከሆነ ድረስ መውሰድ የሚቻል ነው፡፡ ለምሳሌ ፓን አፍሪካኒዝም ሲባል መላ አፍሪካን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ስለዚህ መላ አፍሪካ ውስጥ ያሉ ጥሩ ናቸው፤ አርዓያ ሊሆኑ ይችላሉ፤ ሊያሳድጉንና ሊያስተባብሩን ይችላሉ የሚሉትን መርጠንና አቀናጅተን ትርክት እንፈጥራለን። ከዛ ኅብረት የሚመጣው አንድነትም አፍሪካውያንን ያስተባብራል፡፡

ከዚህም የተነሳ ዓድዋ ከእኛ አልፎ ለሌሎች ሀገራት በሁለተኛ ደረጃ ብሎም በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ጭምር እንደ ታላቅ ትርክት የሚቆጠር ነው። በተለይ በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አፍሪካ ሀገር በሆኑ በጋና እና ሴኔጋል የሚማሩት ጉዳይ ሆኗል፡፡ ለዚህ ትልቁ ምክንያት ምንድን ነው ከተባለ ሁሉም ነጻነቱን መሻቱ ነው፡፡ ይህን ነጻነት ኢትዮጵያውያን እንዴት ሊያስጠብቁ ቻሉ የሚለው ጉዳይ ቁልፉ መሠረት ነው። ከዚህ የተነሳ ዓድዋ የእኛ ብቻ የዐቢይ ትርክታችን መሠረት ሳይሆን በሌሎቹም ሀገራት ዐቢይ ትርክት ውስጥ ሊጨመር የቻለ ሆኗል። እንደሚታወቀው ትርክት ሲባል ታሪክ ላይ የተመረኮዘ ትርክት አለ። ይህ ማለት አንድ የተከናወነ ድርጊት ረጅም ጊዜ የሚያስቆጥር ከሆነ ወደ ታሪክ ይቀየራል ማለት ነው። ይህም የሚገነባው በትውልድ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ዐቢይ የሚባለው የትርክት አይነት ጥሩ እና አንድነትን ለመፍጠር አቅም ያለው ነው፤ ከዚህ በተቃራኒ ያለው ንዑስ የሚባለው የትርክት አይነት ዜጎች መግባባት ላይ እንዳይደርሱ የሚያደርግ ነው ይባላልና ይህንንስ እንዴት ያዩታል?**

**አየለ (ዶ/ር)፡-** እውነቱን እንነጋገር ከተባለ ኢትዮጵያ ውስጥ ሕዝብ ከሕዝብ ይጣላል? ይጋጫል? ብለን መጠየቅ ይኖርብናል፡፡ በእርግጥ ኢትዮጵያውያን አብዛኛው ታሪካችን የጦርነት ነው። በዚህ ታሪካችን ውስጥ ግጭት መኖሩ እንደተጠበቀ ሆኖ መስማማትም መግባባትም እንዳለ የሚዘነጋ

ወደ ገጽ 10 ዞሯል

# ወቅታዊ

# “የዓድዋ ድልና የሕዳሴ ግድብ ኢትዮጵያውያንን...

ከ ገጽ 9 የዞረ

አይደለም፡፡ በመሆኑም ታሪካችን ውስብስብ እንጂ ወጥ ነው ማለት አይቻልም።

መረዳት ያለብን ነገር ቢኖር ግጭት ሲኖር የሚፈጠሩ ትርክቶች ይኖራሉ፡፡ እነዛን ትርክቶች ሆን ብሎ አንዱን ሕዝብ ጠላት ሌላው ሕዝብ ደግሞ ጨቋኝ አድርጎ የማቅረብ ጉዳይ ነው፤ እሱ ደግሞ ሥርዓት እና የፖለቲካ አካሄድ ነው እንጂ ታሪካችን ሲታይ ግን ልክ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ ያለው አይነት ኅብረት ያለው ነው፡፡ ነጬን በሀገር ወዳድ ስሜት ገጥመው ያሸነፉት ኢትዮጵያውያኑ ናቸው፡፡ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ማን ናቸው የሚባል ከሆነ በቋንቋ እና በኃይማኖት የሚለያዩ፤ ነገር ግን ብዝሃነት ያላቸው ሕዝቦች ናቸው። የቱንም ያህል በዘር፣ በኃይማኖት የተለያዩ ቢሆኑም፤ በአንድ ሀገር ውስጥ “እኛ ኢትዮጵያውያን ነን” ብለው የኖሩ ሕዝቦች ናቸው፡፡

አንድ እውነት ስለመኖሩ ግን የሚያጠያይቅ ነገር የለም፡፡ ኢትዮጵያን በመሩ መንግሥታት መካከል ጥፋትም ልማትም መኖሩ አይካድም፡፡ ደግሞም እንደ አጠቃላይ ሲታይ በዓለም ላይ ሀገረ መንግሥት የምንለው በሚመሠረትበት ጊዜ ሰላማዊ በሆነ መንገድ አልፎ ያለምንም ጠብና ቁርሾ የተመሠረተ ሀገር አለ ብሎ ማለት አይቻልም፡፡ ይህ ሐቅ የሆነ የታሪክ ምስክር ነው ማለት ይቻላል፡፡ ዋናው መረዳት ያለብን ነገር ሕዝብ ሁልጊዜ የተሻለ ነገር ያለው መሆኑን ነው።

አንዳንዴ ሁለት የተጋጩ ትርክቶች ሲመጡ ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌ የእስራኤልን እና የፍልስጤምን ጦርነት ብናስተውል በዚያኛው ወገን ያለው “መሬቱ የእኔ ነው ይላል” በእዚህኛው ወገን ያለውም “መሬቱ የእኔ ነው” ሲል ይደመጣል፡፡ በዚህኛውም ሆነ በእዚያኛው ወገን አንድ ሲነገር የቆየ ትርክት አለ ማለት ነው፡፡ በአንድ ጉዳይ ላይ የሚኖር እኩል አይነት ፍላጎት ግጭትን ያመጣል፡፡

በሀገራችን ኢትዮጵያ በተለያየ ምክንያት ሕዝብ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ ይንቀሳቀሳል፡፡ ይህ የሚሆነው ምናልባት የሚያርሱት መሬት አንሷቸው ሊሆን ይችላል። ከዚህ በተጨማሪ የተለያዩ ምክንያቶች ሊኖሩ ይችላሉ። በዚህ ምክንያት ወደ አዲስ አካባቢ ሲያቀኑ በተወሰነ መልኩ ግጭት ሊፈጠር ይችላል። ይህ የሚፈጠረው ደግሞ መግባባት እስካልተቻለ ድረስ ብቻ ነው፡፡

ነገር ግን አሁን አሁን ኢትዮጵያ ውስጥ እያየን ያለው ነገር ወደየትኛውም ስፍራ ቢኬድ ጥርት ያለ አንድ ልዩ የሆነ ጎሳ እዚህ ቦታ አለ ሊባል አይችልም። ሁሉም ክልል የተለያየ ቋንቋ ተናጋሪ አለ፡፡ ለምሳሌ ትግራይ ክልል ትግርኛ ተናጋሪ ብቻ ነው ያለው ማለት አይቻልም፡፡ ምክንያቱም እዛም ሳሆ፣ ኩናማና ኢሮብ አሉ፡፡ እነዚህ በጣም አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ስለሆኑ ብዙውን ጊዜ አይጠቀሱም እንጂ በክልሉ ከጥንት ጀምሮ ያሉ ናቸው። እንዲያውም የሚነገረው የአክሱም አካባቢ የኩናማዎች እንደሆነ ነው፡፡ ከዛ ተገፍተው አሁን ያሉበት ቦታ እንደሄዱም ይገለጻል። ስለዚህ በኢትዮጵያ ባሉ የተለያዩ አካባቢዎች ብንሔድ የምናስተውለው ነገር እንዲህ አይነቱን ብዝሃነትን ነው።

አሁን አሁን እየተደረገ ያለው በቋንቋ ላይ የተመሠረተ የፖለቲካ አስተዳደር ውስጥ እንድንገባ ነው። እሱ ግን ሊሆን አይችልም ባይ ነኝ፡፡ ወደእያዳንዱ ቦታ በምንሔድበት ጊዜ አስቀድሜ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት ጸዓዳ ነው ወይም ጥርት ያለ ነው የሚባል አንድ ቋንቋ ብቻ የሚናገር ሕዝብ የለም። እንዲያም ቢሆን ያ ሕዝብ እናገረዋለሁ የሚለው ቋንቋ ራሱ ሊቀየር ይችላል፡፡ ምክንያቱም ቋንቋ በባሕሪው ተለዋዋጭ ነው፡፡ ኦሮሚኛ ተናጋሪ የነበሩ ሰዎች አማርኛ ተናጋሪ ሊሆኑ ይችላሉ፤ በተመሳሳይ አማርኛ ተናጋሪ የነበሩ ሰዎችም ኦሮሚኛ ተናጋሪ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

ከዚህ የተነሳ የኢትዮጵያውያን ብዝሃነት ስብጥርጥር ያለ ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ ሕዝባዊነት



ደግሞ ለምሳሌ እኔ ስለእኔነቴ ሳስብ ከጎኔ ያሉ ጎረቤቶቼን ካልጨመረ፤ ከጎኔ ያሉ ብሔሮችን ካላካተተ ያኔ ነው አገማመታችንና አሠራራችን ትክክል የማይሆነው። ያኔ ደግሞ አመለካከታችን ትክክል ስለማይመጣ ወደግጭት ያመራል እንጂ እንዲሁ ሕዝብ ከሕዝብ ጋር በምንም አይነት ሁኔታ አይጋጭም፡ ፡ ይልቁኑ ግጭት እንኳ ቢኖር ሕዝብ ከሕዝብ ጋር ሆኖ የሚፈልገው መፍትሔ ነው፡፡ ለዚህ ዋና ምሳሌ አድርገን ማንሳት የምንችለው በሁሉም ብሔር የራሱ የሆነ በሽምግልና የሚካሄድ የእርቅ ሥርዓትን ነው። ቅራኔዎችና አለመግባባቶች በጭራሽ አይኖሩም ብሎ መደምደም አይቻልም፤ በአንዳንድ አጋጣሚዎች የሚነሱ ግጭቶች ካሉ እነዚያን ግጭቶች ለማቃለልና ወደነበረው ሰላማዊ የአኗኗር ዘይቤ ለመመለስ ሁሉም እንደየባህሉ የእርቅ ሥርዓትን ይከተላሉ፡፡

ዋነኛ መገለጫ የሆነው የዓድዋው ጉዳይን ብንመለከት ሁሉም ኢትዮጵያዊ “ከብሔርነቴ ሆነ ከኃይማኖቴ የሚቀድምብኝ ኢትዮጵያዊነቱ ነው” በሚል የተቀበለው ጉዳይ በመሆኑ ዐቢይ ትርክት መሆን ችሏል። በወቅቱ የዓድዋ ጦርነት ላይ ለመሳተፍ የተንቀሳቀሱት በአብዛኛው ከ18 እስከ 25 የእድሜ ክልል ውስጥ ያሉ ናቸው፡፡ እናም በዚያን ወቅት ይህ ኃይል ባለበት ቦታ ሆኖ እና ትዳር መስርቶ አርሶ አደሩም እያረሰ፤ አርብቶ አደሩም እያረባ መኖር ይችል ነበር። ነገር ግን እንዲህ አይነቱ ተደላድሎ መቀመጥ ዘላቂ ሊሆን እንደማይችል ከወዲሁ መረዳት የቻለ ኃይል ነው፡፡ በመተባበርና አንድነቱን ብሎም ብዝሃነቱንና ሀገሩ በመቀበልም በጦርነቱ ያላአንዳች ማቅማማት ሊሳተፍ በቅቷል፡፡

በመሆኑም ዓድዋ የእኛ ዋና እና ታላቁ ትርክታችን ብቻ ሳይሆን ለሌላ ተግባራችንም በዋናነት ተጠቃሽ መሆን የሚገባው ነው፡፡ ለምንሠራቸው የአንድነት ሥራችን ሁሉ ዋና ማጣቀሻችን ሊሆን የተገባው መሆን አለበት፡ ኢትዮጵያውያን ዓድዋ ላይ የከፈሉት መስዋዕትነት ለሁላችን ነውና ያንን ጉዳይ በቅጡ መረዳት መቻል አለብን የሚል አተያይ አለኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ዓድዋን የመሳሰሉ ዐቢይ ትርክቶች የሚገነቡት በትውልድ ነው፤ አሁን አሁን እየታዩ ያሉ አለመግባባቶች አሉና ከዚህስ በኋላ እንዲህ አይነቶቹ አለመግባባቶች መፍትሔ እንዲኖራቸውና ከእኔነት ወደእኛነት የሚያመጡን የትርክት አይነቶችን ይህ ትውልድ መገንባት የሚችለው እንዴት ነው?**

**አየለ (ዶ/ር)፡-** ይህ በጣም ጥሩ ነጥብ ነው፤ በአሁኑ ወቅት እኔ እንዳስተዋልኩት ከሆነ እየነገሰ ያለው እኔነት ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ባልተገባ መንገድ የተዛባ ትርክት አምጪው በዝቷል፡፡ በአቋራጭ መንገድ የሚመጣው የተዛባ ትርክት ቶሎ ለመክበርና ሀብታም ለመሆን በሚያስቡ አካላት ነው፡፡ በእንዲህ አይነት መልኩ የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ስለመኖራቸው ምንም አይነት ጥርጣሬ የለውም፡፡ ሌላው ቀርቶ ነጻ አውጪዎች ነን በሚል በሚንቀሳቀሱበት ጊዜ አሠራራቸው ሁሉ የተመሠረተው ገንዘብ ላይ ነው። አሁን አሁን እንዲያውም የአንድ ነጻ አውጪ አባል ለመሆን ገንዘብ እስከመክፈል የተደረሰበት ሁኔታ እንዳለም በመነገር ላይ ነው፡፡

መገንዘብ ያለብን አንድ ነገር ቢኖር ብዝሃነት መመሪያችን እስከሆነ ድረስ ያ ብዝሃነት ሁላችንንም ሊያግባባን ይችላል፡፡ ብሎም የዴሞክራሲ ሥርዓትንም ሊያመጣ ይችላል፡፡ ስለራሳችን ስናስብ ስለጎረቤቶቻችን እና ከእኛ ቋንቋ ውጭ ስለሚናገሩትም ሆነ ከእኛ ኃይማኖት ውጭ ስለሚከተሉት አማኞች ወገኖቻችን ማሰብ ያስፈልጋል፡፡ ያንን ሳናደርግ ስንቀር ግጭት ይመጣል፡፡

የግጭት መንስዔ እንዳይኖር ማድረግ ተገቢ ነው። መቼም ቢሆ ኢትዮጵያ ውስጥ ‹‹ያለሁት እኔ ነኝ፤ ከእኔ በቀር ኢትዮጵያን ሊገዛት የሚችል ብሔር የለም›› ብሎ ማሰብ በጭራሽ የማያስኬድ ጉዳይ ነው፡፡ ከዚህ የተነሳ ይህን ተረድተን ኢትዮጵያ የሁላችን ሀገር እንደመሆኗ እንዴት አድርገን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ልንጠቀም እንችላለን? እንዴት ለሁላችንም የሚበጅ አስተዳደር ልንፈጥር እንችላለን? በሚል መንፈስ እስካተንቀሳቀስን ድረስ ግጭቶቹ ይቀጥላሉ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የጋራ ትርክት በአግባቡ ይገነባ ዘንድ የፖለቲከኛው ሚና ምን መሆን አለበት ይላሉ?**

**አየለ (ዶ/ር)፡-** የፖለቲከኛው ዋና ኃላፊነት መሆን አለበት ብዬ የማምነው ሰፋ ያለ አመለካከት እንዲኖረው ነው፡፡ ነገሮችን በሚያይበት ጊዜ ሰፋ አድርጎ ለማየት መሞከር አለበት፡፡ ከጠባብ አስተሳሰብ ራሱን ማራቅም ይጠበቅበታል፡፡

አንድ ፖለቲከኛ ወደፖለቲካው የመቀላቀሉ ምስጢር ሀብት ለማካበት ከሆነ በፖለቲከኛው ዘንድ የሚሰበከው ሥርዓትና አሠራሩም ሁሌም ሕዝብን ከሕዝብ ጋር ለማጋጨት ይሆናል፡፡ ይህ አመለካከት የሚመጣው ደግሞ ጠባብ አስተሳሰብ ካለው ፖለቲከኛ ነውና በዚህ ላይ በመሥራት አመለካከትን ማሻሻል የሚጠይቅ ይሆናል፡፡

ጠባብ በሆነ መንገድ ሁኔታዎችን ሁሉ የሚተረጉም ፖለቲከኛ ሀገርን ወደባሰ ችግር ውስጥ ይጨምራል እንጂ ለሰላምም ሆነ ለእድገት የሚሆን መፍትሔ ሊያመጣ አይችልም፡፡ ፖለቲከኛው አስተሳሰቡ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ሰፋ ያለ መሆን ይጠበቅበታል። የሕዝብን ፍላጎት ለመጠበቅ የሚችልም መሆን አለበት፡፡

በእርግጥ የሕዝብን ፍላጎት በተቻላቸው ሁሉ ለማስጠበቅና የሕዝብን መብት ለማረጋገጥ የሚጥሩ ፖለቲከኞች መኖራቸው የሚካድ አይደለም፡፡ እነርሱን ማበረታታት እና አቅም በፈቀደ ሁሉ ከእነርሱ ጋር መሥራት ይጠበቅብናል ባይ ነኝ፡፡

**አዲስ ዘመን፡- ኢትዮጵያን ወደሰላሙ ጎዳና ሊያሻግራት የሚችል ዐቢይ ትርክት ምን መሆን አለበት ይላሉ? በአሁኑ ወቅት አብሮነትን ለማጽናት አስፈላጊው ምንድን ነው?**

**አየለ (ዶ/ር)፡-** እኛ ኢትዮጵያውያን በጣም ሰፊ የሆነ ታሪክ ያለን ሕዝብ ነን፡፡ በዛ ታሪክ ውስጥ አንድ ሁልጊዜ መሠረታዊ የሆነው ነገር ቢኖር ነጻነታችንን አስከብረን ከትውልድ ትውልድ እየተሸጋገርን ዛሬ ላይ መድረሳችን ነው። ከዚህ የተነሳ ነጻ ሕዝብ መሆን መቻላችን አንድ ራሱን የቻለ ጉዳይ ነው፡፡

ከዚህ ጎን ለጎን ከጊዜ ወደጊዜ ለአንድነታችን መሠረት እየሆኑን የመጡ ትልልቅ ድልድዮች አሉን። እነዚህም ከአንድ ብሔርም ኃይማኖትም በላይ ሊያሳትፉ የሚችሉ ተግባራትንም ማከናወን የቻልንና የምንችል ሕዝብ ነን፡፡ እንደእነርሱ አይነት ትልልቅ የአንድነት ድልድይ ናቸው የሚባሉ ተግባራትን ለመፈጸም በሚደረገው ሒደት አብሮነት በጽኑ ገመድ መታሰር ይጀምራል፡፡ ሕዝብ ደግሞ የበለጠ የመተዋወቅ እድልም እንዲኖረው ያደርጋል፡፡ አካል ለአካል ተቀራርቦ ለመሥራት መነሳሳቱ አንዱ ከሌላው የሚማረውና የሚረዳውም ነገር እንዲኖር ያስችላል፡፡

ለአብነት ግልጽ የሆነ ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብን ሥራ ለመሥራት የተሰባሰበው ሰራተኛ ከመላ ኢትዮጵያ ሲሆን፣ የተውጣጣውም ከተለያየ ብሔር እና ኃይማኖት ነው። ይህ ሠራተኛ በሥፍራው እያሳለፈ ያለው ጊዜ ረዘም ያለ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አንዱ የሌላውን ማንነት የማወቅ እድሉ ሰፊ ነው። መተዋወቅ ሲኖር ደግሞ መከባበር አብሮ ይመጣል፡፡ መደጋገፍም ይከተላል፡፡

ይህን መሠረት አድርገን እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ አይነት አስርና አስራ አምስት ሥራ መሥራት ቢቻል እና በዚህ መልኩ ከሁሉም ኢትዮጵያውያን የተውጣጣ ሠራተኛ በሥራው ቦታ ቢሰማራ ሥራዎቹ ራሳቸው የሚያስተሳስሩን ይሆናሉ። በመካከላችን ያለውን አለመግባባትም ለማስወገድ መፍትሔ ይሆናሉ። ትልልቅ ሥራ በሕዝብ መካከል ያለውን መገፋፋት አርቆ ለአንድነት ድልድይ የሚፈጥር ይሆናል፡፡ እንዲህ አይነቱ ሥራ እንዲሠራ በተለይ በአመራር ደረጃ ያሉ ሕዝቡን ቢያበረታቱ መልካም ነው እላለሁ፡፡ ምክንያቱም እንደ ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዳሴ ግድብ ያለ ሥራ ዐቢይ ትርክት እንደመሆኑ ሕዝብን በሀገሩ ጉዳይ በአንድነት እንዲቆም ማድረግ የቻለ ነው፡፡

**አዲስ ዘመን፡- የሁልጊዜ ተባባሪያችን ረዳት ፕሮፌሰር አየለ ስለሰጡን ማብራሪያ ከልብ እናመሰግናለን፡፡**

**አየለ (ዶ/ር)፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## የአልባሳት አምራቾቹ ፈተና- የግብዓት እጥረት

**ሰሚራ በርሀ**

የሀገራችን የአልባሳት ዘርፍ መነቃቃት እየታየበት ነው፤ በተለይ የባህል አልባሳት እና የቆዳና ቆዳ ውጤቶች ምርቶች በስፋት እየተመረቱ ለገበያ እየቀረቡ ናቸው፤ በሀገር ውስጥ በሀገር ባህል አልባሳት አጠቃቀም ላይ የአመለካከት ለውጥ መምጣቱን ይጠቁማሉ፡፡ የአልባሳቱ ለተለያዩ አገልገሎቶች ተፈላጊ እየሆኑ መምጣት የምርቶቹን የሀገር ውስጥ ተፈላጊነት እየጨመረ መሆኑን እንደሚያመለክትም በዘርፉ የተሰማሩ አካላት ይገልጻሉ፡፡

በዘርፉ የተሰማሩ ዲዛይነሮችና ባለሙያዎችም ዘመኑን በሚመጥን መልኩ የተዋቡና ያማሩ አልባሳት እየሠሩ የተጠቃሚውን ፍላጎት ለማሟላት ጥረት እያደረጉ ይገኛሉ። የባህል አልባሳትን በተለያየ መልክ እና ዲዛይን በማዘጋጀት ለበዓላት ወቅት፣ ለሰርግ እና ለተለያዩ ፕሮግራሞች የሚሆኑ ልብሶችን እያዘጋጁ ለገበያ እያቀረቡ ይገኛሉ። በሰርግ፣ በሃይማኖታዊ በዓላት፣ ወዘተ. ወቅቶች የባህል አልባሳት በስፋት ተለብሰው የሚታዩበት ሁኔታም አልባሳቱ በተለያዩ ዲዛይኖች በስፋት እየተመረቱ ለገበያ እንደሚቀርቡ ያስገነዝባል፡፡

እነዚህ አልባሳት ከሀገር አልፈው በዓለም ጭምር እየታወቁ መምጣታቸውንም አምራቾቹና ዲዛይነሮቹ ይገልጻሉ፡፡ በኦንላይን፣ በፖስታቤትና በተለያዩ የዲጂታል አማራጮችና በመሳሰሉት በኩል ምርቶቻቸውን በውጭ ሀገሮች ለሚገኙ ደንበኞቻቸው ተደራሽ እያደረጉ መሆናቸውን አንዳንድ አምራቾችና ዲዛይነሮች ይጠቅሳሉ።

ቀደም ሲል እናቶች እና ጥቂት በሽማ ሥራ የተሠማሩ አካላት ብቻ ይሳተፉበት የነበረ ይህ ዘርፍ ዛሬ በርካቶች የሚሠማሩበት መሆን ችሏል፤ ይህም አልባሳቱ በስፋትና እንደሚመረቱና ተፈላጊነታቸው እየጨመረ እንደመጣ ይጠቁማል፡፡

አሁን የሀገራችን የባህል አልባሳት አምራቾች ችግር እየሆነ የመጣው የገበያ ችግር እንዳልሆነም ባለሙያዎቹ ሲገልጹ ይሰማል፤ ባለሙያዎቹ ችግሩ ለአልባሳት ምርቱ የሚያስፈልጉ ግብዓቶች ማግኘት አለመቻል ወይም እጥረት ነው፡፡ የባህል አልባሳት በዲዛይን አቅርቦት ደረጃም ይሁን በፍላጎት በጥሩ ሁኔታ እየተዋወቁ መሆናቸውን በአልባሳት ማምረት ሥራው የተሠማሩ ባለሙያዎች ጠቅሰው፣ የባህል ልብሶቹን ለመሥራት የሚጠቀሙባቸው አንዳንድ ግብዓቶች ላይ እጥረት እንዳለ ይጠቁማሉ፡፡



ዲዛይነር እጅጋየሁ ኃይለጊዮርጊስ በሙያው ላይ ከ30 ዓመት በላይ ልምድ አላት፤ «እጅግ ጥበብ» የተሰኘ ድርጅት አቋቁማ የተለያዩ የባህል አልባሳትን ትሠራለች፡፡ በዘርፉ በገበያው እና በተጠቃሚዎች ዘንድ ጥሩ ፍላጎት እንዳለ የምትናገረው እጅጋየሁ፤ የባህል አልባሳትን ለመሥራት የሚውሉ የአንዳንድ ግብዓት እጥረት መኖሩ ለገበያ የሚቀርቡ የባህል አልባሳት ዋጋ የማይቀመስ እንዲሆን እያደረገ መሆኑን አመልክታለች፡፡

እሷ እንደምትለው፤ በዘርፉ የጥሬ እቃ ግብዓት እጥረት ያለ ሲሆን፣ ቁልፍ ፣ ክር ፣ ዚፕ እና ላስቲክ ፣ የልብስ ገበር በሽመናው ወቅት ደግሞ ድርና ማግ የመሳሰሉት ግብዓቶች እጥረትና ችግር በስፋት ይታያል፡፡ እነዚህን ምርቶች በሀገር ውስጥ የሚያመርቱ አምራቾች ዲዛነሮቹ በሚፈልጉት አይነትና መጠን ምርቶቹን አለመያዛቸው፣ አንዳንድ አምራቾች ደግሞ ለገበያ በሚያቀርቡበት ወቅት የሚያስቀምጡት የመጠን ገደብ እና አይነት ውስን መሆን ከሀገር ውስጥ እንዳይገዙ እንዳደረጋቸው ዲዛይነሯ ገልጻለች፡፡

ባለሙያዎቹ ከዚህ ቀደም እነዚህን መሰል ግብዓቶች ከቻይና፣ ከህንድ እና ከቱርክ ያስመጡ እንደነበር አስታውሳ፣ በአሁኑ ሰዓት በውጭ ምንዛሪ እጥረት ምክንያት ባለሙያዎቹ ግብዓቶቹን ማምጣት አልቻሉም በማለት አመልክታለች። ከውጭ ከሚያመጡ ነጋዴዎች መግዛት ዋጋቸው በጣም ከባድ መሆኑን አንስታለች፡፡

ዘርፉ ላይ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ ይቻል ዘንድም ከውጭ ሀገር ምርቶች በሚገቡበት ወቅት አምጪዎች ላይ የሚጣለው ታክስ ማስተካከያ እንዲደረግበትም ዲዛይነሯ ጠይቃለች፡፡ ግብዓቶቹን በሀገር ውስጥ በስፋት ማምረት የሚቻልበት ሁኔታ መፈጠር እንዳለበትም ጠቁማለች፤ እነዚህን ግብዓቶች የሚያመርቱ የሀገር ውስጥ አምራቾች በቀጥታ ከባለሙያዎች፣ የባህል ልብስ ዲዛይነሮች ጋር የሚገናኙበት እድል እንዲፈጠርም የመፍትሄ ሃሳብም ዲዛይነር እጅጋየሁ ጠቁማለች፡፡

የኢትዮጵያ ኢንተርፕራይዝ ልማት ኢንቨስትመንት ፕሮሞሽንና የገበያ ልማት መሪ ሥራ አስፈጻሚ አቶ ስዩም ውጁራ፤ በገበያው ላይ የሚታየው የግብዓት እጥረት በሁለት መንገድ እንደሚከሰት ይገልጻሉ፡፡ በሀገር ውስጥ በፋብሪካ ውስጥ የሚመረቱ የጨርቃጨርቅ ምርቶች ላይ እጥረቱ መኖሩን ጠቅሰው፣ ከዚያም ባለፈ ባለሙያዎች ከውጭ የሚያስገቧቸው ምርቶች ወደ ሀገር ውስጥ በበቂ ሁኔታ እንዲገቡ አልተደረገም ሲሉም ገልጸዋል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ እነዚህን በጨርቃጨርቅ አልባሳት ላይ ያሉ አስፈላጊ የሆኑ ግብዓቶች ከውጭ የማስገባት ሥራን የሚሠሩት ጥቂት ናቸው፡፡ ምርቶቹ ወደ ሀገር ውስጥ ከገቡ በኋላ አላስፈላጊ ክምችት ተደርጎባቸው በውድ ዋጋ ለገበያ የሚቀርቡበት ሁኔታም አለ፤ በዚህ ጊዜም በነጋዴዎች እና ምርቶቹን በሚፈልጉት ባለሙያዎች መካከል የሚገባ ደላላ እጥረቱ እንዲፈጠር አንዱ መንስኤ እየሆነ ነው። በኢንተርፕራይዞች በኩልም ይህንን ችግር ለመቅረፍ በጥምረት ተጠናክሮ መሥራት ላይ የዝግጁነት ማነስ ይስተዋላል፡፡

ተቋሙ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ባለሙያዎችን በማቀናጀት በሀገር ውስጥ የሚመረቱና እጥረት የሚታይባቸውን ግብዓቶች በቀጥታ ከፋብሪካዎች የሚያገኙበትን መንገድ ለመፍጠር እንደሚሠራ ገልጸው፣ ከውጭ የሚመጡትን ደግሞ በበቂ ሁኔታ ከውጭ የሚመጡበትን መንገድ ለመፍጠር እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

ከዚህም በተጨማሪ የኢንዱስትሪ ግብዓቶችን የሚያቀርበው የኢትዮጵያ ኢንዱስትሪ ግብዓቶች ልማት ድርጅት እነዚህን ግብዓቶች ለባለሙያዎች ለማቅረብ እየሠራ መሆኑንም አስታውቀዋል፡፡ በቅርቡም አዲስ ፕሮጀክት ቀርጾ በዘርፉ ተሰማርተው ለሚሠሩ እና እጥረት አለብን ብለው ላመለከቱ ባለሙያዎች ግብዓቶቹን ከውጭ የሚያመጡበትን መንገድ ለማመቻቸት ጥረት እያደረገ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

ለዚህም ከኢትዮጵያ ልማት ባንክ የ25 ሚሊዮን ዶላር ብድር መመቻቸቱን ጠቅሰው፣ ተቋማቱ የሚፈልጓቸውን ግብዓቶች ከውጭ የሚያመጡበትን መንገድ እያመቻቸ ይገኛል ብለዋል፡፡ ይህ ተግባር ቀጣይነት ያለው ስለመሆኑም ነው ሥራ አስፈጻሚው ያረጋገጡት፡፡

# ትዝብት/ ማረፊያ

## የአጥብቆ ጠያቂዎች ነገር...

**እየሩስ ተስፋዬ**

ከቀናት በአንዱ ነው፡፡ ከጓደኛዬ ጋር ለቅሶ ቤት ተገኝተናል፡፡ ገና ወደ ድንኳኑ ስንገባ እጄን ጎተት አደረገችኝ፡፡ ለካ የምናውቃትን አንዲት ሴት በቅርብ ርቀት ተመልክታት ወደ እርሷ እንዳንሄድ ለመከልከል ኖሯል፡፡ ምነው? የሚለውን ጥያቄ ገና ከማስከተሌ፤ በድንኳኑ ፊት ለፊት ባየችው ክፍት ወንበር ላይ በፍጥነት ተቀመጠች፡፡ እኔም እንድቀመጥ ጋበዘችኝ፡፡ የማይመች ቦታ ስለሆነ ደጋግሜ ‹‹ለምን እዚህ ጋር ?›› ስል ጠየቋት፡፡ ‹‹እኔ ከሷ ጋር መቀመጥ አልፈልግም፣ በጥያቄ ታሰለቸኛለች›› የሚል ምላሽ ሰጠችኝ፡፡

በአንድ ሰው ምክንያት ምቾት ማጣትን የደረሰበት ያውቀዋል፡፡

የማሕበራዊ ሕይወት አንዱ ከአንዱ እንዲነጋገር መንገድ ከፋች ነው፡፡ ማሕበራዊ ሕይወቱ የሚጀመረው ከሥራ ቦታ ወይም ከመኖሪያ አካባቢ ሊሆን ይችላል። ሰዎች ስለሰዎች የሚያውቁት አንድም ሌሎች ከሚነግሯቸው ተነስተው፤ አልያም ጥያቄዎችን በመጠየቅ ሊሆን ይችላል፡፡

አንዳንዶች በአንድ አጋጣሚ ያገኙትን ሰው በጥያቄ ማጣደፍ ልማዳቸው ነው፡፡ በጥያቄ የሚያሰለቹ ሰዎችን ገና እንዳገኙን አገባህ? ወለድክ? ደገምክ? ምን ሆነህ ነው ያረጀኸው? ሚስትህ ምንድ ነው የምትሠራው? ልጅህን ትምህርት ቤት አስገባሃት? ሲሉ ያዋክባሉ። ድንገት ተጠያቂው ሚስቴ ‹‹ሥራ የላትም›› የሚል ምላሽ ከሰጠ ደግሞ እንዴት በዚህ ጊዜ ቤት ትሆናለች? በማለት የሰውን ቤት ጓዳ ጎድጓዳ ሚስጥር ለማወቅ የማይፈነቅሉት የለም፡፡

ችግሩ እንዲህ አይነት ሠዎች ችግራቸው ቢነገራቸው ለመለወጥ በጣም ቀርፋፎች መሆናቸው ነው፡፡ ምክንያቱም ስለሰው እንጂ ራሳቸው ለመስማት ፍላጎቱም፣ ወኔውም የላቸውምና ፡፡

እነርሱ ስለ ሰው ሲወራ በጣም ሰፊ ገለጻ በመስጠት የሠዎችን ትኩረት በቀላሉ መሳብ ይችላሉ። ነገር ግን ምን ያህል የሌሎችን ግላዊ ነጻነት እየገፈፉ ስለመሆናቸው ፈጽሞ ማሰብ አይፈልጉም፡፡ ወይም ነገሬ ነው አይሉትም። አንዳንዶቹ ደግሞ ለወሬ ፍጆታ እንኳን ባያውሉት ለምን እንደሆነ ሳይገባቸው አሰልቺ ጥያቄዎችን ከመጠየቅ አይቦዝኑም፡፡

ብዙ ሰዎች የሚዘነጉት ነገር ቢኖር የሚጠየቁ እና የማይጠየቁ ጥያቄዎች መኖራቸውን ነው፡፡ ሁሌም ቢሆን ሰዎች በፈቃደኝነትና እንደ ሁኔታዎች አስገዳጅነት ስለራሳቸው ቢናገሩ መልካም ነው፡፡ አንዳንዶች የማያገባቸውን በመጠየቅ ስለሚያሰለቹ ብዙ ሰዎች ከእነርሱ መሆንን አይፈልጉም፡፡ በአስገዳጅ ሁኔታ ከነዛ ሰዎች ጋር ቢገጣጠሙ እንኳን ውሏቸው በጭንቀት የተረበሸ አድርገው ይቆጥሩታል፡፡

እነዚህ ሰዎች ጥያቄ በመጠየቅ ብቻ አወቅን ያሉትን ሁሉም እንዲያውቀው ከሁሉም ቤተኛ ይመስሉ እንጂ አይደሉም፡፡ እንደውም በተቃራኒው በብዙ ሰዎች ዘንድ ይሸሻሉ፡፡ ጠይቀው ያወቁትን ሁሉም እንዲያውቀው ስለሚያጋሩም በሰዎች ዘንድ ክብር አይሰጣቸውም፡፡ ሁሌም እንደ ምስጢር አባካኝ ይቆጠራሉ፡፡

አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ጥያቄያቸው ከንጽጽር ጋር ይያዛል፡፡ የራሳቸውን ነገር ከሌላው ጋር አወዳድሮ ለማሳነስም ይሁን ለማግዘፍ ይጠቀሙበታል፡፡ ለምሳሌ ‹‹ልጅሽ ስንት ወሩ ነው? ወይም ስንት አመቷ ነው? ሲሉ ይጠይቁና መልሱን ተከትሎ እንዲህ ያደርጋል ? እንዲህ ይሞክራል? ሲሉ ይቀጥላሉ። ‹‹የእኔ ግን እንዲህ ማድረግ ይችላል፡፡ ‹‹ያንቺስ እንዲህ ትሆናለች? እንዴ እንዲህማ ካላደረገች በጣም ዘግይታለች›› ይላሉ፡፡ ያስከትሉናም ለምን ወደ ህክምና አትወስጃትም እያሉ ሰው ያላሰበውን እንዲያስብ በማድረግ ጭንቀት ውስጥ እንዲገባ ያስገድዳሉ፡፡

ምናልባትም ይህ ምሳሌ በልጅ ሆነ እንጂ ራሳቸውን ከእኛ ጋር በማነጻጸር ጥርጣሬ ላይ እንድንወድቅ ያደርጉናል፡፡ ታዲያ እንደነዚህ አይነት ሰዎች በድርጊታቸው ምንም ይሉኝታ አያውቁም። እንዲህ አይነቶቹ ጠያቂዎች በማያልቀው ጥያቄያቸው እያታከቱ ሰዎች የረሱትን ሕይወት ዳግም በመቀስቀስ ወደ ኀዘን እና ድባቴ ውስጥ እንዲገቡ ያደርጋሉ፡፡ የትምህርት ቤት ጓደኛችን ለአባቷ ያላት ፍቅር በጣም የተለየ ነበር፡፡ አባቷ በድንገተኛ አደጋ ነበር ያለፉት፡፡ ኀዘን በጣም ጎድቷታል፡፡ ታዲያ ይህች ጓደኛችን ወደቀደመው ማንነቷ ለመመለስ ብዙ ጊዜ ፈጅቶባታል፡፡ በወቅቱ እኛ እንዳይሰማት በማሰብ ተሳስተን እንኳን ስለራሳችን አባት አናወራም፡፡

በአንድ አጋጣሚ ግን ፈጠን ያለች ጓደኛ ተዋወቅን። በቃ! የማትጠይቀው፣ የማታነሳው ጉዳይ የለም። ስለራሷ አባት እስኪበቃን እና እስኪሰለቸን ነገረችን። ቀጥላ ደግሞ ጥያቄዋን ጀመረች። እንደፈራነው ትኩረቷ ጓደኛችን ላይ አረፈ፡፡ ‹‹አባትሽ ምንድነው የሚሠራው?›› ልጅቷ የምትሆነው ጠፋት፡፡ ፈጣኗ ጓደኛችንም ‹‹አው በሕይወት የለም? ይቅርታ ›› የሚል አጭር ምላሽ ሰጠች፡፡ አዎ እንዲህ ያሉ ሰዎች የማይነካ ጉዳይ በመነካካት፤ የተዳፈነው እሳት ከቆሰቆሱ በኋላ ምላሻቸው ከንፈር መምጠጥ ይሆናል፡፡ ምን ዋጋ አለው ከንፈር መምጠጥ? ምን ዋጋ አለው ልብን ካደሙ ካቆሰሉ በኋላ ‹‹በጣም አዝናለሁ፡፡›› ብሎ ምላሽ መስጠት ?

ነገርን ነገር ያነሳዋል እንዲሉ በአንድ አጋጣሚ ራዲዮ እየሰማሁ ፕሮግራም አዘጋጆቹ ርዕሰ ጉዳያቸው ሰዎች ስለሰዎች ካላወሩ የሰዎች ንግግር ውስንነት ያጋጥመዋል የሚል አይነት ሆነ፡፡ አንደኛው ጋዜጠኛ እንዲህ አለ። ‹‹በእኛ ቤት ውስጥ አንድ ሙከራ ሞከርን፣ እርሱም ማንም ሰው ‹‹ስለ ሰው›› እንዳያወራ ነበር፡፡›› ይህን ከመነጋገራቸው በፊት ግን ቤታቸው በጨዋታ ሲደምቅ፣ ሲሞቅ ቆይቷል፡፡

ከደቂቃዎች በኋላ ያጋጠመው ግን ተቃራኒ ነበር፡፡ ሁሉም ለረዥም ጊዜ በዝምታ ተዋጡ፡፡ ቆይተው ጉዳዩን ሲረዱ ለካ በቤታቸው በአብዛኛው የሚያወሩት ስለ ሰዎች ነበር፡፡ ይህ በጥሩም ይሁን በመጥፎ ሊሆን ይችላል፡፡ ወሬዎቹ የሚደምቁት ደግሞ ከንግግር ልውውጥ በዘለለ በጥያቄ ጭምር ታጅቦ ነው።

በእርግጥ ለሁሉም ነገር ልክ እና ቦታ አለው። ‹‹ካለመጠየቅ ደጃዝማችነት ይቀራል›› የሚባለው አባባል ያለቦታው ሲውል ትርጉም አልባ ይሆናል፡፡ ሰዎች አይነኬ የሚሉት የራሳቸው ነገር ይኖራቸዋል። እንዲህ ማድረግ መብታቸው ነው፡፡ እንደውም አንዳንዶቹ በእንዲህ አይነቶቹ ሰዎች የተነሳ ሰው መቅረብ አይፈልጉም፡፡ በራሳቸው ዓለም ብቻ እንዲኖሩና ሽሽትን እንዲመርጡ ያስገድዳቸዋል። እናም ሰው መንገር ሲፈልግ ይናገር። ብዙ ሰው ማስታወስ የማይፈልገው የኋላው እና የቅርብ ታሪክ አለው፡፡ ጥያቄን ለትክክለኛ ጠያቂዎች እንተውላቸው። ዝም ብሎ ከመጠየቅ ‹‹የምጠይቀው ጥያቄ ተገቢ ነው?›› ሲሉ ማሰብ ምን ይከብዳል?

## ነፃ ሃሳብ



(ጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፣ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

# የስብሰባችን ውሎ ኢንቬንቶሪ

### ውሎ ሲያድር ባህል ሆኖብን ይሆን?

ይህ ጸሐፊ ከ2000 እስከ 2010 ዓ.ም ድረስ ለአሥር ዓመታት ያህል የተካፈላቸውን ስብሰባዎችና ሴሚናሮች፣ ምክክሮችና አውደ ጥናቶች በአጭር በአጭሩ በዐውደ ዕለቱ መመዝገቢያ ማስታወሻው ላይ የዜና መዋዕሉን ማስፈርን "ልማዱ" ለማድረግ ሞክሮ ነበር፡፡ ከዚሁ ልማዱ ጎን ለጎንም በተካፈላቸው "መድረኮች" ላይ የተሰጡትን የማንነት መገለጫ የስም ባጆች ከነማንጠልጠያቸው፣ እኛ ተሰብሳቢዎች የተንቆጠቆጥንባቸውን የአንገት ልብሶችንና (ስካርፎች) ባህላዊ አልባሳትን በሙሉ በግሉ "አርካይቭ" በአግባቡ ለማስቀመጥ ሞክሯል፡፡

ከሚሊኒየም ክብረ በዓላት፣ እስከ የሰንደቅ ዓላማ ቀን አከባበር፣ ከታላቁ ህዳሴ ግድብ እስከ የፐብሊክ ዲፕሎማሲ ተሳትፎው፣ ከደራሲያን ማኅበር ዝግጅቶች እስከ መንግሥታዊ ጥሪዎች፣ ከብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በዓላት እስከ የማኅበራት የይገኙልን ጥሪ፣ ከፖለቲከኞች ሸንጎ ተጋባዥነት እስከ የቲንክ ታንክ ቡድኖች አስተባባሪነትና ተሳታፊነት፣ ከመጻሕፍት ምረቃ ሥነ ሥርዓቶች እስከ ደረጃቸው "ከፍ ያሉ ስም አይጠሬ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ" ጉባዔዎች ወዘተ. ለመገኘት ዕድል አጋጥሞታል፡፡ የስብሰባውና የጥሪው ዓይነት ተዘርዝሮም ይሁን ተቆጥሮ በቀላሉ የሚዘለቅ ስላይደለ እዚሁ ላይ መግታቱ ይበጃል፡፡

ከዝርዝሮቹ በማስከተል ለሙግት መቅረብ ያለበት መሠረታዊ ጥያቄ የተጠቃቀሱት ስብሰባዎችም ሆኑ ዐውደ ጥናቶች፣ ምክክሮችም ሆኑ ግብዣዎች ለአዘጋጆቹ ተቋማት፣ ለተጋባዦቹና ለታዳሚዎቹ ከፍ ስናደርገውም ለሀገር ለውጥና መሻሻል ያስገኙት ትሩፋትና ጠቀሜታ ምን ነበር?" የሚል ሊሆን ይገባል፡፡ እርግጥ ነው ያኛውና ይሄኛው ብለን ባንዘረዝርም የተወሰኑት መርሃ ግብሮች በዛሬ ዐይን ሲፈተሹ ጥቂቶቹ ፍሬያቸው በግልጽ የሚታይ፣ ውጤታቸውም ጎምርቶ እንዳማረበት መመስከሩ አግባብ ነው ማለት ብቻ ሳይሆን እውነቱን ባንመሰክር "ኀሊና ራሱ" በትዝብት ልምጭ ይቀጣን ይመስለናል።

ችግሩ ልክ እንደ ቅዱስ መጽሐፉ ታሪክ ሆኖ ከሆነ ነው፡፡ ምሳሌውን እናስታውስ "እነሆ አንድ ገበሬ ዘር ሊዘራ ወጣ፡፡ እርሱም ሲዘራ አንዳንዱ በመንገድ ዳር ወደቀ፤ ወፎችም መጥተው ለቀመው በሉት። አንዳንዱም ዘር አፈሩ ስስ በሆነ ድንጋያማ መሬት ላይ ወደቀ፤ የዳበረ አፈር ስላልነበርም ወዲያው በቀለ፤ ፀሐይ በወጣ ጊዜ ጠወለገ፤ ሥርም ስላልነበረው ደረቀ። አንዳንዱም ዘር በእሾህ መካከል ወደቀ፤ እሾሁም ቡቃያውን አንቆ አደረቀው፡፡ ሌላው ዘር በመልካምና ታርሶ በለሰለሰ መሬት ላይ ወደቀ፤ ፍሬም አፈራ፤ አንዱ መቶ፣ አንዱ ስድሳ፣ አንዱም ሠላሳ፣ ፍሬ አፈራ፡፡ የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ" (ማቴ. 13፡3 -9)፡፡

በመላው የሀገሪቱ ግዛት በቀበሌም ይሁን በወረዳ፣ በዞንም ይሁን በክልል፣ በድንኳን ውስጥም ይሁን በዳስ ውስጥ፣ በዛፍ ጥላ ሥርም ይሁን በመስክ፣ ደረጃቸውን በጠበቁ አዳራሽ ውስጥም ይሁን በተንደላቀቁና በከዋክብት ብዛት በተሰየሙ ሆቴሎች ውስጥ፣ በዘብ በሚጠበቁ የጉባዔ መሰብሰቢያዎች ውስጥም ይሆን በተመረጡ ቦታዎች እስከ ዛሬ የተሰየሙትና ምክክር ወይንም ትምህርት፣ ሪፖርት ወይንም መመሪያ የተላለፈባቸው ስብሰባዎች ያስገኙት ሀገራዊ ውጤት ምን ነበር? ደፍረን ልንጠያየቅ፣ ጨክነን ልንተራረም ጊዜውም ወቅቱም ግድ የሚል ይመስለናል፡፡

ስለ ሰላም የተሰበኩትና የተዘመሩት የጉባዔ ድምጾቻችን ምን ውጤት አስገኙልን? ስለ አብሮነት የተመካከርንባቸውና ቃል የገባንባቸው የአቋም መግለጫዎችስ የት ደረሱ? ለኢትዮጵያ ሁለተንተናዊ እድገትና ልማት ተስፋ ይሆናሉ ያልናቸውና በኪዳን ጭምር የተማማልንባቸው ተስፋዎች ፍሬያቸው ስለምን ደምቆ ሊወጣ አልቻለም? የስብሰባዎቻችንንና የዐውደ ጥናቶቻችንን ኢንቬንቶሪ እንደ ሀገር ወደ ኋላ መለስ ብለን መገምገሙና መፈተሹ ብልህነት ብቻ ሳይሆን ወደ ብሔራዊ ችግሮቻችን መፍትሔም ሊያቀርበን የሚችል ይመስለናል፡፡

"ይህን ያህል ይሆናል" የሚል ቁጥር ለመጥቀስ ለምንቸገርባቸውና ለልኬትም ከሚያዳግቱ ስብሰባዎች፣ ሴሚናሮች፣ ዐውደ ጥናቶች፣ ምክክሮችና ውሎዎች የተገኙት ሀገራዊ ትሩፋቶችና ፍሬዎች በርግጡ ለየትኞቹ ችግሮቻችን መፍትሔ ሆነው ታደጉን?" ከሚለው መሠረታዊ ጥያቄ ጎን ለጎን እና ዛሬም ተጋግለውና ተነባብረው መሰብሰቢያ አዳራሽ እስኪጠፋ ድረስ በገፍ እየተተገበሩ ላሉት ሀገራዊ ስብሰባዎችና ጉባዔዎች ምን ያህል ገንዘብ እንደ ጅረት ፈስሶ ነበር? ወይንም እየፈሰሰ ነው? ያ ለስብሰባ ይወጣ የነበረው ረብጣ ሀብት ለሌላ ልማት ቢውል ምን ያህል ትምህርት ቤቶች፣ የጤና ተቋማትና የግብርና ትራክተሮች ይገዛ ነበር? በጉባዔ ማጠቃለያዎቹ ልዩ መርሃ ግብሮች ላይ በልዩ ሁኔታ ለሚደገሰው የ"ዋንጫ ኖር!" ፌሽታ (toast ‹raising glass› when drinking እንዲሉ ባህር ማዶኞች)፤ ምን ያህል ነዋይ እንደ ምግብ መጠጡ በገፍ ፈሰሰ? ለትልቁም ለትንሹም የስብሰባና የጉባዔ ማድመቂያ እየተባሉ ታዳሚዎች አንገት ላይ የሚሸመለሉት የአንገት ልብሶች፣ የባህል አልባሳት፣ ኮፍያዎች፣ ቦርሳዎች፣ የማስታወሻ ደብተሮችና የጽሕፈት መሣሪያዎች ዋጋቸው ቢተመን በስንት ሚሊዮን ብር ሊገመት ይችል ይሆን? በሆድ ይፈጀው! ቁጭት ብናልፈው ይበጃል፡፡

ሥልጡን ሀገራትና ተቋማት የስብሰባቸውን የፍሬያማነት ውሎ (Meeting Effectiveness Inventory - MEI) የሚገመግሙበት የራሳቸው ስልትና አተገባበር አላቸው፡፡ አጫጭር መርሃ ግብሮች እንደተጠናቀቁ ወዲያው "እጅ በእጅ" ግምገማ ለማድረግ ብቻም ሳይሆን በቀዳሚ ጊዜያት የተከናወኑ ስብሰባዎችና ዐውደ ጥናቶች ወይንም የምምክር ጉባዔዎችም የሚፈተሹት ታስቦባቸውና ምን ትርፍ፣ ምን ኪሳራ እንዳስከተሉ በተገቢ የጥናት ወንጠፍት እየተበጠሩና እየተጠኑ ነው፡፡ ያለበለዚያ ያለፈው ሳይፈተሽ ሌላ ጉባዔ ላይካሄድም ይችላል፡፡

ገንዘብ ጊዜ እውቀት የሚፈስባቸው የሀገራችን ዘርፈ ብዙ ስብሰባዎችና ጉባዔዎችስ በአግባቡ ይገመገሙ ይሆን? ለስብሰባዎችና ለውሎ አበል የሚከፈሉ ወጭዎችሽ በህሊና ዳኝነትና በተዘረጋው የየተቋማቱ የፋይናንስ ማጣሪያ ውስጥ በአግባቡ እየተጣሩ ያልፉ ይሆን? "ተው ቻለው ሆዴ!" አለ የሀገሬ አንጎራጓሪ!

"የሚሰማ ጆሮ ያለው ይስማ" በሚል "የአጋኖ ድምጸት" ተደምድሞ ወደ ተጠቀሰው የላይኛው የቅዱስ መጽሐፍ ምሳሌ ዳግም መለስ ብለን ጥቂት ማነጻጸሪያ እናክልበት፡፡ በዚህ ጸሐፊ እምነት የአብዛኞቹ የሀገራችን ስብሰባዎችና ጉባዔዎች ተገቢውን ፍሬ ሊያፈራ ያልቻሉበት ምክንያቱ አንድም፡- "በጭንጫ ድንጋይ ላይ ተዘርተው እንደሆንስ?"፣ "አንድም ለም ባልሆነ መሬት ላይ ተዘርተውስ ከሆነ?"፣ "አንድም በመንገድ ላይ ተዘርተው ወፎች ለቅመዋቸው ቢሆንስ?"፣ "አንድም በሾህ ታንቀው እንደሆንስ?" አንድምታችንን ከዚህ በላይ ዘርዘር አድርጎ ማስፋቱ ተገቢነት አይኖረውም፡፡ "ስለምን?" ተብሎ ቢጠየቅ ምሳሌው የተደመደመው "ጆሮ ያለው ይስማ!" በሚል አማራጭ ስለሆነ መቀበል ያለመቀበል የአንባቢውና የሰሚው ድርሻ ነው፡፡

የብዙ ሀገራት ድርጅቶችና መንግሥታዊ ተቋማት "መደበኛ" የሚሰኙ የስብሰባ ባህሎቻቸውን ቴክኖሎጂው አግዟቸው ወደ ዘመናዊነት ካሸጋገሩ ሰንበት ብሏል፡፡ ይሄው የቴክኖሎጂ አተገባበር የሚገለጸው እንደሚከተለው ነው፡፡ "A virtual meeting is a form of communication that enables people in different physical locations to use their mobile or internet connected devices to meet in the same virtual room."

ከላይ በተጠቀሰው ዘመን ወለድ ቴክኖሎጂ የተደገፉ ስብሰባዎችም ሆኑ ጉባዔዎች የሚካሄዱት የቦታ ርቀትና ቅርበት ሳይገድባቸው እያንዳንዱ ታዳሚ በዚያው ባለበት ሆኖ ስለሚወያይ የጋራ መሰብሰቢያ አዳራሽና መድረክ የማያስፈልግበት ደረጃ ላይ እየተደረሰ ይገኛል፡፡

ይህ ማለት ግን ስብሰባዎች በሙሉ መካሄድ ያለባቸው በዚህ ቴክኖሎጂ አማካይነት ብቻ ነው ማለት እንዳልሆነ ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ቢባልስ ማን ሊቀበለን!? እንዳስፈላጊነቱ በአካል እየተገናኙ መሰብሰብ ጭራሹኑ አስፈላጊ አይደለም ተብሎ "ውጉዝ ከመ አርዮስ" የሚል አንድምታም ሊሰጠው እንደማይገባም አበክረን እናሳስባለን፡፡

ከላይ ስለ ተጠቀሰው የቴክኖሎጂ ጥበብ ብዕረ መንገዳችንን አንዳንድ ጉዳዮችን ጠቅሰን ብናልፍ ይጠቅም ይመስለናል፡፡ ቨርችዋሉ የርቀት መገናኛ ዘዴ የሚያገለግለው ለበርካታ ማሕበራዊ ጉዳዮች ጭምር ነው፡፡ እንደ ቀደምት ዘመናቱ ልምምድ አንድ የተመሰገነ የዩኒቨርሲቲና የአንድ ሀገር ታዋቂ የኮሌጅ ፕሮፌሰር በተለያዩ ሀገራት ለሚገኙ ተማሪዎች ትምህርታዊ ገለጻ ለመስጠት የግድ የአውሮፕላን ቲኬት ቆርጦ ወይንም ረዥም ርቀት ነድቶም ሆነ ተጓጉዞ ተማሪዎቹ ባሉበት ኮሌጅ ውስጥ እንዲገኝ ላይጠበቅበት ይችላል፡፡ እዚያው ባለበት ሀገርና ቦታ ሆኖ በቴሌ ኮንፍረንስ ትምህርታዊ ገለጻውን ለተማሪዎቹ ሊሰጥ ይችላል፡፡ ማስተማር ብቻ ሳይሆን ተማሪዎቹ ትምህርቱ ገብቷቸው እንደሆነም ይጠይቃል፣ እርሱም በተማሪዎቹ ጥያቄ ይቀርቡለታል፤ ፈተናም ይፈትናቸዋል፡፡

በርቀት ያሉ ሕሙማንና ለመጓጓዝ አቅም የሌላቸው ታካሚዎችም በተለያዩ ሀገራት በሚገኙ ዶክተሮች አማካይነት በዚሁ ዘመናዊ የቪዲዮ ኮንፍራንስ ሕክምና ሊሰጣቸው ይችላል፡፡ ታላላቅ ዓለም አቀፍና አህጉር አቀፍ ስብሰባዎችም እንዲሁ በቨርቹዋል ዘዴ ሲካሄዱ እየተመለከትን ነው፡፡

"ልማድ ውሎ ሲያድር ባህል ይሆናል" ሆኖብን እኛ ግን ዛሬም ድረስ እንደ ሀገር "ከአፍቅሮተ ስብሰባ" ሱሳችን ነፃ መሆን ተስኖናል፡፡ ስብሰባ ከሌለ ብርድ ብርድ እያለ የሚያንዘረዝረው፣ "ለምን ስብሰባ አይጠራም?" እያለ የሚያቁነጠንጠው የሀገሬ "የስብሰባ ቁራኛና" ልክፍተኛ ብዛቱና አበዛዙ ይህ ልኩ የሚባል ዓይነት እንዳይደለ ለመመስከር አገልግሎት እንዲሰጡ የተቋቋሙትን መንግሥታዊ ተቋማት ብቻ መፈተሹ በቂና ከበቂ በላይ የሆነ ማስረጃ ይሆነናል፡፡

ጎበዝ! እንዴት ነው መላው? ይህ እንደ ዘጠና ደቂቃ የእግር ኳስ ጨዋታ የባከነ ጊዜ ሊሰጠው የማይችለው ሕይወታችን እንኳንስ "በስብሰባ ታጅሎ" ይቅርና ያቺው መደበኛ የሥራ ጊዜ እንኳን ምርታማና ትርፋማ እንዳትሆን መጨቆን ምን ይሉት አባዜ ነው፡፡ "እንኳንስ ዘንቦብሽ..." እንዲል ሀገራዊ ብሂል፤ የስብሰባ ሱሳችን ገና ሳይሰክን "በቡሃ ላይ ቆረቆር" እንዲሉ አብዛኛው ሠራተኛ "በሶሻል ሚዲያ" ላይ ተጠምዶ ሥራውን ቸል ባለበት ዘመን ሀገር እንዴት "ሀገር" ሆና ልትቀትል ትችላለች?

በሥልጡን ሀገራት ባህል እንደሆነው ሁሉ በእኛ ሀገርም የሥራ ጠባያቸው ከእጃቸው ላይ ስልክ እንዳይለይ ከሚፈቅዳላቸው የሥራ መሪዎች በስተቀር ለምን እያንዳንዱ ሠራተኛ የእጅ ስልኩን አስቀምጦ ወደ ሥራው እንዲሠማራ አይደረግም? በሥራ ሰዓት ተገልጋዮችን እያስለቀሱ በእጅ ስልካቸው ላይ ቲክ ቶክ፣ ዩ ቲዩብና ፌስ ቡክን የሙጥኝ በማለት በእንጀራቸውና በሙብታችን ላይ በሚሳለቁት ላይስ ስለ ምን ርምጃ አይወሰድም? ርምጃ መውሰድ ሲገባቸው ርምጃ በማይወስዱትስ ላይ ርምጃ የሚወሰደው መቼ ይሆን?

ሀገሬን የውጥር እንደ ያዟት ፈተናዎች አባዛዝ ቢሆን ዛሬ ዛሬ ብዙው የህልውናችን ምሶሶ ተናግቶ "በነበር" በተዘከርን ነበር፡፡ መቼም ድህነቱና መከራው የሕይወታችን አንዱ ክፍል እንዲሆን የፈቀድንለት የስብሰባችን ባህል በቀዳሚነት ይጠቀስ እንጂ እጅግ በርካታ ከሆኑ ትብታቦች ገና ነፃ ለመውጣት ብርታት አላገኘንም፡፡

"ሰው መናገር ከሚችለው በላይ ነገሮች ሁሉ አድካሚ ናቸው፡፡...የነበረው ነገር እንደ ገና ይሆናል፣ የተደረገውም ተመልሶ ይደረጋል" (መክብብ 1፡8 - 11) እንዳለው ጠቢብ፤ ብዙው የእኛ ነገር "ውሃ ቅዳ፤ ውሃ መልስ" ብጤ ሆኖብን እነሆ ግራ ቀኝ እንደተላጋን ከሌት እስከ ንጋት፣ ከእሁድ እስከ ሰኞ፣ ከመስከረም እስከ ጳጉሜ፣ እንዲሁ ብቻ በከንቱ እየተብከነከንን "በቆይ ብቻ ፉከራ" እህህታችንን ቀለብ አድርገን መኖርን ተለማምደናል፡፡ "እህህ እስከ መቼ!?" አለች ድምጻዊቷ ዜመኛ፡፡ ሰላም ለሕዝባችን ለዜጎችም በጎ ፈቃድ፡፡

# ዓለም አቀፍ

## ባራክ ኦባማ በፕሮዲዩሰርነት የሚሳተፉበት ፊልም ወጣ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

የመብት ተሟጋቹ ባያርድ ሩስቲን እና ሩስቲንን ወክሎ የሚጫወተው ዋና ተዋናዩ ኮልማን ዶሚንጎ በቅርቡ ኔትፍሊክስ በባያርድ ሩስቲን ሕይወት ላይ የተመሠረተ ፊልም አውጥቷል። የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዝዳንት ባራክ ኦባማ እና ባለቤታቸው ሚሼል ኦባማ በፕሮዲውሰርነት መሳተፋቸው የበርካታ ሚዲያዎችን ቀልብ ስቧል።

ለብዙዎች ጥያቄ የሆነው ግን ባያርድ ሩስቲን ማን ነው? የሚለው ነው። የአሜሪካንን ታሪክ በሚያውቁ ዘንድም ቢሆን ባያርድ ሩስቲን የሚወሳ ስም አይደለም። ፊልሙም የተሠራበት ምክንያት ይኸው ነው። ሩስቲን ጥቁሮች ከጭቆና ነፃ ለመውጣት በሚደረገው ትግል ከፍተኛ ሚና ቢጫወትም አስተዋፅዖው አይነሳም።

በሲቪል መብቶች ንቅናቄ ውስጥ ቁልፍ ሚና የነበረው ሩስቲን በአውሮፓውያኑ 1963 ማርቲን ሉተር ኪንግ ‘አይ ሃቭ ኤ ድሪም’ (ሕልም አለኝ) የሚለውን ንግግር ያደረገበትን የዋሽንግተኑን ሰልፍ ካዘጋጁት መካከልም አንዱ ነው። ምንም እንኳን የነፃነት ታጋዩ የማርቲን ሉተር ኪንግ ስም፣ እንዲሁም ንግግሩ በመላው ቢናኝም የሩስቲን ስሙ እንኳን አይጠቀስም።

ለዚህም ዋነኛ ምክንያቱ ደግሞ ሩስቲን በግልጽ የተመሳሳይ ፆታ አፍቃሪ መሆኑን በመናገሩ ነው። ጉዳዩ በወቅቱ በአሜሪካ የአደባባይ ምናብ ውስጥ ነውር እና አወዛጋቢ ጉዳይ በመሆኑ ሩስቲንን ለድብደባ ዳርጎታል። ድብደባም ብቻ ሳይሆን ከፍተኛ እንግልት ደርሶበታል፤ ታስሮም ነበር። በባራክ እና ሚሼል ኦባማ ፕሮዲውሰርነት እንዲሁም በኮልማን ዶሚንጎ መሪ ተዋናይነትም በሩስቲን ሕይወት ላይ የተመሠረተው ፊልም ለዕይታ በቅቷል።

መሪ ተዋናዩም በፊልሙ ባሳየው ድንቅ ችሎታ በፊልሙ ዘርፍ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠውን የኦስካር ሽልማት ያሸንፋል ተብሎም እየተጠበቀ ይገኛል። በፊልሙ ላይ በመሳተፉም ከፍተኛ ደስታ እንደተሰማውም ተዋናዩ ዶሚንጎ ለቢቢሲ ተናግሯል። ተዋናዩ ኦስካር ያሸንፋል የተባለውን ፊልም ብቻ ሳይሆን፣ በተጨማሪ ሌላኛውን ፊልሙን ለማስተዋወቅ ለንደን ይገኛል። ከቢቢሲ ጋር ካደረገው ቃለ ምልልስ በፊት በነበረው



**የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ እና ባለቤታቸው ሚሼል ኦባማ**

ምሽት ‘ዘ ከለር ፐርፐል’ የተሰኘ መጽሐፍን ድጋሚ ወደ ፊልም በለወጠው የዩናይትድ ኪንግደም የፊልሙ ምርቃት ላይ የቢቢሲ ጋዜጠኛ ታድሞ ነበር።

በዚህ ፊልም ላይ ተዋናዩ ሚስቱን የሚደበድብ እና አስፈሪ ገፀባሕርይን ተላብሶ ይጫወታል። የቢቢሲ ጋዜጠኛም በምርቃቱ ላይ መገኘቱን በነገረው ወቅት “እዚያ ነበርክ? እናም አሁን አልፈራኸኝም?” ሲል ዶሚንጎ ቀልዷል። ከከለር ፐርፐል በተለየ በሩስቲን ፊልም ላይ ዶሚንጎ ተወዳጅ፣ ግርማ ሞገስ የተጎናጸፈ እና መሪነት የተላበሰውን የመብት ተሟጋችን ወክሎ ነው የሚተውነው። በርካታ ተመልካቶች የሩስቲንን ታሪክ ካለማወቃቸው ጋር ተያይዞ ታሪኩ መነገሩ ትልቅ ስፍራ እንዳለው ዶሚንጎ ይናገራል። ፊልሙ ሩስቲን የሚል ርዕስ ተሰጥቶታል። ሩስቲን ተብሎ በአጭሩ ርዕስ መሰጠቱ “ጥያቄን ያጭራል። እሱ ማን ነው? ብለው እንዲጠይቁ ያደርጋል” ሲልም ተዋናዩ ይናገራል።

“የዋሽንግተኑ ሰልፍ ዋነኛው ቁልፍ ሰው እና መሐንዲስ ነበር። ዘመቻውን በማደራጀት እና በመቀየስም ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል። በእኛ ብቻ ሳይሆን በዓለም ላይ ትልቅ ተፅዕኖን ማሳረፍ የቻለ ሰው ነበር” ይላል። አክሎም “ከታሪክ መዛግብት እንዲሰረዝ ተደርጎ ነበር። አሁን ከጋረደው ጥላ አውጥተን ታሪኩን እና ማንነቱን ማዕከል ባደረገ መልኩ ማሳየት ችለናል” ብሏል።

ምንም እንኳን ተቺዎች ስለ ፊልሙ አንዳንድ ቅሬታዎችን ቢያቀርቡም ሁሉም ያለማቅማማት የሚስማሙበት ጉዳይ፣ የዶሚንጎ ድንቅ የትወና ብቃትን ነው። ኒውዮርክ ታይምስ እና ጋርዲያንን ጨምሮ በርካታ ሚዲያዎች ዶሚንጎ ከስድስት አሥርት ዓመታት በፊት የነበረውን የታሪክ ሁነት በአስገራሚ ችሎታ በመተወኑ አወድሰውታል።

ፊልሙ በጆርጅ ሲ ወልፍ የተዘጋጀ ሲሆን፣ ከዶሚንጎ በተጨማሪ ክሪስ ሮክ፣ ሲሲኤች ፓውንደር፣ ዳቪን ጆይ ራንዶልፍ እና ጄፍሪ ራይትን የመሳሰሉ ታዋቂ ተዋንያን ተሳትፈውበታል። ተዋናዩ በመብት ታጋዩ ሩስቲን ታሪክ ላይ የተመሠረተውን ፊልም ለመሥራት በርካታ ጽሑፎቹን አንብቧል። በተጨማሪም ንግግሮቹን ያካተቱ ጥናታዊ ቪዲዮዎችንም ተመልክቷል።

“የንግግሩን ቅላጼ የተረዳሁት በዚህ ወቅት ነው። አቀማመጡን፣ ሲናገር እጆቹን የሚያንቀሳቀስበት መንገድ እንዲሁም አጠቃላይ ባሕርዩን ለመረዳት ችያለሁ። ዋናው ነገር እሱን ማስመሰል ሳይሆን መንፈሱን መጨበጥ ነው” ብሏል ተዋናዩ። ከፊልሙ ጀርባ የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ባራክ ኦባማ እና ሚሼል ኦባማ የፕሮዳክሽን ኩባንያ የሆነው ሃየር ግራውንድ አለ። ሩስቲን ከሞተ በኋላም ባራክ ኦባማ ናቸው በአውሮፓውያኑ 2013 ለመብት ተሟጋቹ ፕሬዚዳንታዊ የነፃነት ሜዳሊያ የሸለሙት።

“በእርግጠኝነት ማኅበረሰቡ እንደሚያገለው እያወቀ፣ ከሥራ ሊባረር እንደሚችል እና እንደሚነቀፍም ተረድቶ ማንነቱን ያልደበቀ እና ራሱን የሆነ ደፋር ሰው ነው” ሲሉም ኦባማ የመብት ተሟጋቹን በማወደስ ተናግረው ነበር። የኦባማዎች ኩባንያ የተሳተፈበት በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመሠረተ የመጀመሪያ ፊልማቸው ሲሆን፣ ድንቅ ሥራ እንደሠሩም ተዋናዩ ይናገራል።

“ፊልሙ በጥሩ ሁኔታ እንዲሠራ የሚያስፈልገን ነገር ሁሉ እንዳለ የማረጋገጥ ኃላፊነት ነበረባቸው። የፊልም ጽሑፎቹን እንዲሁም ረቂቆችን ማንበብ ነበረባቸው። ለፊልሙ አዘጋጅ ጆርጅ በየቀኑ ዕለታዊ ማስታወሻ ይሰጡት ነበር። ምን እየሠራን እንዳለን እና እንዴት እየሠራን እንደሆነ ተረድተውት ነበር” ሲል ተዋናዩ ስለ ኦባማዎች አስተያየቱን ሰጥቷል።

በኮቪድ ወረርሽኝ ምክንያት የፊልሙ ሥራ ተቋርጦበት በነበረበት ወቅትም “በዙም ሰብስበውን አይዟችሁ ቀጥሉ እያሉ ያበረታቱን ነበር” ሲል ምስክርነቱን ሰጥቷል። ፊልሙ በኔትፍሊክስ ለዕይታ ከበቃ በኋላ ዶሚንጎ በመጪው ጥር የሚደረገውን የኦስካር ሽልማት ያሸንፋል የሚል ግምት ተሰጥቶታል። “ስለ ፊልሙ እንዲህ መነገሩ፣ እያገኘሁት ያለው ፍቅር ሁሉም ድንቅ ነው። ሽልማቱን አሸንፋለሁ ብዬ ባልወራረድም የንግግሩ ማዕከል መሆን በጣም ጠቃሚ ነው፤ ምክንያቱም እውቅና የመስጠት ያህል ነው” ብሏል።

“ሽልማቱን ባሸንፍ ደስ ይለኛል። ድንቅም ነው። ነገር ግን ለእኔ ብቻ አይደለም። ለሩስቲን ባያርድ፣ ለፊልሙ ሠሪዎች እንዲሁም ለባራክ እና ለሚሼል ኦባማ። ለሁላችንም ደስታ የሚፈጥር ነው” ብሏል።

The Ethiopian Herald
አዲስ ዘመን
BARIISAA
العلم
ወጋሕታ
BAKKALCHO
ዘመን
የህትመት ውጤቶቻችንን ለማንበብ ድረገጾችንንና ፌስቡክ ገጾችንን ይቀብሩ!
የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት
ዌብሳይት፡- www.press.et
ፌስቡክ፡- Ehiopian Press Agency

አዲስ ዘመን
ስፖርት

ይህ ቦታ
ለማስታወቂያ ክፍት ነው!

# የከዋክብት አትሌቶች ሀገር የመሮጫ መም ፈተና

ብርሃን ፈይሳ

ኢትዮጵያ በአትሌቲክስ ስፖርት የመታወቋን ያህል ዓለምና አህጉር አቀፍ ውድድሮችን የማስተናገድ አይደለም አትሌቶቿ ልምምድ ሊያደርጉ የሚችሉበት በቂና ጥራት ያለው የስፖርት ማዘውተሪያ ሥፍራ የላትም ሊባል በሚችልበት ሁኔታ ላይ ትገኛለች፡፡ ከዓመታት በፊት ውድድሮችንና የአትሌቶች ልምምድን የሚያስተናግደው መም አንጋፋው የአዲስ አበባ ስታዲየም ብቻ ነበር። ነገር ግን ስታዲየም በእድሳት ምክንያት ለዓመታት ከአገልግሎት ውጪ በመሆኑ አትሌቶችና አሠልጣኞች በተደጋጋሚ ቅሬታ ሲያሰሙ ቆይተዋል፡፡

የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን በቅርቡ ባካሄደው መደበኛ ጠቅላላ ጉባዔው ላይም ይህንኑ ጉዳይ አጽንኦት ሰጥቶ ተወያይቶበታል፡፡ ነገር ግን ችግሩ አሁንም በቀላሉ መፍትሄ የሚያገኝ አይመስልም፡፡ በኢትዮጵያ አትሌቲክስ ፌዴሬሽን የፋሲሊቲ ዳይሬክተር አቶ አሰፋ በቀለ፤ በየክልሉ ዘመናዊ ስታዲየሞች መገንባታቸውን ተከትሎ በሀገሪቱ ያለው የመም ቁጥር እያደገ መሆኑን ይናገራሉ፡፡ ይሁንና ካለው የአትሌቶች ፍላጎትና ቁጥር አንጻር በቂ ካለመሆኑም ባለፈ በርካታ ክለቦችና አትሌቶች ከሚገኙባቸው ሥፍራዎች አንጻር ሁኔታው አሳሳቢ ደረጃ ላይ እንዲደርስ አድርጎታል ይላሉ፡፡

በተለይ አዲስ የአበባ ስታዲየም ከእድሳት ጋር በተያያዘ ለዓመታት ሥራ ማቆሙን ተከትሎ


ከዋክብት ኢትዮጵያውያን አትሌቶች በመሮጫ መም እጦት መፈተናቸውን ቀጥለዋል፣

በአማራጭነት የኢትዮጵያ ስፖርት አካዳሚን መም ለልምምድና ውድድሮች መጠቀም ቢቻልም ካለበት ጫና አንጻር መጎዳቱ አልቀረም፡፡ በዚህም ምክንያት አትሌቶች ወደ ጎዳና በመውጣት ልምምድ ለመሥራት በመገደዳቸው ሕይወትን ሊያሳጣ ለሚችል አደጋ እየተጋለጡ መሆኑን ይታወቃል፡፡ ይሁንና የፌዴሬሽኑ ኃላፊነት ከድጋፍና ክትትል ውጪ ማዘውተሪያዎችን መገንባት ባለመሆኑ የፌዴራሉ መንግሥትና ክልሎች ሊያስቡበት ይገባል፡፡

በሌላ በኩል የአትሌቲክስ ማዘውተሪያ ሥፍራዎች በየክልሉ እየተገነቡ መሆኑ አበረታች ቢሆንም፤ የጥራታቸው ጉዳይ ግን አሁንም አነጋጋሪ ከመሆን ወደኋላ አላለም፡፡ ውድድሮች በሚካሄዱባቸው ወቅት አሊያም የባለሙያዎች ምልከታ በሚከናወንበት ወቅት ጉድለቶች መኖራቸው እንደሚደረስበትም ዳይሬክተሩ ይናገራሉ፡፡ አንዳንድ መሞች ረጅም ዓመት እንዲያገለግሉ ቢጠበቅም ሁለት ዓመት ሳይሆናቸው ለብልሽት ይዳረጋሉ። ይኸውም ከግንባታ ጋር በተያያዘ በሚኖር የጥራት ጉድለት የሚከሰት ሲሆን፤ በኢትዮጵያ ደረጃውን የጠበቀ ባለሙያ አሊያም ተቋም ካለመኖሩ ጋር ተያይዞ ችግሩን አስፍቶታል። ፌዴሬሽኑም በቻለው መጠን ግንባታዎች ሲከናወኑ ክትትል በማድረግ አስፈርሶ በአዲስ መልክ እንዲሠራ እስከማድረግ የሚደርስ ርምጃም ይወስዳል፡፡

በዚህም በእድሳት ላይ የሚገኘው የአዲስ አበባ ስታዲየምም ከመም ግንባታው ጋር በተያያዘ አስተያየት እንዲሰጥ አስቀድሞ ፌዴሬሽኑን ማወያየቱን ዳይሬክተሩ አስታውሰዋል፡፡ በቀጣይ በሚኖረው ሂደትም ፌዴሬሽኑ እድሳቱን ከሚያከናውነው የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ጋር በቅርበት ይሠራል፡፡ ኢትዮጵያ ከሀገር ውስጥ ባለፈ አህጉርና ዓለም አቀፍ ውድድሮችን ማዘጋጀት እንድትችል የዓለም አትሌቲክስ መስፈርቶችን ያሟላ መም ባለቤት መሆን ስለሚገባት ይህንኑ ታሳቢ ያደረገ እንቅስቃሴም እየተደረገ ነው፡፡ ይሁንና በሌሎች አካባቢዎች የሚገነቡ መሞች በባለሙያ እና ልምድ ባላቸው ተቋማት ካልተሠሩ ችግሩ መቀጠሉ አይቀሬ መሆኑንም አሳስበዋል፡፡

በተያዘው ዓመት የፓሪስ ኦሊምፒክ የሚካሄድ እንደመሆኑ አትሌቶች በአግባቡ ተዘጋጅተው ሀገራቸውን እንዲወክሉ ለማድረግ የማዘውተሪያ ሥፍራዎች መኖር አስፈላጊነት አያጠያይቅም። በመሆኑም የኢፌዴሪ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር በእድሳት ላይ የሚገኘው የአዲስ አበባ ስታዲየም መም ለብሄራዊ ቡድኑ ዝግጅት ይደርሳል የሚል ተስፋን ሰጥቷል፡፡ ከዚህ በተጓዳኝም ፌዴሬሽኑ ችግሩን ለመፍታት በእቅድ እየሠራ ሲሆን፤ በየክልሉ በመገንባት ላይ ላሉት ማዕከላት ክትትል ከማድረግ ባለፈ በራሱ አቅም ሸገር ከተማ ላይ የአሸዋ ትራክ ለመሥራት በእንቅስቃሴ ላይ መሆኑንም ዳይሬክተሩ ጠቁመዋል። በቀጣይም በሀገሪቷ ባሉት 7 የአትሌቲክስ ሥልጠና ማዕከላት በተጨማሪ የመሥራት እቅድ መኖሩን ተከትሎም እገዛውን አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡